# እውነት

እውነት - ቅጽ 1፣ ቁጥር 2

የማይሸጥ

እውነትም አርነት ያወጣችኋል/ዮሐ8፡32/

ወርኃ ሰኔ 1993 ዓ.ም.


## በወቅታዊ ዓምዶች

| | |
|---|---|
| ከተመሠረተው በቀር... | 1 |
| ከዮናስ የሚበልጥ | 1 |

## በቋሚ ዓምዶች

| | |
|---|---|
| አገልግሎት  አገልግሎት መሥዋዕት ነው | 3 |
| ቤተክርስቲያን  ቤተክርስቲያን በማቴ 16 ክፍል 2 | 5 |
| አምልኮት  በዚህ ተራራ.. . | 7 |
| በረከተ - ጥበብ | |
| - ጠበው | 14 |
| - ስለ ክርስቶስ ምን... | 14 |
| - አንተ ግን... | 14 |
| -የአገልግሎትህ ምክንያት | 15 |
| -ክርስቲያን  | 15 |
| የአንባብያን ዓምድ  | 16 |


## ከተመሠረተው በቀር ማንም ሌላ መሠረት ሲመሠርት አይችልም /1ቆሮ 3፡11/

በርእሱ የተመለከተውን መሪ ቃል ለቆሮንቶስ ሰዎች የጻፈው ሐዋርያው ጳውሎስ ነው፤ የጽሑፉም መነሻ የቆሮንቶስ ምእመናን እርስ በእርሳቸው ተከፋፍለው በተለያየ መሠረት ላይ የሚቆሙበት ሁኔታ መፈጠሩ ነው፤ ሐዋርያው ከመጀመሪያው ምዕራፍ ጀምሮ ሲናገር «ወንድሞች ሆይ በመካከላችሁ ክርክር እንዳለ ስለእናንተ የቀሎዔ ቤተሰዎች አስታውቀውኛልና» ይላል /1ቆሮ1፡11/:: በቆሮንቶስ ለሚኖሩ ሰዎች መጀመሪያ የጌታ ኢየሱስን ወንጌል ይገኙባቸዋል:: የቆሮንቶስም ሰዎች በመካከላቸው የነበሩትን ክርክሮች በፍቅር መፍታትና አብሮ መኖር ሳይችሉ ሲቀሩ እንደመፍትሔ የተከተሉት መንገድ ባገለገሉአቸው የእግዚአብሔር አገልጋዮች ስም ቡድን ማቋቋም ነበር:: ስለሆነም ከማህበሩ የተወሰነው የጳውሎስ ቡድን ለመሆን ሲወስን ሌላው ወገን ደግሞ ይሻለኛል ብሎ በማሰብ ራሱን በአጵሎስ ስም ማደራጀትን መረጠ፤ የተቀሩት ደግሞ ምናልባትም ወደ ጴጥሮስ

> ያላመኑ አዳዲስ ሰዎች በክርስቶስ ሲያምኑም ሆነ ባለማወቅ በተሳሳተና ሰው ሠራሽ በሆነ የክርስትና ሃይማኖት ክፋት ውስጥ የነበሩ ሰዎች በነበሩበት ክፋት ላይ ነቅተውበት ራሳቸውን ከዚያ አመፃ ሲለዩ በትክክል እንዲሆን እግዚአብሔር የሚፈልገው ቀድሞ ወደ ተመሠረተችውና የክርስቶስ አካል ወደሆነችው አንዲት ቤተክርስቲያን ብልት ሆነው እንዲጨመሩና ክርስቶስ ራስ እንዲሆናቸው ነው እንጂ በአንዳች ስም አዲስ ወይም ሌላ ቤተክርስቲያን እንዲመሠርቱ ወይም ቀድሞ ለተመሠረተ የሃይማኖት ድርጅት ቅርንጫፍ እንዲሆኑ

የሰበከላቸውና ወደ ጌታ ለመምጣታቸው እንደመሣሪያ የሆነው ጳውሎስ ነበር /ሐዋ.ሥ18፡1/:: ጳውሎስ አገልግሎ ከሄደ በኋላ ሌሎች አገልጋዮችም ወደ ቆሮንቶስ መጥተው በዚያ የተሰበሰበችውን ጉባኤ አገልግለዋል:: ከእነዚህም አገልጋዮች መካከልም አጵሎስ፣ ኬፋ ማለትም ጴጥሮስ በመሳባቸው ሊሆን ይችላል በጴጥሮስ ስም ራሳቸውን ሲያስቀምጡ ሌሎች ደግሞ ጳውሎስንም፣ ጴጥሮስንም አጵሎስንም አናውቅም እኛ የክርስቶስ ነን ብለው ለብቻቸው ተቀመጡ፤ ይህንንም ሀዋርያው ሲገልጥ «ይህንም እላለሁ፤ እያንዳንዳችሁ እኔ የጳውሎስ ነኝ፤ እኔስ የአጵሎስ ነኝ፤

(ወደ ገጽ 8 ይዞራል)

## እነሆ ከዮናስ የሚበልጥ ከዚህ አለ/ማቴ 12፡41/

መጽሐፍ ቅዱስ በብሉይ ኪዳን ክፍሉ በምሳሌና በጥላ ስለክርስቶስ የሚናገር እንደሆነ ግልጥ ነው፤ በማደሪያው ድንኳን ውስጥ የሚገኙት ንዋያተ ቅድሳትና በውስጧም የሚፈፀሙት የመሥዋዕት አይነቶች እንዲሁም ሌሎች ሥርዓታት በጥላነት ስለክርስቶስ ይናገሩ ነበር፤ በተጨማሪም በህልምና በራእይ የተገለጡ እንዲሁም ታሪክና ድርጊት የሆኑ በምሳሌነት ስለ ክርስቶስ የሚናገሩ ብዙ የብሉይ ኪዳን ክፍሎች አሉ፤ ከዚህም አንፃር ዮናስ በእርሱ በኩል በተገለጠው ሁኔታ በምሳሌነት ስለ ክርስቶስ የሚናገር የብሉይ ኪዳን ነቢይ ነው::

አንዳንዶቹ ምሳሌያት ከአማናዊው ነገር ጋር በቀጥተኛ መንገድ የሚነጻጸሩ ሲሆኑ ሌሎቹ ደግሞ የማወዳደር /ማበላለጥ/ መንገድን ተከትለው የሚነጻጸሩ ናቸው:: ዮናስ ከክርስቶስ ጋር ሊነጻጸር የቻለበትን መንገድ ስንመለከት ክርስቶስ ከዮናስ ይልቅ የሚበልጥ መሆኑን በመግለጥ በሁለተኛው መንገድ የተነጻጸረ እንደሆነ እንረዳለን::

«እነሆ ከዮናስ የሚበልጥ ከዚህ አለ» የሚለውን ማራኪ ቃል የተናገረው ራሱ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው:: ይህንንም ቃል የተናገረው «መምህር ሆይ ከአንተ ምልክትን ልናይ እንወዳለን» ላሉት አይሁድ ነው:: እነዚህም አይሁድ ከጻፎችና ከፈሪሳውያን መካከል አንዳንዶቹ ናቸው፤

(ወደ ገጽ 2 ይዞራል

# እውነት ጋዜጣ

**«እውነትም አርነት ያወጣችኋል» በሚለው የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ላይ ተመሥርቶ በየሁለት ወሩ የሚወጣ የክርስቲያኖች ጋዜጣ ነው::**

**ዋና አዘጋጅ፤ መዘምር በለጠ**
**ም/ዋና አዘጋጅ፤ ደጉ ምሕረቴ**


# መልእክተ እውነት

## የክርስቲያኖች ማንነት

በኢየሱስ ክርስቶስ የሚያምኑ ወገኖች በዚህ ዓለም ሲኖሩ ያላቸው ማንነት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተገልጧል፤ መጽሐፍ ቅዱስ የሚያሳየን የክርስቲያኖች ማንነት ክርስቶስ በምድር ሳለ የነበረውን ማንነት ነው:: ምእመናን ኢየሱስ ክርስቶስን እንዲመስሉ የእግዚአብሔር ውሳኔ ነው:: ጳውሎስ ስለዚህ ጉዳይ ሲጽፍ «ልጁ በብዙ ወንድሞች መካከል በኵር ይሆን ዘንድ አስቀድሞ ያወቃቸው የልጁን መልክ እንዲመስሉ አስቀድሞ ወስኗልና» ብሏል/ሮሜ.8፡29/:: በመሆኑም አማኞች ስለማንነታቸው ለሚጠይቋቸው ሰዎች ኢየሱስ ስለማንነቱ በተጠየቀ ጊዜ የሰጠውን ዓይነት መልስ ሊመልሱ ይገባቸዋል::

ጌታ ኢየሱስ በዓመፀኞች ተይዞ በጲላጦስ የፍርድ ወንበር ፊት በቀረበ ጊዜ ስለማንነቱ ተጠይቆ የሰጠው መልስ ለዚህ አብነታችን ነው:: በዮሐ.18፡33-38 ያለውን ስናነብ ጲላጦስ ኢየሱስን «የአይሁድ ንጉሥ አንተ ነህን?» ብሎ በጠየቀው ጊዜ ኢየሱስ መልሶ «አንተ ይህን የምትለው ከራስህ ነውን ወይስ ሌሎች ስለ እኔ ነገሩህን?» ሲለው እንመለከታለን፤ ከዚህም የምንረዳው በራሱ በጲላጦስም ሆነ በሌሎች ሰዎች ዘንድ ስለ ኢየሱስ ማንነት በግምት የሚባልና የሚነገር ነገር እንደነበረ ነው፤ ግምቱም «ኢየሱስ የአይሁድ ንጉሥ ነው» የሚል ነው:: እንዲህም ሲሉ በምድር፣ በአይሁድ ላይ መንግሥትን የሚመሠርት የአይሁዳውያን ንጉሥ እንደሆነ ያስቡ ነበር:: በቁ.35 ላይ እንደምናነበው ጲላጦስ «እኔ አይሁዳዊ ነኝን? ወገኖችህና የካህናት አለቆች ለእኔ አሳልፈው ሰጡህ ምን አድርገሃል?»ብሎ ከተናገረው ቃል እንደምንረዳው «ኢየሱስ የአይሁድ ንጉሥ ነው» የሚለውን ወሬ ከራሳቸው ከአይሁድ የሰማው ይመስላል፤ አይሁድ ንጉሣችን ነው ብለው አምነውበት ሳይሆን ከቄሣር ቤተመንግሥት ለማጣላት እንዲያመቻቸው «የአይሁድ ንጉሥ ነኝ» ይላል እያሉ በሐሰት ይከሱት ነበር /ሉ23፡2፣ዮሐ19፡21/ እንደዚሁም ምድራዊ ሐሳብ ያላቸው እንደ አይሁድ ያሉ ዓለማዊ ሃይማኖት ያላቸው ሰዎችና እንደ ጲላጦስ ያሉ ምድራዊ አኗኗርን ብቻ የሚከተሉ ሰዎች በጥላቻ ለምእመናን ሐሰተኛ ማንነትን ሊሰጡ ይችላሉ፤ ለመክሰስና ስማቸውን በክፉ ለማንሣት ወይም እንደራሳቸው ዓይነት ምድራዊ ቅርጽ ለመስጠት የሚገምቱትን ማንነት በአማኞች ላይ ሊያስወሩ ይችላሉ፣ ይሁን እንጂ ጌታ ኢየሱስ ለጲላጦስ የሰጠው ቀጣዩ መልስ በእርሱ በኢየሱስ የምናምንና የእርሱ ደቀመዛሙርት የሆንን ሁላችንም ልንሰጠው የሚገባ መልስ ነው፤ እርሱም እንዲህ አለ፤ «መንግሥቴ ከዚህ ዓለም አይደለችም፤ መንግሥቴስ ከዚህ ዓለም ብትሆን ወደ አይሁድ እንዳልሰጥ ሎሌዎቼ ይዋጉልኝ ነበር፤ አሁን ግን መንግሥቴ ከዚህ አይደለችም» አለ/ቁ፡36/:: ጌታ ኢየሱስ በአይሁድ መካከል ምንም ስፍራ አልነበረውም፤ ወደዚህ ዓለም የመጣውም የአይሁድን ምድራዊ መንግሥት ሊመሠርት አልነበረም፤ የኢየሱስ መንግሥት መንግሥተ-ሰማያት /የሰማያት መንግሥት/ ነበረች:: ጲላጦስ ይህንን ቢረዳ ኖሮ ምንም ዓይነት ሥጋት ባላደረበት ነበር:: ዛሬም ሐሳባቸው ምድራዊ የሆነ ሰዎች በእኛ በምእመናን ማንነት ዙሪያ ብዙ ይጨነቁ ይሆናል፤ የእኛ ማንነት ብዙ ያሳስባቸው ይሆናል፤ እኛ ግን በዚህ ዓለም ምንም የለንም፤ ሀገራችንም በሰማይ ነው/ፊልጵ3፡20/፤ ምክንያቱም የእምነታችን ራስና ፈጻሚ የሆነው ኢየሱስ መንግሥቱ ሰማያዊ ናት እንጂ ከዚህ ዓለም አይደለችም፤ መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚል «በዚህ የምትኖር ከተማ የለችንም»/ዕብ13፡14/:: በዚህ ዓለም ለጥቂት ጊዜ ስንኖር እንኳ የሚኖረን ስፍራ ኢየሱስ በዚህ ዓለም ይዞት የነበረው የነቀፋ ስፍራ ነው፤ እርሱን የጠላችው ዓለም ደቀመዛሙርቱንም ትጠላለችና፤ ስለዚህ እርሱ በዚህ ዓለም ይኖር በነበረበት መከራ ልንኖር ከእርሱ ጋር ተጣብቀናል::

ሆኖም ክርስቲያኖች «እነማን ናችሁ?» የሚለው ጥያቄ ከዚህ ዓለም ሰዎች በተደጋጋሚ ሲቀርብላቸው የሚመልሱትን የመጨረሻ መልስ ከጌታ ከኢየሱስ ይማራሉ፤ የጲላጦስ የምርምር ጥያቄ ቀጥሎ «እንግዲያ ንጉሥ ነህን?» ባለው ጊዜ ጌታችን የመለሰለት ቃል «እኔ ንጉሥ እንደሆንኩ አንተ ትላለህ፤ እኔ ለእውነት ልመሰክር ስለዚህ ተወልጃለሁ፤ ስለዚህም ወደ ዓለም መጥቻለሁ ከእውነት የሆነ ሁሉ ድምፄን ይሰማል» የሚል ነው/ቁ.37/:: እንደ አይሁድና እንደ ጲላጦስ ያሉ ሰዎች የሚሉንን ያንኑ አባባል የማንነታችን መግለጫ አናደርገውም፤ ያን ምድራዊ ግምታቸውን «እናንተ ትላላችሁ» ብለን ለእነርሱ ልንተወው ይገባል፤ የእኛ የክርስቲያኖች ማንነት ግን በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ከተገለጠው እውነት ጋር የሚነገር ሊሆን ይገባል:: «እኛ ስለ እውነት ልንመሰክር በምድር ላይ የምንኖር ነን፤ ከእውነት የሆነም ይሰማናል» በማለት ራሳችንን በዚህ ዓይነት ልንገልጥ ይገባል:: ምናልባት የዚህ ዓለም ሰዎች ከአንድ የሃይማኖት ጎራ መድበው እነ እገሌ ናቸው እያሉ የመሰላቸውን ሊያስቡም ሆነ ሊናገሩ ይችሉ ይሆናል፤ ያንን ግን የሚሉት እነርሱ ናቸው፤ የክርስቲያኖች ማንነት ግን የሚገኘው «እውነትን ሊመሰክሩ በዚህ ዓለም የሚኖሩ» በሚለው ቃል ውስጥ ነው::

እኛ «እውነት» በሚል ስያሜ የምትጠራው የዚህች ጋዜጣ አዘጋጆችና ከእኛም ጋር በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም የሚሰበሰቡ ክርስቲያን ወንድሞችና እኅቶችም ማንነታችን ይህ ብቻ እንደሆነ በአንባብያን ዘንድ የታወቀ ይሁን እንላለን!!

## ከዮናስ የሚበልጥ..ከገጽ 1 የዞረ

ጻፎች የሚባሉት የኦሪት መጻሕፍትን የሚገለብጡ /የሚያባዙ/ ሲሆኑ ፈሪሳውያን ደግሞ ሕግ አጥባቂዎችና ሕግ አዋቂዎች ናቸው:: ከዚህም የተነሣ ጻፎችና ፈሪሳውያን የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት የሚተርኩትን ነገር ያውሉ ብሎ ማሰብ ይቻላል:: በመሆኑም በትንቢተ ዮናስ የተመዘገበውን የዮናስን ታሪክ በሚገባ ሊያውቁ እንደሚችሉ እሙን ነው፤ ይልቁንም በዮናስ ታሪክ ውስጥ የታየውን አስደናቂ ምልክት ማለትም በዓሣ አንባሪ ሆድ ውስጥ ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት አድሮ መውጣቱንና ለነነዌ ሰዎች መስበኩን በሚገባ የሚያውቁ ሰዎች ናቸው፤ አይሁድ ደግሞ ምልክትን ይሻሉና /1ቆሮ1፡22/ እንዲህ ያለውን ምልክት በጣም እንደሚያጠኑት ደጋግመውም እንደሚመሠክሩለት መገመት ይቻላል:: እነዚህ ሰዎች ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም በማስተማር ዘመኑ በተደጋጋሚ ያደረጋቸውን ምልክቶች አይተዋል /ማቴ8፡1-34፣ 9፡1-8፣ 18-34፤ 12፡9-22/:: ታዲያ ሕዝቡ «እንዲህ ያለ በእስራኤል ዘንድ ከቶ አልታየም፤ እንጃ ይህ ሰው የዳዊት ልጅ ይሆንን?» እያሉ ሲደነቁ ፈሪሳውያን ግን «በአጋንንት አለቃ አጋንንትን ያወጣል» ወይም «ይህ በብዔል ዜቡል በአጋንንት አለቃ ካልሆነ በቀር አጋንንትን አያወጣም» ይሉ ነበር/ማቴ.9፡34፤12፡24/:: በዓይን የሚታየውንና በግልጥ ምልክት የተረጋገጠውን እውነት ከሕዝብ ሁሉ ተለይቶ መቃወም የጻፎችና የፈሪሳውያን ልማድ ነበር፤ ቅን ልብ ቢኖራቸው ኖሮ ያዩአቸው ምልክቶች ሁሉ የኢየሱስን መሲሕነትና የእግዚአብሔር ልጅነት ለማመን የሚያስችሏቸው ነበሩ:: ነገር ግን ኢየሱስ አጋንንትን በሥልጣን ማዘዙና ካደሩባቸው ሰዎች ማስወጣቱ ሊክዱት የማይችሉት ተአምር ቢሆንም ስለሚጠሉት ብቻ በአጋንንት አለቃ አጋንንትን ያወጣል ለማለት ደፈሩ፤ ከእነርሱ መካከል እውነተኛ ሰው የነበረው ፈሪሳዊው ኒቆዲሞስ እንደመሰከረው ኢየሱስ ያደርጋቸው የነበሩትን ምልክቶች ማድረግ የሚችል አልነበረም/ዮሐ.3፡2/:: ነገር ግን 5 እንጀራ እና 2 ዓሣን ያበረከተበትን ምልክት በፊታቸው ባደረገ ጊዜ «እንኪያ አይተን እንድናምንህ ምን ምልክት ታደርጋለህ? ምንስ ትሠራለህ? ይበሉ ዘንድ ከሰማይ እንጀራ ሰጣቸው ተብሎ እንደተጻፈ አባቶቻችን በምድረ በዳ መና በሉ»

*(ወደ ገጽ 4 ይዞራል)*

# አገልግሎት

እርሱ ደግሞ በመንፈስ እንጂ በፊደል ለማይሆን ለአዲስ ኪዳን አገልጋዮች እንሆን ዘንድ አበቃ/2ቆሮ3:6/::



በጌታ የተቀበልከውን አገልግሎትህን እንድትፈጽመው ተጠንቀቅ /ቆላ4:17::

የሚያገለግለኝ ቢኖር ይከተለኝ/ዮሐ12:26/

## አገልግሎት መሥዋዕት ነው
### ሮሜ12፡1

ስለመንፈሳዊ አገልግሎት ሲነሳ በአብዛኛው የሚታሰበን የአገልጋዩ ማንነት ነው:: ወደ አንድ መንፈሳዊ አገልግሎት የሚጋብዙ ጥሪዎችና ማስታወቂያዎችም ከሁሉ በፊት በአገልግሎቱ ምንነት ሳይሆን በአገልጋዩ ማንነት ልባችንን ለመማረክ ሆን ተብለው የተዘጋጁ ሆነው እናገኛቸዋለን፤ የአገልግሎት ምንነትና የአገልጋይ ማንነት የማይለያዩ ቢሆኑም በዘመናችን ለአገልግሎት የሚሰጠው ትርጉምና አገልጋይም እንደአገልጋይ የሚታወቅባቸው መታወቂያዎች ፈርጀ ብዙ ከመሆናቸው የተነሳ ግራ መጋባት በመኖሩ መደነጋገርን ለማስቀረት ሲባል የአገልግሎትን ምንነትና የአገልጋይን ማንነት ከእግዚአብሔር ቃል አንጻር በግልጥ የማስቀመጡ አስፈላጊነት አያጠያይቅም:: አገልጋይም ማንነቱን ማግኘት ያለበት ከትክክለኛ መንፈሳዊ አገልገሎት ምንነት አኳያ ብቻ ነው፤ አንደ ሰው «የተቀባ ነው» መባሉ ብቻውን ያን ሰው አገልጋይ ሊያሰኘው አይችልም፤ አገልግሎቱም በሌሎች ሰዎች ስለተወደደ ወይም ሰዎች «ተባርከንበታል» ስላሉ ብቻ አገልግሎት ሊሰኛ አይበቃም፤ አገልጋይም የጌታ አገልጋይ ሊሰኛ የሚበው አገልግሎቱ በእግዚአብሔር ቃል ተመዝኖ ምልዓት ሲያገኛና የእግዚአብሔር ቃል ለአገልግሎት የሚሰጠውን ትርጉም ይዞ ሲገኛ ነው:: ከዚህ አንጻርም በመጽሐፍ ቅዱስ ስለአገልግሎት ከሚናገሩት በርካታ ምንባቦች ውስጥ አንዱን ብቻ ማየቱ በቂ ይሆናል:: ይህም ምንባብ በሮሜ12:1 ላይ የምናገኘው ሲሆን እርሱም: «ሰውነታችሁን እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኛና ሕያው ቅዱስም መሥዋዕት አድርጋቸሁ ታቀርቡ ዘንድ በእግዚ አብሔር ርኅራኄ እለምናችኋለሁ፤: እርሱም ለአእምሮ የሚመች አገልግሎታችሁ ነው» የሚል ነው:: «ለአእምሮ የሚመች» ተብሎ የተተረጎመው የግሪክ ቃም /λογικ ην/ ሎጊኬን የሚል ሲሆን ቀጥተኛ ትርጉሙም መንፈሳዊ ምክንያት ሊሰጥበት የሚችል፣ በበቂ መንፈሳዊ እውቀት ላይ የተመሠረተና አግባብነት ያለው ማለት ነው:: ለአእምሮ የሚመች የሚለው ትርጉም በራሱ ስህተት ባይሆንም ቃሉ ከሚሰጠን እውነተኛ ትርጉም በተለየ መንገድ ለሰው አእምሮ የሚመች እያደረጉ ማገልገልን ሊያሳይ ስለሚችል በምትኩ «አግባብነት ያለው አገልግሎት» ብሎ መተርጎሙ ተገቢ ይሆናል:: የእንግሊዝኛውም ፍቺ intelligent service ይለዋል:: አግባብነት ያለው ስንልም አግባብነቱ ከሰው አኳያ ሳይሆን ከእግዚአብሔር አኳያ ነው:: ከእግዚአብሔር ረገድ አግባብነት ያለው አገልግሎት ደግሞ ሰውነትን ለእግዚአብሔር «ደስ የሚያሰኛና ህያው ቅዱስም መሥዋዕት» አድርጎ ማቅረብ እንደሆነ በግልጥ እናነባለን:: ራሱን ለእግዚአብሔር የሰጠ አገልጋይ ለሰውነቱ አይሰስትም፤ ድካሙን አይቆጥርም፤ ራሱን አሳልፎ ሰጥቷልና መዋረድም ሆነ መክበር ለእርሱ ገንዘቡ አይደለም:: በሰዎች መናቅም ሆነ ተቀባይነትን ማግኘት ለእርሱ ለውጥ የለውም፤ መራብም ሆነ መጥገብ፣ ማግኘትም ሆነ ማጣት ከአገልግሎት አያግደውም፤ በሥራውም አይመካም፤ ሞትንም ሆነ መከራን አይፈራም:: ከዚህም በተጨማሪ ለእግዚአብሔር መሥዋዕት ሆኖ የሚቀርበው ይህ ሰውነት እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኛና ሕያው ቅዱስም እንዲሆን ይገባል:: ለእግዚአብሔር የሚቀርብ መሥዋዕት ምን ጊዜም እንዲሁ ሊሆን ያስፈልገዋልና፤ እግዚአብሔር ሕያውና ቅዱስ በመሆኑ የሚቀርብለት መሥዋዕትም እንዲሁ ሊሆን ይገባዋል::

አንድ አገልጋይ የሚያገለግለው አገልግሎት አግባብነት ያለው አገልግሎት ሊሰኛ የሚችለውም አገልጋዩ ሰውነቱን «መሥዋዕት» አድርጎ ለእግዚአብሔር ሲያቀርብ ነው:: ራሱን የሚቆጥብ፣ ለድካሙም የሚራራ፣ ለሰውነቱም የሚሳሳ ምቹ መጓጓዣ ካልቀረበለት በተገኘው ወይም በገዛ እግሩ ሄዶ ሊያገለግል የማይችል ሰው አገልግሎቱ ገና እግዚአብሔር አገልግሎት ብሎ ወደሚጠራውና ደስ ወደሚሰኛበት ደረጃ አልደረሰምና አገልጋይ ተብሎ ሊጠራ አይገባም:: ምቾቱንም የሚያስቀድም ሰው ማገልገል የሚፈልገው እንግልት በሌለበት ቦታ ብቻ ነው::

ሙሴ በቤተመንግሥት ያደገ እንደመሆኑ መጠን ወገኖቹን ነጻ ለማውጣት ያለውን ሐሳቡን ለመፈጸም የሚችልባቸው ሌሎች አማራጮች ሊኖሩት እንደሚችሉ አያጠራጥርም፤ ለምሳሌ ስለወገኖቹ ፈርኦንን ማነጋገር ወይም እርሱ ወደ ሥልጣን የሚመጣበትን ወቅት ጠብቆ ወገኖቹን ነጻ ማውጣት ይችል ነበር፤ እነዚህ መንገዶች ሙሴን ወደ እንግልት፣ ስደትና ችግር የማይከቱ ናቸው፤ በሌላ አባባልም የሙሴን የሕይወት መሥዋዕትነት የማይጠይቁ ናቸው፤ ሙሴም መሥዋዕትነት የሌለው አገልግሎት «አገልግሎት» አለመሆኑን ያውቃልና «ከእግዚአብሔር ሕዝብ ጋር መከራ መቀበልን መረጠ፤ ብድራቱን ትኩር ብሎ ተመልክቷልና» /ዕብ11:26/:: ጌታ ኢየሱስም በአባቱ እቅፍ ሆኖ ስለእኛ መጸለይ ይችል ነበር፤ ሳይሞትም እስከዛሬ ድረስ መልካምን እያደረገ በምድር ላይ መመላለስ ይችል ነበር፤ ሆኖም ይህ ሁሉ ዘላቂ መፍትሔ እንደማያመጣ ያውቅ ስለነበር «የስንዴ ቅንጣት በምድር ወድ ካልሞተች ብቻዋን ትቀራለችና ብትሞት ግን ብዙ ፍሬ ታፈራለች»/ዮሐ12:24/ ብሎ ውድ ነፍሱን ለሰው ልጆች ሲል መሥዋዕት አድርጎ ሰጠ:: እንደዚሁም በሌላ ጊዜ «የሰው ልጅ ሊያገለግልና ነፍሱን ለብዙዎች ቤዛ ሊሰጥ እንጂ እንዲያገለግሉት አልመጣም» በማለት አገልግሎቱ የመሥዋዕትነት አገልግሎት እንደሆነ ተናግሯል/ማር10:45/:: እንግዲህ ይህ ሁሉ አገልግሎት ማለት መሥዋዕት ማለት እንደሆነ የሚያስገነዝብ ነው፤ ያውም መላ ሰውነታችንን የሚጠይቅ መሥዋዕት! ያለ መሥዋዕትነት ማገልገል ለሰው ደስ የሚያሰኘው ቢሆንም ለእግዚአብሔር ደስ አያሰኘውም፤ ፍሬውም የእግዚ ብሔር ፍሬ አይደለም፤ አገልግሎቱም አግባብነት የለውም:: ሰውነታችን መሥዋዕት ሆኖ ሳይሰጥ በማንጎዳበት ሁኔታ ወንጌልን ለማዳረስ የሚደረገው ጥረት ወዴትም ሊያደርስ እንደማይችል የጌታ የኢየሱስ ተከታዮች ሁሉ ልብ ሊሉት ይገባል:: የሚያሳዝነው ደግሞ ወንጌልን ያለ መሥዋዕትነት ለማገልገል መፈለጉ ብቻ ሳይሆን ወንጌልን ለዚህ ዓለም ኑሮ ማሻሻያ፣ የግል ኢኮኖሚ ማዳበሪያና መክበሪያ ለማድረግ እንዲመቻቸው ሲሉ የአገልግሎት ተቋማትን የሚመሠርቱ፣ የመሥዋዕትነት ወንጌልንም «የድሃ ወንጌል» ብለው የሚያጣጥሉ፣ ከምእመናን ላይ አታለው በሚሰበስቡት ገንዘብ እየተቀማጠሉ በመከራ የተሰጠ በከቸውን ወንጌል «የብልጽግና» መሰላል ለማድረግ የተነሡ ሰዎች በምድር ላይ መበርከታቸው ነው:: እንደእነዚህ ያሉት

*(ወደ ገጽ 12 ይዞራል)*

## ከዮናስ የሚበልጥ...ከገጽ 2 የዞረ

በማለት ያዩትን አስደናቂ ምልክት ሊያልሉ ሞከሩ /ዮሐ.6፡30-31/:: ጌታ ኢየሱስ «ክፉ ትውልድ» ብሎ እንደጠራቸው ሁሉ የሰውን ልጅ የመጨረሻ የክፋት ባሕርይ ተላብሰው ስለነበር እርሱ ሲያደርጋቸው የነበሩትን ታላላቅ ምልክቶች እያዩ ለማመን ተሣናቸው፤ እነዚህ ሰዎች ክፉ ብቻ ሳይሆኑ አመንዝራ ትውልድም ነበሩና በየጊዜው የተለያየ ምልክትን ማየት ይፈልጋሉ እንጂ በታየው ምልክት አምነው የኢየሱስን የእውነት ቃል ተቀብለው ንስሐ ሊገቡ አልቻሉም:: እንደሚታወቀው «አመንዝራ» የሚለው ቃል በሚያደርገውና በሚያየው ነገር የማይረካ፣ እዚህም እዚያም የሚል፣ ያልተገደበ ፍላጐት ያለው፣ በፊት ያየውንና የያዘውን እየናቀ ሌላ አዲስ ነገርን የሚፈልግ በብዙ ነገሮችና ሁኔታዎች የተጠመደ ሰውን ያመለክታል:: እንዲህ ዓይነት ትውልድ በጌታ በኢየሱስ ሲደረግ በሚያየውና፣ ሲነገር በሚሰማው በአንድ ነገር አይረካም፤ አይረታምም፤ እንዲያውም በምትኩ ለበፊቶቹ ምልክቶችና ስብከቶች የነበረውን አድናቆት እየተወ ሌላ አዲስ ምልክትና አዲስ ትምህርት ፍለጋ አንዴ እዚህ አንዴ እዚያ ሲቅበዘበዝ ይኖራል:: ታዲያ ለእንዲህ ዓይነት ክፉና አመንዝራ ትውልድ ምን ምልክት ይሰጠዋል?

### ከነቢዩ ከዮናስ ምልክት በቀር ሌላ ምልክት አይሰጠውም

ጌታ ኢየሱስ ራሱ ከአንዴም ሁለት ጊዜ በግልጥ እንደተናገረው ለእንደዚህ ዓይነት ክፉና አመንዝራ ትውልድ «ከነቢዩ ከዮናስ ምልክት በቀር ሌላ ምልክት አይሰጠውም /ማቴ12፡39፣ ማቴ16፡4/ ተመልከት/:: ጌታችን ኢየሱስ የጠቀሰው በነቢዩ በዮናስ የታየው ምልክት ዮናስ በዓሣ አንባሪ ሆድ ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት ማደሩ ነው:: በትንቢተ ዮናስ ላይ እንደተገለጠው ዮናስ ወደ ታላቂቱ ወደ ነነዌ ከተማ ሄዶ እንዲሰብክ ከእግዚአብሔር የተላከ ነቢይ ነበር:: ለእግዚአብሔር ባለመታዘዝ ወደነነዌ ከመሄድ ይልቅ ወደተርሴስ በመርከብ ቢኰበልልም እግዚአብሔር በባሕሩ ላይ ማዕበል አሥነስቶ የዮናስን አለመታዘዝ በተሳፋሪዎቹ መካከል ከገለጠ በኋላ ወደ ባሕር እንዲጣል አደረገው፤ በባሕሩ ውስጥ እርሱን የሚውጥ ዓሣ አንባሪም እንዲዘጋጅ አደረገ፤ ከሦስት ቀንም በኋላ እግዚአብሔር ዓሣውን አዘዘው፤ ዓሣውም ዮናስን በየብስ ላይ ተፋው /ዮና1፡1፣2፡11/:: በዮናስ ላይ የታየው ምልክትም ይህ በዓሣ ሆድ ውስጥ ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት መኖሩ ነው /ዮና2፡1/::

ኢየሱስን «ከአንተ ምልክት እንድናይ እንወዳለን» ብለው የጠየቁት ጻፎችና ፈሪሳውያን ይህን በዮናስ ላይ የታየውን ምልክት በእርግጥ በዓይናቸው አላዩም፤ ነገር ግን ከነቢያት መጻሕፍት ማለትም ከትንቢተ ዮናስ ውስጥ አንብበው የሚያውቁ ነበሩ:: ይሁን እንጂ ኢየሱስ ከነቢዩ ከዮናስ ምልክት በቀር ሌላ ምልክት አይሰጠውም አላቸው:: ኢየሱስ ራሱ ብዙ ምልክቶችን እያደረገ በነበረበት በዚያ ዘመን የዮናስን ምልክት ለዚያ ትውልድ በቂ እንደሆነ መናገሩ እግዚአብሔር በኋላ ዘመን ለሚነሣ ትውልድ ቀድሞ የተደረገውን ምልክት በበቂ ማስረጃነት እንደሚጠቀምበትና የዚያንም ትውልድ ምልክት የማየት ፍላጐት ለማሟላት ብሎ ሌላ ምልክት እንደማያደርግ ያስረዳል፤ እንዲሁም የኋላ ዘመን ትውልድ ምንም እንኳ በዓይኑ ባያያቸውም በቅዱሳት

> ፈጣሪ ከፍጡር፣ አምላክ ከነቢይ የሚበልጥበትን መጠን በምን መለካት ይቻላል? ስለዚህ ጌታ ኢየሱስ ዮናስን ምን ያህል ይበልጠዋል? ተብሎ ቢጠየቅ እንዲያው ዝም ብሎ «ያለ ልክ» ይበልጠዋል ከማለት በቀር ሰው ሊናገረው የሚችለው ልክ የለውም::

መጻሕፍት ተመዝግቦ የሚያነባቸውንና ሁልጊዜም በየስብከቱ የሚሰማቸውን ታላላቅ ምልክቶችን ሁሉን የሚያጸኑ ማስረጃዎች መሆናቸውን አውቆ በመቀበል ሊያምን እንደሚገባ ያስገነዝባል::

አንድ ክርስቲያን የሚያምነውን የወንጌል ቃል የሚያጸኑለት የተትረፈረፉ ምልክቶች በቅዱሳት መጻሕፍት ተመዝግበውለታል፤ ኢየሱስ ያደረጋቸውን ምልክቶች በተመለከተ ከተጻፉትም ውጪ ብዙ ምልክቶች ተደርገው እንደነበረ ተገልጧል/ዮሐ 20፡30/:: በሐዋርያትም እጅ ብዙ ድንቅና ምልክት በሕዝብ መካከል ይደረግ ነበር/የሐ.ሥ.2፡43፣5፡12/:: እነዚህም በሐዋርያት እጅ ይደረጉ የነበሩት ምልክቶች የሐዋርያነታቸው ምልክት በመሆን ያገለግሉ ነበር /2ቆሮ12፡12/:: የምልክቶቹ ዋና ዓላማ ግን ሐዋርያት ከጌታ የሰሙትን የእውነት ቃል ለሌሎች ሲያስተላልፉ ሉ ከእግዚአብሔር መሆኑን ማጽናት /ማረጋገጥ/ ነበር/ማር16፡20፣ ዕብ2፡4/:: እነዚህ ሁሉ ምልክቶች የኋለኛው ዘመን ትውልድ ሳያያቸው ሊያምንባቸው የሚገቡና የእግዚአብሔርን ቃል ሊያረጋግጡለት የሚችሉ ምልክቶች ናቸው፤ በእነዚህ ሁሉ ምልክቶች ሳይረካ ቀርቶ እንደገና ሌላ ምልክት ሊያይ የሚወድ ቢኖር እርሱ ክፉና አመንዝራ ትውልድ ነው:: ለዚህ ትውልድ ደግሞ ከነቢዩ ከዮናስ ምልክት በቀር ሌላ ምልክት አይሰጠውም፤ ነገር ግን ለእኛ እንደዮናስ የሚሆንልን ማን ነው? በእርሱስ ላይ የታየው ዋነኛ ምልክት ምንድር ነው?

### «እነሆ ከዮናስ የሚበልጥ ከዚህ አለ»

ኢየሱስ ለዚህ ክፉና አመንዝራ ትውልድ እንደ ዮናስ የሚታይ ብቻ ሳይሆን «ከዮናስ የሚበልጥ» መሆኑን ራሱ በማያወላውል ቃል ተናግሯል፤ ጌታ ኢየሱስ ከዮናስ የሚበልጥበትን መጠንም የሰው ልጅ በምንም ዓይነት መስፈሪያ /መለኪያ/ ሊናገረው አይችልም፤ ምክንያቱም በሥጋ ተገልጦ ለምልክት ፈላጊዎች መልስ እየሰጠ ያለው ኢየሱስ የነቢዩ የዮናስ ፈጣሪ ብሎም ዮናስን ወደነነዌ የላከው አምላክ እርሱ ነው:: ፈጣሪ ከፍጡር፣ አምላክ ከነቢይ የሚበልጥበትን መጠን በምን መለካት ይቻላል? ስለዚህ ጌታ ኢየሱስ ዮናስን ምን ያህል ይበልጠዋል? ተብሎ ቢጠየቅ እንዲያው ዝም ብሎ «ያለ ልክ» ይበልጠዋል ከማለት በቀር ሰው ሊናገረው የሚችለው ልክ የለውም::

ለመሆኑ ከነቢዩ ዮናስ በሚበልጠው በጌታ በኢየሱስ ላይ የታየው ምልክት ምንድር ነው? የሚለው ደግሞ ቀጣዩ ጥያቄ ነው:: በእርግጥ ከላይ እንደተጠቀሰው ጌታ ኢየሱስ እጅግ ብዙ ታላላቅ ምልክቶችን በሕዝብ ሁሉ ፊት አድርጓል፤ የታወሩ ዓይኖችን አብርቷል፤ ለምጻሞችን አንጽቷል፤ ሽባዎችን ተርትሯል፤ ሙታንን አስነሥቷል፤ ኅብስት አበርክቷል፤ በባሕር ላይ ሄዷል፤ ነፋሳትና ማዕበላትን ፀጥ አድርጓል.. .. ወዘተ:: ይሁን እንጂ እነዚህን ሁሉ ምልክቶች ሲያደርግ እያዩና እየሰሙ አልረካ ብለው እንደገና ምልክትን ለማየት ለጠየቁት ሰዎች ኢየሱስ ይሰጣቸው የነበረው መልስ ከእነዚህ ዓይነት ምልክቶች አንዱን በመጥቀስ ሳይሆን ሞቱንና ትንሣኤውን ነበር:: በዚሁ እየተነጋገርንበት ባለንው ንባብ ውስጥም ጌታችን ሲመልስ «ዮናስ በዓሣ አንባሪ ሆድ ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት እንደነበረ እንዲሁ የሰው ልጅ በምድር ልብ ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት ይኖራል» በማለት በግልጽ ተናግሯል /ማቴ12፡40/:: የሰዎችን አለመታዘዝ /ኃጢአት/ ተሸክሞ በመስቀል ላይ ለመሞትና ወደ መቃብርም ገብቶ በምድር ልብ ውስጥ ሦስት ቀንና

*(ወደ ገጽ 6 ይዞራል)*

# ቤተክርስቲያን

ኀበ ሀለዉ ክልኤቱ ወሠለስቱ ጉቡኣን **በስምየ** ህየ ሀለውኩ አነ ማዕከሎሙ /ማቴ18፡20/



ሁለት ወይም ሦስት **በስሜ** በሚሰበሰቡበት በዚያ በመካከላቸው እሆናለሁ /ማቴ18፡20/

## ቤተክርስቲያን በማቴ 16 ክፍል 2

በእውነት ጋዜጣ ቅጽ1 ቁ1 እትማችን በማቴ16፡18 ላይ በመመሥረት በዚሁ ቤተክርስቲያን በተሰኘው ዓምድ ሥር የቤተክርስቲያንን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማንነትና በ፡ተክርስተ፡ያን የተመሠረተችበትን አለት፣ እንደዚሁም ቤተክርስቲያንን የሲኦል ደጆች የማይችሏት ስለመሆኗ በሰፊው ማብራራ ታችን የሚታወስ ነው፤ በዚህ እትምም ከዚያው ከማቴ16፡19 በመነሳት ስለቤተክርስቲያን በዚያ ምዕራፍ የሚገኘውንና በቀዳሚው እትም ያላነሳነውን እውነት እናጠናለን፡፡ የጥናታችን መነሻ የሆነው ምንባብ ሙሉ ሉም እንዲህ ይነበባል፤

**«እኔም እልሃለሁ፤ አንተም ጴጥሮስ/**Πετροσ**-ፔትሮስ/ ነህ፤ በዚችም አለት/**πετρα**-ፔትራ/ ላይ ቤተክርስቲያኔን እሠራለሁ፤ የገሃነም ደጆችም አይችሉአትም፤ የመንግሥተ ሰማያትንም መክፈቻዎች እሰጥሃለሁ፤ በምድር የምታስረው ሁሉ በሰማይ የታሰረ ይሆናል፤ በምድርም የምትፈታው ሁሉ በሰማይ የተፈታ ይሆናል»/ማቴ**16፡18-19/፡፡

በመሆኑም በዚህ እትም «የመንግሥተ ሰማያትንም መክፈቻዎች እሰጥሃለሁ በምድር የምታስረው ሁሉ በሰማይ የታሰረ ይሆናል፤ በምድርም የምትፈታው ሁሉ በሰማይ የተፈታ ይሆናል» ሲል ጌታ ለጴጥሮስ የተናገረውን እንመለከታለን፡፡

### የመንግሥተ ሰማያት መክፈቻዎች

ቤተክርስቲያኑን «ኢየሱስ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ነው» በሚለው እውነት ላይ የሚገነባው ራሱ ጌታ ኢየሱስ ሲሆን ይህችም ቤተክርስቲያን በዚህ ዘመን ቤተክርስቲያን በሚለው ል ላይ የተለያየ ተቀጽላ የያዙ የእምነት ድርጅቶች ወይም ሕንጻዎች ሳትሆን «ሁለት ወይም ሦስት» ወይም ከዚያን በላይ ሆነው ጌታ ኢየሱስን ከማይወደው ዓለም ተለይተው በሌላ ስም ሳይሆን በራሱ በጌታ በኢየሱስ ስም የሚሰባሰቡና እርሱ ቀደም ሲል በምድር ላይ ይዞት የነበረውን ስፍራ ይዘው የሚገኙ የእውነተኛ አማኞች አንድነት እንደሆነች በቀዳሚው እትማችን ተብራርቷል፡፡ ስለሆነም ወደ ዚህች ባሕርይዋ ሰማያዊ መታዘዟም ለጌታዋ ወደ ሆነችው፣ ጌታ ኢየሱስም ራስ ወደሆነላት ወደአንዲቱ የክርስቶስ አካል ሰዎች የሚጨመሩት እንዴት ነው የሚለውን ማጤኑ ከላይ ለጴጥሮስ የተነገረውን ለመረዳት በር ይከፍታል፡፡ በዚህ ረገድም ሰዎች ወደዚያች ህብረት ብልት ሆነው የሚገቡት በመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ሲያብራራ «አይሁድ ብንሆን የግሪክ ሰዎችም ብንሆን ባሪያዎችም ብንሆን ጨዋዎችም ብንሆን እኛ ሁላችን በአንድ መንፈስ አንድ አካል እንድንሆን ተጠምቀናል» ይለናል/1ቆሮ12፡12-13/፡፡ ይሁን እንጂ መንፈስ ቅዱስ ሰዎችን ወደዚህች የክርስቶስ አካል የሚጠራው አስቀድሞ ብልት በሆኑ አማኞች በኩል መሆኑም የማይካድ እውነት ነው፡፡ የእነዚህም ሰዎች አገልግሎት ወይም ምስክርነት እጅግ ጠሚ ከመሆኑም ባሻገር በተሰባኪዎች ዘላለማዊ እጣ ፈንታ ላይ ወሳኟነት አለው፤ ስለዚ ህም ሐዋርያው ሲያስረዳ «የጌታን ስም የሚጠራ ሁሉ ይድናል» ካለ በኋላ «እንግዲህ ያላመኑበትን እንዴት አድርገው ይጠሩታል? ባልሰሙትስ እንዴት ያምናሉ? ያለሰባኪስ እንዴት ያምናሉ?» በማለት የሰባክያን አገልግሎት እንደምን ወሳኟ እንደሆነ ይናገራል /ሮሜ10፡13-14/፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ መሰበኩ ብቻ ተሰባኪውን የዚያች የእውነተኛይቱ ጉባኤ ብልት እንዲሆን የማያደርገው መሆኑም ሌላው እውነታ ነው፤ የተሰበከለት ሰው ስብከቱን አምኖ መቀበሉና አለመቀበሉ ከስብከት ቀጥሎ ጠሚ የሆነ ወሳኟ ነገር ነው፡፡ ተሰባኪው ስብከቱን አምኖ ቢቀበል መንፈስ ቅዱስ ወደዚያች ጉባኤ ብልት አድርጎ ይጨምረዋል፤ የተሰበከለትን ባያምነው ደግሞ አለማመኑ ኃጢአት ይሆንበታል፤ ብልት ሆኖ ወደ ክርስቶስ አካል አይጨመርም፤ «ባለማመናቸው ጠንቅ ሊ ገቡ እንዳልተቻላቸው እናያለን» ተብሎ ስለቀደሙት ሕዝበ እስራኤል እንደተነገረ /ዕብ3፡19/ ያው ወደ ክርስቶስ አካል ብልት ሆኖ እንዲገባ የተጠራበት የምስክርነት ል ሰውን እንዳይገባ ያደርገዋል፤ እንደዚሁም ጌታ «እኔም መጥቼ ባልነገርኋችሁስ ኃጢአት ባልጠ ሆነባቸውም ነበር፤ አሁን ግን ለኃጢ አታቸው ምክንያት የላቸውም» /ዮሐ15፡22/ ሲል እንደተናገረው ነው፡፡ በተጨማሪም ሉ «በእርሱ በሚያምን አይፈረድበትም፤ በማያምን ግን በአንዱ በእግዚአብሔር ልጅ ስም ስላላመነ አሁን ተፈርዶበታል» ይላልና የሰማነውን ል ማመን አሁኑኑ ከፍርድ የዳንን/የተፈታን/ ሰዎች ሲያደርገን አለማመን ደግሞ አሁኑኑ የተፈረደብን/የታሰሩ/ ሰዎች ያደርገናል /ዮሐ3፡18/፡፡

በተጨማሪም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ ወራቱ በጊዜው ለነበሩ ጻፎችና ፈሪሳውያን የተናገረው ሐሳብ ሌላው የተነሣንበትን ምንባብ ለማብራራት የሚያስችለን ሆኖ ይገኛል፤ ጌታችን ለእነዚያ በዘመኑ መጻሕፍትን እናውለን መንፈሳዊነትንም ይዘናል ለሚሉ ነገር ግን የመጻሕፍትን ሐሳብ ለሚያጣምሙ ሕዝቡን ደግሞ «ሕግን የማያውቅ ርጉም ነው»/ዮሐ7፡49/ እያሉ ከእግዚአብሔር እውቀት እንዲገለል አድርገው ለነበሩት ሰዎች «እናንተ ሕግ አዋቂዎች <u>የእውቀትን መክፈቻ</u> ስለወሰዳችሁ ወዮላችሁ፤ ራሳችሁ አልገባችሁም፤ የሚገቡትንም ከለከላችሁ» ሲል ተናገራቸው /ሉ11፡52/፡፡ በተመሳሳይ መልኩ በማቴዎስ ወንጌልም «እናንተ ግብዞች ጻፎችና ፈሪሳውያን መንግሥተ ሰማያትን በሰው ፊት <u>ስለምትዘጉ</u> ወዮላችሁ፤ እናንተም አትገቡም፤ የሚገቡትንም ትከለክላላችሁ» ሲል ተናግሯል/ማቴ23፡13/፡፡

እነዚህ ሰዎች መንግሥተ ሰማያትን የዘጉት እንደምን ነው? ቢባል መልሱ ህጉን ባለማስተማርና በማጣመም ነው የሚል ይሆናል፡፡ ስለሆነም ከላይ የ

(ወደ ገጽ 8 ይዞራል)

> መስበክና ማስተማርም መክፈቻውን ሥራ ላይ ማዋል ነው፤ ምስክርነቱን ሰዎች ሳይቀበሉ ሲቀሩ የተፈረደባቸው ወይም የተዘጋባቸውና የታሰሩ ይሆናሉ፤ ምስክርነቱን ሲቀበሉ ወደ መንግሥተ ሰማያት ለመግባት ከፍርድ የዳኑና የተፈቱ ይሆናሉ፤ በዚህ መንገድ ሰባኪው ቁልፉን ይጠቀማል፤ ማለትም ያስራል፤ ይፈታል፡፡ ለጴጥሮስም የተባለው ይኸው ነው፡፡

## ከዮናስ የሚበልጥ..ከገጽ 4 የዞረ

ሦስት ሌሊት ለመኖር የተገባው ጌታ ኢየሱስ እንደሞተ አልቀረም፤ ነገር ግን ሞትና መውጊያውን ሰብሮ፣ በሞት ላይ ሥልጣን ያለውን ዲያብሎስን በሞቱ ሽሮ በኃይልና በሥልጣን ሕያው ሆኖ ተነሥቷል:: ስለሆነም ጌታ በዚህ ክፍል «ከነቢዩ ከዮናስ ምልክት በቀር ሌላ ምልክት አይሰጠውም» ብሎ ከተናገረ በኋላ በራሱ ላይ የሚሆነውን ይህንን በምድር ልብ ውስጥ ሦስት ቀን ሦስት ሌሊት የመኖሩን ምልክት መናገሩ ለክፉና ለአመንዝራ ትውልድ ከዚህ የጌታ ኢየሱስ የሞቱ እና የትንሣኤው ምልክት በቀር ሌላ ምልክት እንደማይሰጠው ያስረዳል::

ከዚህ ታሪክ ቀደም ብሎ ጌታ ኢየሱስ ገና የምልክቶች መጀመሪያ እያደረገ በነበረ ጊዜ ስለምልክቶች ተጠይቆ የሰጠው መልስም ይህንኑ ዓይነት መልስ ነበር:: ይህም የመጀመሪያውን የቤተመቅደስ የማጽዳት ሥራ በሠራበት ጊዜ ነበር፤ በቤተመቅደስ ውስጥ የነበሩትን በጎችና በሬዎችን በጅራፍ ካስወጣ በኋላ የገንዘብ ለዋጮችን ገንዘብ ሲያፈስ ገበታዎችንም ሲገለብጥ፣ ርግቦቹንም ከዚህ ውሰዱ ሲልና *<u>የአባቴን ቤት</u>* የንግድ ቤት አታድርጉት ብሎ ሲናገር የሚያደርገውና የሚናገረው ሁሉ በሥልጣን እንደነበረ ያዩት አይሁድ «ይህን ስለምታደርግ ምን ምልክት ታሳየናለህ?» ብለው ጠይቀውት ነበር:: ኢየሱስም የሰጠው መልስ ሲያደርጋቸው ከነበሩት ተአምራት /ምልክቶች/ አንዱን በመጥቀስ አልነጠበረም፤ ነገር ግን «ይህን ቤተመቅደስ አፍርሱት በሦስተኛውም ቀን አነሣዋለሁ» የሚል አስደናቂ መልስ ሰጣቸው:: አይሁድ በፊደላዊ መንገድ በማሰብ «አፍርሱት» ያላቸው ቤተመቅደስ በጊዜው የነበረው የቤተመቅደስ ሕንፃ መስሏቸው ነበር:: ይሁን እንጂ ጌታ ኢየሱስ ስለ ሰውነቱ «ቤተመቅደስ» ይል ነበር /ዮሐ2፡21/:: በሦስት ቀን አነሣዋለሁ ማለቱም ሞቶ በሦስተኛው ቀን እንደሚነሣ የሚያረጋግጥ ቃል ነበር /ቁ.22/::

ስለዚህ በዘመናት ሁሉ ምልክት ለሚፈልጉ ሰዎች ጌታ ኢየሱስ የሰጠው ምልክት ሞቱና ትንሣኤውን ነው:: በ4ቱ ወንጌላትና በመላው የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ሁሉ በግልጽ የተመዘገበውን የኢየሱስን የሞቱንና የትንሣኤውን ምልክት እያነበቡና ዘወትር ሲነገር እየሰሙ ነገር ግን ለሚያምኑት ነገር ምልክት ፍለጋ በየስፍራው የሚቅበዘበዙ ወገኖች ይህንን እውነት በእርጋታና በማስተዋል ሆነው ሊመለከቱት ይገባል:: ለቶማስ የተነገረው ቃልም እንደዚሁ እንዲህ ላሉ ሰዎች ተጨማሪ መረጃ ሆኖ ሊረዳቸው ይችላል፤ ቶማስ ጌታ ኢየሱስ ከሙታን ከተነሣ በኋላ ለሐዋርያት ራሱን በገለጠበት በመጀመሪያው ቀን በሐዋርያት መካከል አልነበረም፤ ከስምንት ቀን በኋላ ግን ቶማስን ጨምሮ ሁሉም ሀዋርያት በዝግ ቤት ውስጥ ሳሉ ጌታ ኢየሱስ በድጋሚ ተገልጦ ለቶማስ ራሱን አሳየውና «ያመንክ እንጂ ያላመንክ አትሁን» ሲለው ቶማስ «ጌታዬ አምላኬም» ብሎ አመነ:: ከዚህ በኋላ ኢየሱስ ለሁላችንም የሚሆን ወሳኝና ጠሚ ቃል ተናገረው፤ ይህም ቃል «ስለ አየኸኝ አምነሃል፤ ሳያዩ የሚያምኑ ብፁዓን ናቸው» የሚል ቃል ነው /ዮሐ20፡26-29/::

እግዚአብሔር እርሱ ራሱ እንደፈቀደ በምልክትና በድንቅ ነገር በልዩ ልዩ ተአምራትም መንፈስ ቅዱስንም በማደል አብሮ የመሰከረለት /ዕብ2፡4/ የጸና ቃል በዚህ ዘመን ለምንገኛ ሰዎችም ደርሷል፤ በመሆኑም ካላየሁ አላምንም በሚል የአለማመን ዝንባሌ እየተነሣሣን የእግዚአብሔርን ቃል የሚያጸኑልን

ስለዚህ በዘመናት ሁሉ ምልክት ለሚፈልጉ ሰዎች ጌታ ኢየሱስ የሰጠው ምልክት ሞቱና ትንሣኤውን ነው::

ምልክቶች ፍለጋ ልንጠማና ወዲያ ወዲህ ልንል አይገባም፤ በሰው ፍላጎትም ላይ ተመሥርቶ የሚደረግ ምንም የጌታ ምልክት የለም፤ በፊትም ቢሆን ጌታ ምልክትን ያደርግ የነበረው እርሱ ራሱ እንደፈቀደ ነበር እንጂ/ዕብ2፡4/ ሰዎች ለፈውስና ለሌሎች ምልክቶች ቀን ወስነው ፕሮግራም እያወጡለት አልነበረም:: ስለሆነም እግዚአብሔር በልጁም ሆነ በሐዋርያት እጅ ያደረጋቸው ምልክቶች የጸናውን ቃል ለእኛ ትተውልን አልፈዋልና ምልክቶችን ለማየት ወዲያና ወዲህ ከመንከራተት ይልቅ በጸናው ቃል ላይ ማረፍና መመካት ተገቢ ነው፤ ጴጥሮስ የእርሱን ግርማ አይተው ከሰማይ የመጣውን ድምፅ በቅዱስ ተራራ ሰምተው የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ኃይልና መምጣት እንዳስታወቁ ከገለጠ በኋላ «ከእርሱም ይልቅ እጅግ የጸና የትንቢት ቃል አለን» ይላል /2ጴጥ1፡19/:: ይህም የጸናው የትንቢት ቃል ቅዱሳን ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው የተናገሩት ቃል ነው/ቁ.20-21/:: ስለሆነም ምንም እንኳን ያየው የተራራው ምልክት እጅግ የከበረ ቢሆንም ሉ ከማናቸውም መንፈሳዊ ምልክት የሚበልጥ በመሆኑ ጴጥሮስ «ከእርሱም ይልቅ እጅግ የጸና የትንቢት ቃል አለን» ማለት ተገብቶታል:: በመሆኑም ከጸናው የእግዚአብሔር ቃል ይልቅ ዛሬ ሰዎች እግዚአብሔር እንዲህ ብሎኛል እንዲያ ተናግሮኛል በሚሉት ከመወሰድ ልንጠነቀቅ ይገባል:: የጸና የእግዚአብሔር ቃልም በተሟላ ሁኔታ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተመዝግቦልን ስላለ እርሱን የጸናውን የትንቢት ቃል እንደገዛ ፈቃችን ሳይሆን እንደመንፈስ ፈድ በመካከላችን እየገለጥን ምክሩን ማወቅና ማመን ተገቢ ነው:: በዚህ ፈንታ ግን ተአምራዊ በሆነ መንገድ የሚመጣ አዲስ የትንቢት ቃልና ምልክት ፍለጋ መንከራተት የቀደመውን የጸና ቃል መናቅ ከመሆኑም ባሻገር ካላየሁ በቀር የተጻፈልቛን አላምንም የማለት ያህል ተጠራጣሪነት ነው:: ስለሆነም ምልክት ፍለጋ ወዲያና ወዲህ የሚንከራተቱ ሰዎች በጌታ በኢየሱስ ሞትና ትንሣኤ ላይ በማረፍ ሀዋርያው ጴጥሮስ «እርሱንም ሳታዩት ትወዱታላችሁ፤ አሁንም ምንም ባታዩት በእርሱ አምናችሁ የእምነታችሁን ፍጻሜ እርሱም የነፍሳችሁን መዳን እየጠ ተቀበላችሁ በማይነገርና ክብር በሞላበት ሐሤት ደስ ይሳችኂል»/1ጴጥ1፡8-9/

## ክርስቲያን.... ከገጽ 15 የዞረ

**ክርስቲያን**

- ♥ ***በአእምሮው*** *ክርስቶስን የሚያስብ*
- ♥ ***ልቡን*** *የክርስቶስ መኖሪያ ያደረገ*
- ♥ ***በድምጹ*** *ክርስቶስ የሚናገርበት*
- ♥ ***በእጆቹ*** *ክርስቶስ የሚራዳበት*

**ሰው ማለት ነው፡**

### *አምስቱ መጠሪያዎቻችን*

♣ **<u>ክርስቲያን</u>**፣
ክርስቶስን ስለምንከተልና የክርስቶስ ስለሆንን /የሐ.ሥ.11፡26/

♣ **<u>ቅዱሳን</u>**፣
በክርስቶስ ደም ተቀድሰን ሥጋንና መንፈስን ከሚያረክስ ነገር ስለተለየን /1ቆሮ.1፡1፤ 2ቆሮ.7፡1፤ ፊልጵ1፡1/

♣ **<u>ወንድሞች</u>**፣
የአንድ አባት የእግዚአብሔር ልጆች ስለሆንንና ስለምንዋደድ /ማቴ.23፡8፣ የሐ.ሥ.9፡30፣ 15፡1፡36፤ ሮሜ8፡29/

♣ **<u>ምእመናን/አማኞች/</u>**፣
በእግዚአብሔር ልጅ በጌታኢየሱስ ብቸኛ አዳኛነት ስለምናምን /ሐ.ሥ.10፡45፣ራእ17፡14/

♣ **<u>ደቀመዛሙርት</u>**፣
የክርስቶስ ተማሪዎችና ቋሚ ተከታዮች በመሆናችን /ዮሐ.8፡31፣ የሐ.ሥ.6፡7፣ 9፡19፣ 21፡16::/

...በፍጹም ልብህ በፍጹምም ነፍስህ ታመልከው ዘንድ ...ነው እንጂ አምላክህ እግዚአብሔር ከአንተ የሚልፈገው ምንድር ነው?



# አምልኮ

**እኛ በመንፈስ እግዚአብሔርን የምናመልክ በክርስቶስ ኢየሱስም የምንመካ በሥጋም የማንታመን . . . ነንና /ፊልጵ.3:3/**

## በዚህ ተራራ ወይም በኢየሩሳሌም ለአብ የማትሰግዱበት ጊዜ ይመጣል/ዮሐ.4:21/::

በርእሱ የተመለከተውን ል ለአንዲት የሰማርያ ሴት በያዕቆብ ጉድጓድ አጠገብ የነገራት የእግዚ አብሔር ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ ነበር፤ ታሪኩ የሚጀምረው «ውኃ አጠጪኝ» በሚል የልመና ል ነበር፤ ምን አልባትም ይህ ገጠመኝ ለሴቲቱ የመጀመሪያዋ ሳይሆን አይቀርም፤ በባህል፣ በታሪክና በሃይማኖት የማይመስላት አንድ ከአይሁድ ወገን የሆነ እጅግ በጣም ትሁት ሰው ውኃ አጠጪኝ ብሎ ሲጠይቅ በጣም እንደተደነቀች ማሰብ ይቻላል:: በታሪካቸው አይሁድ ከሳምራዊያን ጋር በምንም ነገር አይተባበሩም ነበርና በእርግጥም ጥያቄው ያስደንቃል፤ የሴቲቱም መልስ «አንተ የይሁዳ ሰው ስትሆን ሳምራዊት ሴት ከምሆን ከእኔ መጠጥ እንዴት ትለምናለህ? የሚል ነበር፤ እርግጥ ነው አይሁድ ሳምራውያንን ሲጸየፏቸው ሳምራውያን ግን ለአይሁድ የእነርሱን ያህል ጥላቻ አልነበራቸውም ነበር/ሉ.10:30-35 በዚህ ጥቅስ ላይ የደጉ ሳምራዊ ታሪክን ያስታውሷል/:: ይህ የጌታ ጥያቄ በሁለቱ መካከል ያለውን ልዩነት የሚያስወግድ፣ የአጠ ይሁድን ትምክህት ባዶ የሚያደርግ በፍጻሜው ደግሞ የሰማርያ ሰዎችን ከይሁዳ ወገን ከሆነው ከኢየሱስ ጋር እንዲተባበሩና እንዲመሰክሩለትም የሚያደርግ ነበር /ዮሐ4:39-42/::

ይህ በጌታና በሳምራዊቱ ሴት መካከል የተደረገው ውይይት ልብን ለአዲስና ታላቅ ጥቅምን ሊ ያስገኛ ለሚችል አዲስ ሕይወት የሚያዘጋጅ የጾጋ ውይይት ነበር:: ጌታ ኢየሱስ ከያዕቆብ ጉድጓድ የሚመነጭን ውኃ ምክንያት ያደረገ ጥያቄ ለሴቲቱ አቅርቦ ለእርሷና ለወገኖቿ ከእግዚአብሔር መቅደስ የሚፈሰውን፣ አንድ ጊዜ ከተጠጣ ለዘላለም የማያስጠ ማውን፣ ከእርሱ የጠጡትን ሁሉ ደግሞ ለዘላለም ሕይወት የሚፈልቅ የውኃ ምንጭ የሚያደርገውን የሕ ይወት ውሃ እንድትጠይቀው አነሳሳት /ዮሐ4:15/::

በውይይቱ መጨረሻ ላይ ሴቲቱ የራሷን ትታ ከእርሱ ብቻ የሚገኘውን የሕይወት ውኃ በመሻት «ውኃ አጠጪኝ» ብሎ የለመናትን ጌታ መለመን ጀመረች፤ «ጌታ ሆይ እንዳልጠማ ውኃም ልቀዳ ወደዚህ እንዳልመጣ ይህን ውኃ ስጠኝ» አለችው/ቁ.15/፤ የጌታ መልስ ግን ለየት ያለ ነበር፤ «ሂጂና ባልሽን ጠርተሽ ነይ» የሚል:: ይህ ደግሞ ለሴቲቱ ሌላው አስደናቂ ነገር ነው:: «ይህ ሰው ማነው? የቤቴን ምስጢር አንድም ሳይቀር የሚያውቅ ይህ ማነው?» ብላ እንድታስብና ነቢይ መሆኑን እንድትገምት አስችሏታል ብንል ከእውነታው የተለየ አይደለም፤ ምክንያቱም «አንተ ነቢይ እንደ ሆንህ አያለሁ» ብላ ስለእርሱ ማንነት በልቧ የታሰባትን ተናግራለችና፤ እንደዚህ ካለው ሰው ጋር ዋና ዋና በሆኑ አርእስት የእግዚአብሔርን ነገር መወያየት በውስጥ ለተሰወረ የልብ ጥያቄ መልስ ያስገኛል:: ከዚህ የተነሣ ይመስላል ይህች ሳምራዊት ሴት ስለ አምልኮ ስፍራ በልቧ ይመላለስ የነበረውን ርእስ ያነሣችለት፤ እንዲህ በማለት:- «አባቶቻችን በዚህ ተራራ ሰገዱ እናንተም ሰው ሊሰግድበት የሚገባው ስፍራ በኢየሩሳሌም ነው ትላላችሁ» /ቁ.19-20/::

ጌታ ኢየሱስም:- «አንቺ ሴት እመኚኝ በዚህ ተራራ ወይም በኢ የሩሳሌም ለአብ የማትሰግዱበት ጊዜ ይመጣል» አላት /ዮሐ.4:21/::

እስኪ እዚህ ላይ ቆም ብለን ስግደት ማለት ምን ማለት እንደሆነና መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ስግደት የሚገል ጠው እውነት ምን እንደሆነ እናጥና፤

«**ስግደት**» የሚለው ል «መገዛት» የሚለውን ትርጉም ይሰ ጠናል:: «ስግዱ ለእግዚአብሔር በፍርሃት» ቢል «ለእግዚአብሔር በፍርሃት ተገዙ» ማለት ነው ፤ ይህም በመላ ሕይወታችን ለእግዚአብሔር መገዛት ነው እንጂ የልብ መታዘዝ ሳይኖረንና ፈሪሃ እግዚአብሔር በልብ ሳይሰማን ይህን ያህል ጊዜ ሰግጄ ነበር ለማለት ቁጥር እየቆጠሩ በሥጋ አካል እየወደቁ መነሳት ማለት አይደለም:: አምልኮ ማለትም መገዛት ማለት በመሆኑ ስግደትና አምልኮ የሚሉት ሳት ተመሳሳይ ትርጉም ይኖራቸዋል:: በሌላ አባባል ስግደት ስንል ስለ አምልኮ መናገራችን ነው::

ከዚህ በመነሣት ጠቅለል ያለውን የስግደትን /የአምልኮን/ መሠረታዊ ይዘት ከርእሱ ጋር በሚጣጣም መልኩ መተንተን ተገቢ ነው::

አምልኮ እግዚአብሔርን በእግዚ አ ብሔርነቱ ለእርሱ የሚገባውን ክብር መስጠትና እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ያደረገውን ታላቅ ነገር እያስታወሱ በሕይወት ዘመን ሁሉ ለእርሱ መገዛት እንዲሁም በጸሎት፣ በምሥጋና በዝማሬ እርሱን ከፍ ከፍ ማድረግ ነው:: በዕብራ ይስጥ ቋንቋ ብዙውን ጊዜ ለአምልኮ የሚያገለግለው ል ስግደት የሚል ፍቺ ያለው ል ነው:: ለምሳሌ በዘፍ18:2 እግዚአብሔር ለአብርሃም ሲገለጥለት አብርሃም እንደ ሰገደ የተጻፈውም በዚሁ መሠረት ነው::

ማስተዋል ለተሰጠው ማንኛውም ሰው እግዚአብሔርን ማምለክ እንደሚገባው ግልጥ ነው፤ መላእክት እግዚአብሔርን ያመልኩታል /ነህ9:6/:: ቅዱሳን ሰዎችም ያመልኩታል፤ በዘላለም ወንጌል የተጠሩ ሰዎች ሁሉ እግዚአብሐ ርን ሊፈሩና ሊያከብሩ ይገባቸዋል፤ በመጨረሻም በምድር ያለው ሁሉም ፍጥረት እግዚአብሔርን ያመልካል /ሶፎ2:11/::

መላእክት እግዚአብሔርንና ማንነቱን በማወቅ በእውነት ያመልኩታል፤ ሰዎች ደግሞ ጌታችን ኢ የሱስ ክርስቶስን በማመን ዳግመኛ ተወልደው የተሟላ ህይወትን ሲቀበሉ እግዚአብሔርን ማምለክ ይጀምራሉ:: ዳግመኛ ያልተወለዱ ሰዎችም ቢሆኑ የቍጣውን ኃይል ሲቀምሱ እግዚአብሐ ርን ሊያመልኩ ይችላሉ:: ይሁን እንጂ እግዚአብሔር ከዚህ ከፍርሃት ከመነጨ ውጫዊ አምልኮ የሚበልጥ አምልኮን ከሰው ይጠብቃል:: ይኸውም ሰው ለእግዚአብሔር ካለው የፍቅር ስሜት የመነጨ ክብርን ለእግዚአብሔር በመስጠት የሚያቀርበው አምልኮ ነው:: በሉም አማካይነት ስለዚህ አምልኮ ጠ ባይና ኃይል እንደዚሁም አምልኮው ስለሚካሄድበት እውነተኛ ስፍራ ተነግሮናል::

## እውነተኛው የአምልኮ ስፍራ

በብሉይ ዘመን ቤተ እስራኤል በጉባዔ እግዚአብሔርን ማምለክ የጀመሩት ከግብፅ አገር የፈርኦን አገዛዝ ነፃ ከወጡ በኋላ ነበር:: በባዕድ አገር ጣዖት በሚመለክበትና ነፃነት በሌለበት ሁኔታ ቤተ እስራኤል እግዚአብሔርን በነፃነት ማምለክ ቀርቶ ለማምለክም

*ወደ ገጽ 9 ይዞራል*

## ቤተክርስቲያን.. ..ከገጽ 5 የዞረ

ጠቀስናቸው ሁለት ሐሳቦች የመንግሥተ ሰማያት መክፈቻ ወይም ቁልፍ እግዚአብሔር ኃጥአንን ወደራሱ የሚጠራበት በሰዎች ያልተጣመመ ትክክለኛ የሉ ምስክርነት እንደሆነ ያሳዩናል:: ይህንን ምስክርነት ሰጥቶ ሰዎችን ወደ እግዚአብሔር የመጥራትን ጥሪ መቀበልም መክፈቻውን መቀበል ነው፣ መስበክና ማስተማርም መክፈቻውን ሥራ ላይ ማዋል ነው፤ ምስክርነቱን ሰዎች ሳይቀበሉ ሲቀሩ የተፈረደባቸው ወይም የተዘጋባቸውና የታሰሩ ይሆናሉ፤ ምስክርነቱን ሲቀበሉ ወደ መንግሥተ ሰማያት ለመግባት ከፍርድ የዳኑና የተፈቱ ይሆናሉ፤ በዚህ መንገድ ሰባኪው ቁልፉን ይጠቀማል፤ ማለትም ያስራል፤ ይፈታል:: ለጴጥሮስም የተባለው ይኸው ነው::

### መታሰርና መፈታት

የተሰባኪዎች መታሰርና መፈታት የሰባክያን ቀጥተኛ ውጤት ሳይሆን መክፈቻ የሆነው የእግዚአብሔር ል በሰሚዎች ላይ የሚያመጣው ውጤት ነው:: ሰዎቹን ማሰርና መፍታት የጴጥሮስ ቀጥተኛ ድርሻ አይደለም፤ ከጴጥሮስ የሚጠበቀው የተሰጠውን የወንጌል ሰባኪነት ጸጋ ሥራ ላይ ማዋል ነው፤ ልብ እንበል፤ ይህ ሰዎችን «ተፈቱ» ወይም «ታሰሩ» ብሎ በአፍ ከመናገር ወይም ፈድን ከመግለጥ ወይም ከማወጅ በእጅጉ የተለየ ነው:: የሰዎች መፈታትም ሆነ መታሰር የመክፈቻው ውጤት እንጂ የጴጥሮስ ፈድ ወይም ፍላጎት አይደለም፤ የመንግሥተ ሰማያት መክፈቻ የሆነው የእግዚአብሔር ል በሰው ልብ ላይ እንዲሠራ ሲደረግ ውጤት አለው፤ ውጤቱም አንዳንዶችን ለእምነት ማብቃቱ ሲሆን አንዳንዶችን ደግሞ በእልከኛነታቸው ምክንያት በክህደት እንዲገለጡ ማድረጉ ነው፤ አንዱ እሳት ሰሙን ሲያቀልጥ ሸክላውን ደግሞ ከፊት ይልቅ ጠንካራ ያደርገዋል፤ የእግዚአ ብሔር ልም በሰዎች ላይ ተመሳሳይ ውጤት ያስከትላል::

ስለሆነም ጴጥሮስ በተሰጠው መክፈቻ ማለትም በወንጌል ል ሰዎችን ወደ እግዚአብሔር መንግሥት እንዲገቡ ለማድረግ ሲሰብክና ሰዎች አምነው በመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ወደ ክርስቶስ አካል ሲገቡ መክፈቻውን ተጠቅሞ በምድር እየፈታ ነበር፤ ሰዎች ምስክርነቱን አንቀበልም ሲሉ ደግሞ «ባለማመናቸው ጠንቅ» ወይም «ሉ ከሰሚዎቹ ጋር በእምነት ስላልተዋሐደ»/ዕብ.4:2/ ወደ መንግሥተ ሰማያት እንዳይገቡ ሆነዋልና በምድር የታሰሩ መሆናቸውን እየገለጠ ነበር:: ለምሳሌ

> **አንዱ እሳት ሰሙን ሲያቀልጥ ሸክላውን ደግሞ ከፊት ይልቅ ጠንካራ ያደርገዋል፤ የእግዚአብሔር ልም በሰዎች ላይ ተመሳሳይ ውጤት ያስከትላል::**

ያህልም በበዓለ ሃምሳ ዕለት ጴጥሮስ ሲሰብክ ሦስት ሺህ ያህል ነፍሳት ወደ ቤተክርስቲያን አምነው ሲጨመሩ /ሲፈቱ/ እንመለከታለን፤ እንደዚሁም በሌላ ወቅት ጴጥሮስ የሰበከውን ል አምነው ብዙዎች ወደ ሐዋርያት ሲጨመሩ /ሲፈቱ/ በስብከቱ ደስ ያልተሰኙ ሌሎች ደግሞ በሐዋርያት ላይ «እጃቸውን ጭነውባቸው» ወደ ክርስቶስ ጉባኤ ሳይገቡ እንደቀሩ /እንደታሰሩ/ እናነባለን/ሐዋ.ሥ4:3-4/::

ስለሆነም የቁልፉን ያዥ ድርሻና የቁልፉን ውጤት መለየት ይኖርብናል:: ቍልፉን በሥራ ላይ ማዋል ማለትም ሉን መስበክ ነው፤ ሉን መስበክ የጴጥሮስ ድርሻ ነው፤ የሰዎች መታሰርና መፈታት መክፈቻው በሰዎቹ ምላሽ ላይ ተመርኩዞ የሚያመጣው ውጤት ነው::

### ሰማይና ምድር

በመቀጠል ደግሞ «በምድር የምታስረው ሁሉ በሰማይ የታሠረ ይሆናል፤ በምድር የምትፈታው ሁሉ በሰማይ የተፈታ ይሆናል» በሚለው አባባል ውስጥ ያለውን የሰማይና የምድር ግንኙነት እንመለከታለን:: ይህም ማለት ጴጥሮስ ወንጌሉን እንደመለኮት ፈድ ከሰበከ ያለጥርጥር ተሰባኪው ለወንጌሉ የሚሰጠው ምላሽ በሰማይ እውቅናና ክትትል አለው ማለት ነው:: ይህም ምድር ላይ እንደ ሰማይ ፈድ ለተሠራው ሥራ ሁሉ ሰማያዊ ክትትል፣ እውቅናና ድጋፍ እንዳለ የሚያመለክት ነው:: ስለዚህ አገልጋዩ የሚያገለግለው ብቻውን ሳይሆን መለኮታዊ መገኘትና ክትትል ባለበት ሁኔታ ውስጥ ነው ማለት ነው:: ሰዎች የሰባኪውን ል አምነው ሲቀበሉ መቀበላቸው በእግዚአብሔር ዘንድ ወዲያውኑ የታወቀ ሲሆን አለመቀበላቸውም ወዲያውኑ በእግዚአብሔር ፊት ለፍርድ የተዘጋጁና የተፈረደባቸው ከእግዚአብሔር መንግሥትም የተገለሉ እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል:: ስለዚህ ሰዎች በምድር ላይ ለሚሰሙት የወንጌል ል የሚሰጡት ምላሽ በእጅጉ ዘላለማዊ ማንነታቸውን የሚወስን ነው ማለት ነው:: ከዚህም ሌላ ሰዎች በምድር ላይ በወንጌል ስብከት አምነው ወደ ክርስቶስ አካል ካልተጨመሩ በቀር ዛሬም ሆነ ወደፊት በሰማይ ላይም ያልተጨመሩ ሆነው እንደሚቀሩ የሚያሳይና እንደዚሁም እንደፈዱ አሠራር የሚሰጠውን ምስክርነት አምነው ወደ ክርስቶስ አካል የተጨመሩት ደግሞ መጨመራቸው በሰማይም ጭምር የተረጋገጠና ይህ መብታቸውና ያገኙትም ስፍራ ሰማያዊ እውቅናና ድጋፍ ያለው መሆኑን ከዚህ ምንባብ መረዳት እንችላለን:: በምድር ሳሉ ሉን ያላመኑትና የካዱት ሁሉ በሰማይም የካዱ ሆነው ይታወሉ፤ ከሞቱ በኋላ ወደ ክርስቶስ አካል መጨመርም አይችሉም፤ ሰው ነፍሱ ከሥጋው በምትለይበት ወቅት የነበረው ማንነቱን ሰማይ ላይ ሊቀይር ወይም ሊያሻሽል

*(ወደ ገጽ 11 ይዞራል)*

## ከተመሠረተው.. .ከገጽ 1 የዞረ

እኔ ግን የኬፋ ነኝ፣ እኔስ የክርስቶስ ነኝ ትላላችሁ:: ክርስቶስ ተከፍሏልን? ጳውሎስስ ስለእናንተ ተሰቀለን? ወይስ በጳውሎስ ስም ተጠመቻችሁን?» ብሏቸዋል/1ቆሮ1:12-13/:: እንግዲህ ይህ በቆሮንቶስ ማህበረ ምእመናን መካከል የተፈጠረው መለያየት እጅግ አደገኛና የክርስቶስን ምስክርነት የሚያበላሽ ሆኖ በመገኘቱ የእግዚአብሔር መንፈስ በባሪያው በጳውሎስ በኩል ምላሽ ሲሰጥበት ይታያል:: በአንዱ በክርስቶስ እንደዳኑ የተመሰከረላቸው ሰዎች ክርስቶስን ትተው ስለእርሱ በመሰከሩላቸው አገልጋዮች ስም ሲከፋፈሉ ይህ የጌታን ክብር በእጅጉ የሚያልል ነው:: ክርስቶስ አስቀድሞም አልተጠ ከፈለም፤ በባሕርዩም መከፈል የለበትም፤ በሉም መለያየት የለበትም፤ አካሉ የምትሆን ቤተክርስቲያኑም እንዳትከፈል በመፈለጉ «አንተ እንደላክኸኝ ዓለም ያምን ዘንድ አባት ሆይ በእኔ እንዳለህ እኔም በአንተ እነርሱ ደግሞ በእኛ **አንድ ይሆኑ** ዘንድ እለምናለሁ» በማለት ስለአካሉ አንድነት ጸሎት አቅርቦ ነበር /ዮሐ17:20-23/:: ሆኖም ግን እስራኤል ከግብጽ ተጠ ርቶ ኋላ ግን ራሱ ከባርነት ነጻ ካወጣው አምላኩ በማፈግፈጉ ከገባባት ርስት ተነቅሎና ወደባቢሎን ተወስዶ ለግዞት እንደተዳረገ ሁሉ አሕዛብም በእግዚአብሔር ርኅራኄ ከተጠሩበት የመንፈስ ኑሮ ወደ ሥጋዊነት ፈቀቅ ብለው ከጸጋው እየወደቁ ስናይ ሰው ምንኛ አሳዛኝ ፍጡር ነው ብለን ለማሰብ እንገደዳለን:: የእግዚአብሔር መንፈስ ጣል ባይገባ ኖሮ በቆሮንቶስ አንዲቱ የክርስቶስ አካል ለአራት ትከፈል ነበር:: በሌላ አባባል ይህንን የጠላት ደባ እግዚአብሔር ባያከሽፈው ኖሮ አንዲቱ ጉባኤ ለአራት ተከፍላ ምናልባትም ከፊሎቹ ኬፋን መሠረት ያደረገ «የቅዱስ ጴጥሮስ ቤተክርስቲያን»፣ ሌሎች ደግሞ አጵሎስን መሠረት በማድረግ «የቅዱስ አጵሎስ ቤተክርስቲያን» ሦስተኛው ቡድን ደግሞ ጳውሎስን መሠረት ያደረገ «የቅዱስ ጳውሎስ ቤተክርስቲያን»፣ የተቀሩት ደግሞ መለያየቱን መሠረት

*(ወደ ገጽ 9 ይዞራል)*

## በዚህ ተራራ..... .ከገጽ 7 የዞረ

የሚያስቡበት መንፈስም ሆነ ምቹ ጊዜ አልነበራቸውም:: ከፈርዖን አገዛዝ ነፃ ወጥተው ባሕረ ኤርትራን በተሻገሩና የፈርዖንን መጨረሻ በተመለከቱ ጊዜ ግን በነፃነትና በድል መንፈስ ፍጹም ሀሴትን ተሞልተው በአንድ ልብ በመሆን የከንፈራ ቸውን ፍሬ ለእግዚአብሔር እንዳቀረቡ ይህም በሕይወታቸው ለመጀመሪያ ጊዜ ለባለውለታቸው ለእግዚአብሔር በዜማ ያቀረቡት መሥዋዕት እንደ ነበር ቅዱስ መጽሐፍ ይነግረናል/ዘጸ15:1-21/:: እስራኤል በምድረ በዳ ጉዟቸው በሲና ተራራ ህግን በሙሴ እጅ ከእግዚአብሔር ከተቀበሉ በኋላ ግን የአምልኮ ሥፍራና ጊዜ፣ ለአምልኮ የሚያገለግሉ ንዋያተ ቅድሳት፣ በአምልኮ ወቅት የሚቀርቡ መባዎችና መሥዋዕቶች ምን መሆንና መምሰል እንዳለባቸው እንዲሁም አምልኮውን የሚመሩ አገልጋዮች እነማን መሆን እንዳለባቸው ለሙሴ መመሪያ ተሰጥቶት ነበር:: ለሙሴ ከተሰጠው ትእዛዝ አንዲቱ ብትጐድል ወይም አንዲት የሰው ሐሳብ ብትጨመር የእግዚአብሔር ቁጣ በአገልጋዮቹም ሆነ በጉባዔው ላይ ትነድ ነበር::

በኢየሩሳሌም የነበረው ታላቁ የሰጠ ሎሞን ቤተ መቅደስ ከመሠራቱ በፊትም በእስራኤል ማኅበር መካከል ልዩ በሆነ ትእዛዝ የተሠራው የመገናኛው ድንኳን /ደብተራ ኦሪት/ ነበር:: በዚህ ድንኳን ውስጥም የተሟላ የአምልኮ ሥነ-ሥርዓት ይከናወን ነበር:: እግዚአብሔርም በዚያው ድንኳን ውስጥ የሚቀርበውን መሥዋዕት መቀበሉን ለመግለጥ በመገናኛው ድንኳን በክብር ደመና በመገለጥም የአምልኮውን መሪዎች ያነጋግራቸው ነበር /ዘጸ40:34-38፣ ዘሌ1:1/::

በዚሁ መሠረት እግዚአብሔር ራሱ የአምልኮውን ጠባይና አምልኮው የሚከናወንበት ተንቀሳቃሽ ድንኳን እንዲሠራ ለሙሴ አዝዞት አምልኮው በምድር በዳ ሲከናወን ቆይቷል:: ወደሚወርሷት አገር ሲገቡም አምልኮው ስለሚከናወንበት ስፍራ እግዚአብሔር ሲናገር «በዚያን ጊዜ አምላካችሁ እግዚአብሔር ስሙ ይ ጠራበት ዘንድ ወደዚያ ወደ መረ ጠው ስፍራ እኔ የማዛችሁን ሁሉ የሚጠለውን መሥዋዕታችሁን ሌላ መሥዋዕታችሁንም አሥራታችሁንም በእጃችሁ ያነሣችሁትንም ቁርባን ለእግዚአብሐር ተስላችሁ የመረጣችህትን ስለታችሁን ውሰዱ» /ዘዳ12:11/ብሏቸዋል:: ይህም ስፍራ ከሌሎች ስፍራዎች የሚለየው በእግዚ አብሔር በመመረጡና እግዚአብሔር ስሙን በዚያ ስላኖረ ነው:: ያም ስፍራ ኢየሩሳሌም እንደነበር በኋላ ዘመናት ተገልጦአል/መዝ132:13/::

ከዚያ ሥፍራ ውጪ ቤተእስራኤል የተሟላ የአምልኮ ሥነ-ሥርዓት የማይፈጽሙ ሲሆን ይህም ለዘመናት ሲከናወን የኖረ የእግዚ አብሔር ሥርዓት ነበር::

የሰማርያይቱም ሴት «አባቶቻችን በዚህ ተራራ ሰገዱ፣ እናንተም ሰው ሊሰግድበት የሚገባው ስፍራ በኢየሩሳሌም ነው ትላላችሁ» ያለችበት ምክንያትም ይኸው የአይሁድ ሃይማኖታዊ ልማድ ነበር:: ጌታ ኢየሱስ ግን ሁኔታው መቀየሩን ለሴቲቱ ያበሰራት «አንቺ ሴት እመኚኝ በዚህ ተራራ ወይም በኢየሩሳሌም ለአብ የማትሰግዱበት ጊዜ ይመጣል» በማለት ነበር:: ይህ ል አዲስ የሆነ የአምልኮ ሥፍራ ከእግዚአብሔር ዘንድ እንደተዘጋጀ በእርግጠኛነት የሚያመለክት ሲ ሆን ይህም የሰማርያ ሰዎችን እለት እለት ወደ ተራራ ከመውጣት ቤተእስራኤልን ደግሞ በየጊዜው ለመሥዋዕት የሚቀርቡ እንስሳትን ይዘው ወደ ኢየሩሳሌም ከመሄድና ከመድከም የሚያሳርፍ የምሥራች ነው::

አንድ ሰው በህመም ወይም በሌላ ችግር የተነሣ ወደ ተራራው ወይም ወደ ኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስ መሄድ ባይችል ከአምላኩ ጋር የመገናኘትና ለአምላኩ የሚቀርብ መሥዋዕትም ሆ ነ መ ባ የማቅረብ ዕድል ሳያገኝ ይቀር ነበር:: ይሁን እንጂ ቢሆንለትና እዚያ ቢደርስ እንኳን መንፈሳዊ ልደትን ባላገኘ፣ ዳግም በክርስቶስ ባልተፈጠረና ከዲያብሎስ አገዛዝ ነፃ ባልወጣ መንፈሳዊ ባርነት ሥር ወድቆ የሚያቀርበው አምልኮ በመሆኑ በእግዚአብሔር ዘንድ አምልኮው ፍጹም አልነበረም::

ዛሬም የአምልኮ ስፍራው የመቀየሩ ብስራት ያልደረሳቸው /ያልገባቸው/ አንዳንድ ክርስቲያኖች ይህን የአጠ ይሁድና የሳምራውያንን ሃይማኖታዊ ልማድ በግልጽ ሲያከናውኑት እናያለን:: እግዚ አብሔር ሊመለክበት ራሱ ወደመረ ጠው ስፍራ በመሄድ ፈንታ ባማረ ድንጋይ በተገነባ ሕንፃ ወይም ቅዱሳት መካናት ተብለው በሰዎች ወደተሰየሙ አድባራትና ገዳማት በመሄድ ሥፍራና ቦታ የሚወስነው የአምልኮ ሥርዓት ውስጥ ገብተው

(ወደ ገጽ 10 ይዞራል)

## ከተመሠረተው.. ከገጽ 8 የዞረ

አድርገው «የክርስቶስ ቤተክርስቲያን» ወይም ተመሳሳይ ቡድናዊ/ሴክታሪያን/ ቤተእምነት ሊመሠርቱ ይችሉ እንደነበር መገመት ይቻላል:: ይህም ወደ ሌሎች ቦታዎች እየጠ ተስፋፉ አንዲቱን የክርስቶስን አካል በእጅጉ በከፋፈለ ነበር፤ ይሁን እንጂ እንዲህ ማድረጉ አግባብ ካለመሆኑም የተነሣ ፈጽሞ መንፈሳዊነት የጎደለውና የዳኑበትን ጌታ አለማወቅ በመሆኑ ሐዋርያው «ጳውሎስስ ስለእናንተ ተሰቀለን? ወይስ በጳውሎስ ስም ተ ጠመቻችሁን?» ሲላቸው እንመለከታለን:: እዚህ ላይ በጥቂቱ ቆም ብለን ብናስብ የእነዚህ ሰዎች መሠረታዊ ችግር ያለው በመካከላቸው የተከሰተውን ልዩ ልዩ ክርክር በፍቅርና በትህትና በመፍታት አብረው መኖር ሳይችሉ ሲቀሩ አገልጋዮችን እንደእምነት መሠረት አድርጎ በእነርሱ ስም ለመሰባሰብ መፈለጋቸው ላይ ነው:: ይሁን እንጂ ጳውሎስም ምንም እንኳን የተመረጠ ዕ/ሐዋ.ሥ.9:15/ ቢባልም የእምነት መሠረት አይደለም፤ እንዲሁም ጴጥሮስ ብፁዕ ቢባልም/ማቴ16:17/ ጴጥሮስን ብፁዕ ያሰኘው አብ የገለጠለትና እርሱ የመሰከረው «አንተ ክርስቶስ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ነህ» የሚለው ምስክርነት እንጂ ራሱ ጴጥሮስ ለማንም መሠረት ሊሆን አይችልም:: አጵሎስም ምንም ያህል በመጻሕፍት እውቀት የበረታና የጌታን መንገድ የተማረ ቢሆንም/ሐዋ.ሥራ18:25/ መጻሕፍት የሚመሰክሩለት ጌታ ኢየሱስ እንጂ/ዮሐ5:39/ አጵሎስ ለማንም መሠረት ሊሆን አይበም:: ስለሆነም ይህንኑ ችግራቸውን ለመቅረፍ ሐዋርያው ለቆሮንቶስ ምእመናን የሚከተለውን ጻፈላቸው፤ «አጵሎስ እንግዲህ ምንድነው? ጳውሎስስ ምንድን ነው? በእነርሱ እጅ ያመናችሁ አገልጋዮች ናቸው፤ ለእያንዳንዳቸውም ጌታ እንደሰጣቸው ያገለግላሉ:: እኔ ተከልሁ አጵሎስም አጠጣ ነገር ግን እግዚአብሔር ያሳድግ ነበር፤ እንግዲያስ የሚያሳድግ እግዚአብሔር እንጂ የሚተክል ቢሆን ወይም የሚያጠጣ ቢሆን አንዳች አይደለም:: .. .. የእግዚአብሔር ህንፃ ናችሁ፤ ከእርሱ ጋር አብረን የምንሠራ ነንና»/1ቆሮ3:5-9/::

እዚህ ላይ ምእመናን የእግዚአ ብሔር ሕንጻ ከተባሉ የአንድ ሕንጻ ብቃትና ጥራት የሚመዘነው ደግሞ በመሠረቱ ጥንካሬ ነውና ሐዋርያው በመቀጠል «የእግዚአብሔር ጸጋ እንደ ተሰጠኝ መጠን እንደ ብልሃተኛ የአናጺ አለ መሠረትን መሠረትሁ፤ ሌላውም በላዩ ያንጻል፤.. .. ከተመሠረተው በቀር ማንም ሌላ መሠረት ሊ መሠርት አይችልምና፤ እርሱም ኢ የሱስ ክርስቶስ ነው»አላቸው/1ቆሮ3:11/:: እንግዲህ አንድ ህንጻ የሚገጥሙትን ችግሮች ሁሉ ሊቋቋም የሚችለው በአለት ላይ ሲመሠረት መሆኑ በሰው ሁሉ ዘንድ የታወቀ ነው:: እግዚአብሔርም እንዲሁ ሕንጻውን የሚመሠርተው በአለት ላይ ነው:: ይህ የእግዚአብሐ ር አለት ደግሞ ማነው? ብሎ መጠየቁ አግባብነት አለው፤ ለዚህም ቅዱሳት መጻሕፍት መልስ አላቸው::

(ወደ ገጽ 10 ይዞራል)

## ከተመሠረተው .... ከገጽ 9 የዞረ

ጌታ ሥጋ ለብሶ ወደዚህች ዓለም ከመግባቱ በፊት የተነገረው የትንቢት ቃል እንዲህ ይላል፤ «እነሆ በጽዮን ድንጋይን ስመሠረት አስቀምጣስሁ፤ የተፈተነውን የከበረውን መሠረቱ የጸናውን የማዕዘን ድንጋይ የሚያምንም አያፍርም»/ኢሳ28፡16/:: ከዚህ ምንባብም እግዚአብሔር ከመጀመሪያው ለቤቱ የሚሆንለትን መሠረት ራሱ ለማስቀመጥ እንደወሰነና ያም መሠረት 1ኛ/የተፈተነ 2ኛ/የከበረና 3ኛ/የጸና የማዕዘን ድንጋይ በመሆኑ በእርሱ የሚያምን ፈጽሞ እንደማያፍር መናገሩን እንረዳለን:: ይህም መሠረት ሌላ ሳይሆን ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው:: እንግዲህ ይህን መሠረት ያስቀመጠው ራሱ እግዚአብሔር ከሆነ ሰው ሌላ መሠረት ሊመሠርት ቢሞክር ለእርሱ ባልተሰጠው ነገር መግባቱ ነውና ተጠያቂ ያደርገዋል፤ በተጨማሪም ሰው የሚመሠርተው መሠረት የተፈተነ፣ የከበረ፣ የጸናና የማያሳፍር ሊሆን እንደማይችል የሰው ልጅ የዘመናት ታሪክ በራሱ በቂ ምስክር ነውና በዚያ ሰው ሠራሽ መሠረት ላይ የተመሠረቱ ሁሉ የኋላ የኋላ የሚያፍሩ ይሆናሉ፤ «አወዳደቃቸውም ታላቅ» ይሆናል /ማቴ7፡26-27/:: የቆሮንቶስን ምእመናን ለዚህ ችግር የዳረጋቸው ዋናው ምክንያት በማደግ ፈንታ በእግዚአብሔር እውቀት ህጻናትና የሥጋ ሰዎች እየሆኑ መሄዳቸው እንደነበር ሐዋርያው ሲገልጥላቸው «ቅናትና ክርክር ስለሚገኝባችሁ ሥጋውያን መሆናችሁ አይደላችሁምን? እንደሰው ልማድስ አትመላለሱምን? አንዱ እኔ የጳውሎስ ነኝ፣ ሁለተኛውም እኔ የአጵሎስ ነኝ ቢል ሰዎች ብቻ መሆናችሁ አይደለምን?»/1ቆሮ3፡1-4/ በማለት መከፋፈል በመካከላቸው በሆነ ጊዜ የነበሩበትን የመንፈሳዊ ሕይወት ብልሽት ያስረዳል:: ስለሆነም በመካከላቸው የተፈጠረው መለያየት በእግዚአብሔር ል አለማደግ ከመሆኑም ባሻገር አልፎ አልፎ በመካከላቸው የሚነሱ ውዝግቦችን የሚፈቱበትን መንፈሳዊ ጥበብን ማጣት እንደነበር የዚሁ መልእክት ሁለተኛ ምዕራፍ በይበልጥ ያስረዳል:: የቆሮንቶስ ምእመናን በሥነምግባር ችግር/ምዕ.5/፣ በግል ጠብ /ምዕ6/፣ በጋብቻ ጉዳይና/ምዕ7/፣ ለጣዖት የታረደ ሥጋን ስለአለመብላት/ምዕ8-11/፣ ስለ ራስ መከናነብና አለመከናነብ/ምዕ11፡1-16/፣ ስለ ጌታ እራት /ምዕ11፡17-34/፣ ስለ ጸጋ ስጦታና ስለአምልኮ/ምዕ.12-14/፣ ስለትጠ ንሣኤ /ምዕ.15/.. ወዘተ በመሳሰሉት ጉዳዮች ላይ አለመግባባት ነበረባቸው:: እነዚህን አለመግባባቶቻቸውንና ክርክሮቻቸውን በፍቅር/ምዕ.13/ በማርገብ የክርስቶስን አካል አንድነት በመጠበቅ ፈንታ በአገልጋዮቻቸው ስም ቡድን አብጀት ወደመለያየት አመሩ:: ይህም ምን ያህል መንፈሳዊነት በመካከላቸው ተዳክሞ እንደነበር ያሳያል:: ሰው በሥጋዊነት ተጽዕኖ ሥር ሲወድቅ የሚገጥሙትን አከራካሪ ጉዳዮችን በፍቅር እየዳኘ አንድነቱን በክርስቶስ ላይ በማጽናት ምትክ በግትርነትና በአልሸነፍም ባይ ስሜት እየተገፋ ያከራከሩትን ችግሮች ምክንያት አድርጎ ወደመለያየት ያመራል፤ ክርስቶስንም ትቶ በክርስቶስ አገልጋዮች ላይ ወደመመሥረት ይሄዳል:: በቤተክርስቲያን ታሪክም የተፈጸመውና እስከዛሬም በክርስቶስ አካል ላይ ጠላት ሰይጣን እየፈጸመው ያለው ጥቃትም ከዚሁ የመነጨ እንደሆነ ግልጥ ነው፤ ይህ ደግሞ የሥጋዊነት መገለጫ ነው::

ዓለማዊቷ የዘመናችን የአፍ አማኟ «ቤተክርስቲያንም» «መለኮታዊ ጠብዓያትን» አጥታ «ሰው ብቻ» ሆና ለመታየቷና መሠረቷንም ከተመሠረተው መሠረት ለይታ በአገልጋዮቿ ላይ መሥርታ ለመገኘቷ ዋንኛው ምክንያት ልትመራባቸው ለሚገቡ ለእግዚአብሔር ቃልና መንፈስ ትክክለኛ ስፍራ ባለመስጠቷና በመካከሏ የሚነሡ የአስተሳሰብና የአመለካከት ልዩነቶችን የምትፈታበትን ጥበብ ማጣቷ እንደሆነ የሚጠራጠር ማን ነው? የቆሮንቶስ «ሥጋውያን አማኞች» ክርስቶስን ትተው በአገልጋዮች ስም የእምነት ጎራ ለይተው ለማምለክ በጣሩበት መንገድ ዛሬም ብዙዎች ከሕያዋን ሰዎች አልፈው በሙታን ሰዎች ስም እየተሰበሰቡ ስብሰባውንና መሰበሰቢያውን በፍጡራን መላእክትና በሙታን የእምነት ባለታሪኮች ስም «የእገሌ ቤተክርስቲያን» ብለው መጥራታቸው፣ ለራሳቸውም በሕያው አለት ፈንታ ፍጡራንን የእምነት መሠረት አድርገው በእነርሱ ስም መጠራታቸው እንደ ስህተት ከመቆጠር አልፎ እንደ ጽድቅ መንገድ እየተሠራበት ሲታይ እንዴት ያሳዝናል:: በሌላ በኩል በልዩ ልዩ ጊዜያት በእግዚ አብሔር ጸጋ ከላይ በተጠቀሰው ስህተት ላይ ነቅተውበት የነበሩበትን ቦታ በመልቀቅ ወደ ክርስቶስ የመጡ ሌሎች ደግሞ

(ወደ ገጽ 19 ይዞራል)

## በዚህ ተራራ...ከገጽ 9 የዞረ

ገንዘባቸውን፣ ጊዜያቸውንና ጉልበታቸውን ሲያባክኑ እናስተውላለን::

ከሁሉ የሚያሳዝነው ደግሞ ተራራ ወጥተው፣ ረጅም መንገድ በእግራቸው ተጉዘው፣ ቀናትንና በዓላትን ምክንያት አድርገው ራሳቸው በሠሩት ሥርዓት እግዚ አብሔርን ለማምለክ መድከማቸውና ይህንንም ድካማቸውን እንደ ታላቅ ጽድቅ፣ የኃጢአት ሥርየት ማግኛ /ኃጢአትን ማስተስረያ/ እንዲሁም የመንግሥተ ሰማያት መውረሻ አድርገው ሲቆጥሩት ማየቱ ነው::

ጌታ ኢየሱስ ለሰማርያይቱ ሴት የነገራት ልብን የሚያሳርፍና ከንቱ ከሆነ አላስፈላጊ ድካም የሚገላግል የሕይወት ቃ ዛሬም ለእነዚህ ሰዎች ሊነገራቸው የተገባ ነው፤ ዛሬ እግዚአብሔር የሰው እጅ የሠራውን ስፍራ ለቅቆ ራሱ ወዳዘጋጀው የከበረ ሥፍራ እንደሄደም ሊነገራቸው የግድ ነው:: እግዚአብሔር በሌለበት ሥፍራ መገኘት/መሰባሰብ/ አድካሚ ከመሆኑም ባሻገር የከበረውን አምላክ በቦታና በሥፍራ ወስኖ ለማምለክ መሞከርም በራሱ ስህተት መሆኑ ሊታወቅ ይገባል::

እንግዲያውስ ታዲያ የእግዚ አብሔር የአምልኮ ሥፍራ ወዴት ነው? ብሎ መጠየቁ ተገቢ ነው:: በክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅነት ያመኑ ክርስቲያኖች ሁለት ወይም ሦስት ወይም ከዚያ በላይ ሆነው በክርስቶስ ስም በተሰባሰቡበት በማናቸውም ሥፍራ እግዚአብሔር ይገኛል/ማቴ18፡20/:: እርሱ አምልኮና ለስሙ የሚሆን መሥዋዕት ይቀርብለት ዘንድ በአዲስ ኪዳን ስሙን ሊያኖርበት የመረጠው ስፍራም ይህ ነው:: የእግዚአብሔር የመገኘቱም ምሥጠር የሥፍራው ታሪካዊነት ወይም ክብር ሳይሆን በክርስቶስ ስም ዙሪያ መሰባሰቡ ነው:: ይህም መሰባሰብ በጌታ በኢየሱስ እስከሆነ ድረስ የእግዚአብሔር መቅደስ ነው:: እግዚአብሔርም በክብር በአማኞች መካከል ይገለጣል/ይመላለሳል/::

እንደዚህ በጌታ በኢየሱስ ስም ስንሰበሰብ እርሱ በመካከላችን በመንፈስ እንደሚገኝ ሁሉ እኛም እርሱ በሊቀ ካህናትነት ወደሚያገለግልባት እውነተኛይቱ ሰማያዊት መቅደስ በመንፈስ እንገባለን:: ስለ እኛ ቀዳሚ ሆኖ ጌታ የገባበት ሰማያዊ መቅደስ ክርስቲያኖች ሁሉ በግልም ሆነ በማህበር በሚሰባሰቡበት ጊዜ በልጅነት መንፈስ ሆነው በመንፈስ ቅዱስ ኃይል እየታገዙ እግዚአ ብሔርን የሚያመልኩበት ማዕከል ነው /ዕብ6፡20/:: በዚያ ማዕከል መሥዋዕቱም መሠዊያውም ሊቀ ካህናቱም አንድ ብቻ ሲሆን እርሱም ሰው የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው:: በምድር ላይ ያሉ አማኞች በሙሉ በጋራ ያላቸው የአምልኮ ማዕከል ያቺው በሰማይ ያለች የእግዚአብሔር መቅደስ ናት:: ስለሆነም እግዚአብሔርም ልጁን ልኮ የተሻለ አምልኮ መፈጸም የምንችልበትን መንገድና የአምልኮ ማዕከል አመለከተን፤ ከእንግዲህ ወዲያ በሥፍራና በቦታ ሳይሆን እጅ ባልነካትና ባልተ ጠበባት ሰማያዊ መቅደስ በልጅነት

(ወደ ገጽ 12 ይዞራል)

## ቤተክርስቲያን.. .. ከገጽ 8 የዞረ

አይችልም፤ በምድር ላይ የነበረውን ማንነቱን ይዞ ወደዘላለም ስፍራው ይሄዳል እንጂ:: ከኃጢአቱ ከሞተ በሰማይም ኃጢአተኛ ነው:: በምድር ላይ በጌታ በኢየሱስ ቤዛነት ከኃጢአቱ ድኖ በሥጋ ቢሞት ደግሞ ከዚያን በኋላ ማንነቱን ሊያበላሽበት የሚችል ምንም ኃይል የለም፤ ምክንያቱም በምድር ላይ ከኃጢአቱ ሲድን መዳኑ በሰማይም እውቅና አግኝቷልና:: ስለሆነም በዚህ ምድር ስለጌታ ኢየሱስ የሚሰጠውን የሱን ምስክርነት አምኖ ራስ ወደሚሆን ወደእርሱ የተጠጋ አማኝ በአካለ ሥጋ እያለም በእጅ ወዳልተሠራችውና ራሱ ጌታ ኢየሱስ ወዳለባት ሰማያዊ መቅደስ በመንፈስ የመግባት በዚያም ሆኖ የመጸለይ ብቻ አለው/ዕብ10:19-20/፤ ከዚህም ባሻገር እንዲህ ያለው አማኝ ነፍሱ ወደ ጌታ ሳትሄድ ከወዲሁ «ወደ ጽዮን ተራራና ወደሕያው እግዚአብሔር ከተማ፣ ወደ ሰማያዊቱም ኢየሩሳሌም፣ በደስታም ወደ ተሰበሰቡት ወደ አእላፋት መላእክት፣ በሰማያትም ወደ ተጻፉ ወደ በኩራት ማህበር፣ የሁሉም ዳኛ ወደሚሆን ወደ እግዚአብሔር፣ ፍጹማን ወደሆኑት ወደ ጻድቃ መንፈሶች፣ የአዲስ ኪዳን መካከለኛ ወደሚሆን ወደ ኢየሱስ፣ ከአቤልም ደም ይልቅ የሚሻለውን ወደሚናገር ወደመርጨት ደም» ደርሷል/ዕብ12:22-24/::

ስለሆነም ምስክርነቱን በተመለከተ ሰዎች ዛሬ በምድር ላይ የሚወስኑት ውሳኔ ምድራዊ ውሳኔ ብቻ ሳይሆን በሰማይ ላይም በጌታ ፊት የሚታወቅ ውሳኔ መሆኑን አውቀው ሊጠነቀቁ ይገባቸዋል:: በምድር ላይ ካልተሻሻለም ውሳኔው በሰማይ ላይ ሊሻሻል አይችልም:: ወንጌሉን እምቢ አንቀበልም ሲሉም እምቢ ያሉት የሚመሰክረውን ምስክር ብቻ አይደለም፤ ምስክርነቱንና ምስክሩን የላከውን ጌታ ጭምር እንጂ:: በመሆኑም ሰዎች በጊዜው አሁን በምድር ላይ እየተሰጠ ያለውን ምስክርነት ሊቀበሉና ወደ ክርስቶስ ሊከማቹ ይገባል:: እዚህ ላይ አንባቢው ልብ ይበል::

ከዚህ በመቀጠል ደግሞ እንዲህ ያለውን ግልጥና የተባረከውን የጌታ ኢየሱስን ንግግር በማስታከክ የተፈጠሩና ለብዙ ዘመናት የተንሠራፉ በእጅጉ ስህተት የሆኑ አመለካከቶችን በመዘርዘር እንመለከታቸዋለን:: አላማውም ሰዎችን ለመተቸት ሳይሆን የተመሠረቱት የስህተት አተሳሰቦች ከዚህ ምንባብ ጋር ምንም ግንኙነት የሌላቸው መሆናቸውን ለማሳየት ነው:: ስለሆነም በጥቅሉ ሱ የሚከተሉትን አመለካከቶች የሚያሳይ አይደለም::

### 1.መክፈቻው ለጴጥሮስ ብቻና ለተወሰኑ ተተኪ ነን ባዮች የተሰ ጠ አይደለም

የመንግሥተ ሰማያት መክፈቻ ለጴጥሮስ ብቻና በእርሱ እግር የተተካን ነን ለሚሉ ወገኖች ብቻ የተሰጠ ነው ብለው የሚያምኑ በርካታ ሰዎች አሉ፤ ይህ ደግሞ በጴጥሮስ እና በእነርሱ በኩል ያላለፈ ሁሉ ወደ መንግሥተ ሰማያት አይገባም ያሰኛል፤ ሆኖም እግዚአብሔር ልጁን ኢየሱስ ክርስቶስን እንጂ ከፍጡር ወገን ጴጥሮስንም ሆነ ማናቸውንም ሌላ ወገን ወይም ጴጥሮስን ማዕከል ያደረጉ የሃይማኖት ድርጅቶችን ብቸኛ መንገድ አላደረገምና ይህ ምንባብ መክፈቻው የተሰጠው ለጴጥሮስና ለተተኪ ነን ባዮች ብቻ ነው ብለው ለሚያምኑ ሰዎች መሠረት ሊሆናቸው

ይህ መክፈቻም ሆነ ሌላው የጸጋ ስጦታ በራሱ በጌታ ኢየሱስ የሚሰጥ እንጂ ሲወርድ ሲዋረድ የሚኖርና ከግለሰቦች የሚወረስ አይደለም::

አይችልም፤ ምክንያቱም መክፈቻው ለጴጥሮስና ለእነርሱ ብቻ ሳይሆን በኋላም «ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው ያዘዝኋችሁንም እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀመዛሙርት አድርጓቸው» /ማቴ28:18-20/ በሚል በዘላለማዊ መገኘቱና በሰማይና በምድር በተጐናጸፈው ሥልጣኑ የተደገፈ ትእዛዝን ጌታ ለሁሉም ደቀመዛሙርቱ እንደሰጠ እናያለንና:: በሌላ በኩል ደግሞ ለጴጥሮስና ለእኛ ብቻ የተሰጠ ነው የሚሉ ሰዎች ይህ አባባላቸው መጀመሪያም ከጴጥሮስ በቀር በሌሎች ሐዋርያት እጅ ነፍሳት ወደ ጌታ አልመጡም ወይም ከዚያን በኋላም በሌሎች አገልጋዮች እጅ ወደጌታ የመጡ ነፍሳት የሉም እንደሚያሰኛቸው ሊገነዘቡ ይገባል:: ይሁን እንጂ መክፈቻው በጴጥሮስና በሌሎች ሐዋርያት ሳያበቃ እስከዛሬ ድረስም እንደፈጹ ለዚህ አገልግሎት ለተጠሩ ሁሉ የሚሰጥ ነው:: ይህ ስለሆነም ወደ አንዲቱ ሕያዊት ቤተክርስቲያን እየዳኑ የሚጨመሩ ነፍሳት ቁጥር በዘመናትና በቦታ ሳይገደብ፣ የእግዚአብሔርም የጸጋ ወንዝ ሳይቋረጥ እየፈሰሰ ከዚህ ትውልድ ሊደርስ እንደቻለ ስናይ ይበልጡኑ ጌታን እናመሰግናለን:: ስለሆነም መክፈቻው የጥቂት ግለሰቦች ወይም የሃይማኖት ቡድኖች የብቻ ስጦታ ሳይሆን በሁሉም ስፍራ በሁሉም ዘመናት «ሰዎች ሁሉ ሊድኑና እውነቱን ወደማወቅ እንዲደርሱ በሚወድ በእግዚአብሔር» ወደ አገልግሎት ለተጠሩ፣ ወደፊትም ለሚ ጠሩ አገልጋዮቹ ሁሉ የሚሰጥ መሆኑ ሊታወቅ ይገባል/1ጢሞ2:3/::

### 2.መክፈቻው በሰዎች በኩል አይተላለፍም

በሌላ ረገድ ደግሞ ይህ ለጴጥሮስ የተሰጠው መክፈቻ በእርሱ እግር በተተኩት ሰዎች አማካይነት ከመጀመሪያው ምእተ ዓመት ጀምሮ ሳይቋረጥ በሐዋርያዊ ትውፊት /አፖስቶሊክ ሰክሰሽን/ ወይም በሐዋርያት እግር በተተኩት አበው ወይም ጳጳሳት ወይም ፓፓዎች በኩል በቅብብሎሽ ሲወርድ ሲዋረድ ከእኛ እጅ ደርሷል የሚሉ ወገኖች ስላሉ ይህንን አባባላቸውንም ከዚሁ ከተነሳንበት ምንባብ አኳያ ማየቱ ተገቢ ይሆናል::

በመሠረቱ ይህ ሲወርድ ሲዋረድ ከእኛ እጅ ደርሷል የሚሉት መክፈቻ ወይም እንደእነርሱ አባባል ሐዋርያዊ ሥልጣን በጴጥሮስ በኩል ሊወረስ እንደሚችል ወይም ጴጥሮስ ለተከታዮቹ የሚያወርሰው እንደሆነ በምንባቡ አልተገለጠም:: ጴጥሮስም ሆነ ሌሎች ሐዋርያት እንድንወርሰው የጻፉልን ከጌታ የተቀበሉትን ድንጋጌ /1ቆሮ.11:23/፣ ስለሕይወት ቃል ከመጀመሪያው የነበረውን፣ ያዩትን፣ የሰሙትን፣ የዳሰሱትንና የተገለጠውንም ሕይወት/1ዮሐ1:1-5/፣ ከሌሎች ጋር «የሚካፈሉትን መዳንና» «ለቅዱሳን አንድ ጊዜ ፈጽሞ የተሰጠውን ሃይማኖት» /ይሁዳ 3/ እንጂ ሌላ በሰዎች በኩል ስለሚተላለፍ ሥልጣን አይደለም:: ይህ መክፈቻ የሚወረስ እንደሆነም አልነገሩንም:: ስለሆነም መክፈቻው በኋላ ዘመናትም ቢሆን የክርስቶስ ደቀመዝሙር ለሆነ ሁሉ በራሱ በጌታ በኢየሱስ ያን ጊዜ ለጴጥሮስ እንደተሰጠ የሚሰጥ ነው እንጂ ግለሰቦች ወይም የሃይማኖት ድርጅቶች እንደነገሥታት ቤተሰባዊ በትረ ሥልጣን ወይም ሃብት የሚቀባበሉት ወይም አንዱ ለአንዱ የሚያወርሰው በግለሰቦች ውክልና የሚታደል አይደለም፤ ሲወርድ ሲዋረድ በሰዎች በኩል የመጣ መክፈቻም የለም፤ ይህ መክፈቻም ሆነ ሌላው የጸጋ ስጦታ በራሱ በጌታ ኢየሱስ የሚሰጥ እንጂ ሲወርድ ሲዋረድ የሚኖርና ከግለሰቦች የሚወረስ አይደለም::

ዛሬም በሰማይና በምድር ሥልጣን ያለው ጌታ ኢየሱስ በጸጋው ለሚጠራቸው በመንፈስ ቅዱስ በኩል እንደወደደ ስጦታን ይሰጣል /1ቆሮ12:11/፤ የምርኮው ባለቤትም ራሱ ነው/ኤፌ4:8/፤ ለጴጥሮስ አስቀድሞ ኋላም ለሁሉም ደቀመዛሙርት የሰጠውን መክፈቻ እየሰጠ ዛሬም ሆነ ነገ ለቤቱ አገልግሎት አገልጋዮችን የሚያስነሳ፣ በኃይልና በመገኘቱ የሚያስማራም ራ

*(ወደ ገጽ 13 የዞረ)*

## በዚህ ተራራ.. .. ከገጽ10 የዞረ

*መንፈስ እየገባን አብን በነፃነት የምናመልክበት ማዕከል በክርስቶስ ኢየሱስ እንደተዘጋጀልን ይህም የዛሬ ሁለት ሺህ ዓመት ገደማ በእርሱ ወደዚያች መቅደስ መግባት እንደ ተጀመረ አውቀናል/ዕብ10፡19/፤ ክብር ለእርሱ ይሁን፡፡*

በዘመነ ብሉይ በምድር የተበተኑ አይሁድ በዓመት አንድ ጊዜ ወደ ኢየሩሳሌም እየሄዱ ይሰግዱ እንደ ነበር ሁሉ በዘመነ ሐዲስ ያሉ አማኞችም በሰንበት ወይም በበዓላት ወይም በወር መባቻ ወይም በዓመት አንድ ጊዜ ሳይሆን በፈለጉት ጊዜ ወደ ሰማያዊቷ መቅደስ በመንፈስ በመግባት ለእግዚአብሔር ይሰግዳሉ፤ ***<u>በምድር ላይ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተሰብስበው እግዚአብሔር በመካከላቸው በክብር ሲገለጥ እነርሱም በአንድ ልብ በመንፈስ ሆነው በሰማያዊቷ መቅደስ በአብ ፊት በክርስቶስ ክብር ይገለጣሉ፡፡</u>*** ይህ ደግሞ ለአማኞች የተሰጠ ታላቅ ጸጋ ነው፡፡ ይህንንም ተረድቶ እንደ እግዚአብሔር ል ለአብ መስገድ/አብን ማምለክ/ ህይወትና እረፍት ነው፤

## ቤተክርስቲያን.ከገጽ 13 የዞረ

በድሉ ስለበደላቸው የመጣባቸውን የእግዚአብሔርን ተግሣጽ ያውጅ ነበር እንጂ በራሱ ሥልጣን ማንንም ከኃጢአቱ እንዲሞት ወይም በበደሉ እንዲታሠር አላደረገም/ሐዋ.ሥራ5፡1-6/፡፡ እንደዚሁም በስብከቱም ሆነ በአገልግሎቱ ወንጌልን እየሰበከ በወንጌሉ ኃይል ሰዎች ነጻ እንዲወጡ ያደርግ ነበር እንጂ ማንንም ሰው እንደጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ «ኃጢአትህ ተሠርዮልሃል» ወይም «እግዚአብሔር ይፍታህ» ብሎ አሰናብቶ አያውቅም፡፡ በጻፈው መልእክት በኩልም ሰዎች ከኃጢአት እንዲጠበቁ አበክሮ አሳሰበ እንጂ እርሱ ኃጢአትን ሊያስተሠርይ እንደሚችል አልጻፈም፡፡ ሆኖም በማቴ18፡18 እና በዮሐ20፡23 ላይ የተጻፈው ምን ማለት ነው? የሚል ጠያቂ አይጠፋምና ጌታ ቢፈቅድ በእውነት ጋዜጣ ቁጥር 3 ላይ በዚህ ኃጢአትን የማስተስረይ ርእስ ላይ በሰፊው እንደ ምንቀጥልበትና ከላይ የተጠቀሱትን ጥቅሶችም እንደ ምናብራራ ከወዲሁ በመግለጥ ጥናታችንን እንደመድማለን፡፡

## ከተመሠረተው ...ከገጽ 19 የዞረ

ሰይጣን ከማናቸውም ጊዜ ባላነሰ መልኩ ሥጋዊነትን ተጠቅሞ ልዩ ልዩ ቡድኖችን ከቁጥር በላይ እስኪሆኑ ድረስ ባበራከተበት ዘመን ላይ ብንገኝም ቤተክርስቲያን አንዲት ናት፤ ዛሬም ከሁለት ሺህ ዓመታት በኋላ መሠረቷ ጌታ ኢየሱስ ብቻ ነው፤ ራሷም ያረገውና በክብር ያለው በቅድስተ ቅዱሳን በተከሻውና በልቡ ጽላት ላይ የአባሎቿን ስም በጋራና በግል ተሸክሞ በአብ ፊት የሚታይ ታላቁ ሊቀካህን ጌታ ኢየሱስ ነው፡፡ ከምድራዊ የክርስትና ሃይማኖት ጎሰኞነት አልፈው ወደዚህች መንፈሳዊት ማህበር የደረሱ፣ «የጌታ ኢየሱስን ል ሰምተው የሚያደርጉ» /ማቴ7፡24/፣ የፍጡራንን ስሞችና ሰው ሠራሽ አስተሳሶችን ትተው መሰብሰቢያቸውን የጌታ ኢየሱስ ስም ያደረጉ/ማቴ18፡20/፣ እንደ ሰው ልማድ የማይመላለሱ ነገር ግን «የክርስቶስ ልብ» ያላቸው/1ቆሮ2፡16/ እነርሱ በሕያው አለት በክርስቶስ ላይ ተመሥርተዋልና የአንዲቱ የክርስቶስ አካል ብልቶች ስለሆኑም ደስ ይላቸዋል፤ የአካሉን አንድነት ለመጠበቅና ነፍሳትንም ወደዚያች ለመጨመር የሚተጉ ከጌታ ብድራት አላቸው፡፡

> «ስለዚህ ማንም በሰው አይመካ ነገር ሁሉ የእናንተ ነውና ጳውሎስም ቢሆን አጵሎስም ቢሆን ኬፋም ቢሆን ሞትም ቢሆን ያለውም ቢሆን የሚመጣውም ቢሆን ሁሉ የእናንተ ነው፤ እናንተም የክርስቶስ ናችሁ፤ ክርስቶስም የእግዚአብሔር ነው» /1ቆሮ3፡21-23/፡፡

## አገልግሎት ...ከገጽ 3 የዞረ

ሰዎች ከመጀመሪያውኑ ወደ መንፈሳዊ አገልግሎት የሚገቡት በዚህ ምድር የሚገኘውን ጣፋጭ ፍሬ ከያዘ ዛፍ ላይ በሌላ መንገድ ሊደርሱና የሚፈልጉትን አለማዊ ፍሬ ለመቀጠፍ ሳይችሉ ስለቀሩ ወንጌልን መሰላል አድርገው ለመጠቀም ነው፡፡ ስለሆነም ምንም ያህል በሰው ፊት አብዝተው ቢያገለግሉ፣ አገልግሎታቸውም የሠመረ ቢመስልና ሰዎችንም ማሰባሰብ ቢችሉ በእርግጥ አገልግሎታቸው በእግዚአብሔር ፊት መሥዋዕት ሆኖ የቀረበ አይደለምና አግባብነት የጎደለው እንደሆነ ሊያውቁና ሊታረሙ ይገባል፡፡

አገልግሎት መሥዋዕት ከመሆኑም በተጨማሪ በመሥዋዕትነቱ ሊኖረው የሚገባውን ጠባይ መንፈስ ቅዱስ ሳይገልጥልን አልቀረም፡፡ እነዚህም ጠባያቱ እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኙ፣ ሕያውና ቅዱስ መሆኑ ናቸው፡፡

### <u>እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ መሥዋዕት</u>

ሰዎች ሌሎች መሥዋዕቶችን እግዚአብሔር በማይፈልገው መንገድ አዘጋጅተው ለእግዚአብሔር እንደሚያቀርቡ ሁሉ አገልግሎታቸውንም እግዚአብሔርን ደስ በማያሰኝ መንገድ ሊፈጽሙት ይችላሉ፡፡ በመሆኑም በማናቸውም ለእግዚአብሔር በምናቀርበው ነገር እንደምንጠነቀቀው ሁሉ አገልግሎትም እግዚአብሔርን ደስ የማያሰኝ እንዳይሆን ልንጠነቀቅ ይገባል፡፡ በአቤልና በያል መሥዋዕቶች መካከል የነበረው ቀዳሚው ልዩነት በየል መሥዋዕት እግዚአብሔር ደስ አለመሰኘቱ ነው/ዘፍ4፡5/፡፡ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ባቀረበው መሥዋዕት ውስጥ ግን ይህ የመሥዋዕት ጠባይ ተሟልቶ ይገኛል፤ እግዚአብሔር በጌታ በኢየሱስ ሙሉ በሙሉ ደስ ተሰኝቶበታል /ማቴ.17፡5/፡፡ ጌታ ኢየሱስ «ለእግዚአብሔር የመዓዛ ሽታ የሚሆንን መባንና መሥዋዕትን አድርጎ ራሱን አሳልፎ ሰጠ» /ኤፌ.5፡1/፡፡ ስለዚህ አገልጋይም እንደጌታው ለእግዚአብሔር ሙሉ በሙሉ የመዓዛ ሽታ አድርጎ ራሱን አሳልፎ የሰጠ ሰው ሊሆን ይገባል፤ ጌታ ኢየሱስ ለላከው አባቱ ፍጹም ታዛዥነትን እንዳሳየ የላከውን የአባቱን ፈቃድ እንጂ የራሱን እንዳላደረገ፣ ከራሱም እንዳልተናገረ የራሱንም ፈቃድ እንዳልፈጸመ ሁሉ /ዮሐ4፡34፣ 5፡30፣6፡38/ አገልጋይም እንዲሁ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ብቻ የሚፈጽም ሊሆን ይገባዋል፤ እንዲህ ያለው አገልግሎት እግዚአብሔርን በእጅጉ ደስ ያሰኘዋል፡፡ ስለሆነም በጥቅሉ አንድ አገልጋይ ሰውነቱን እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ አድርጎ ማቅረብ የሚችለው አገልጋዩ የእግዚአብሔርን ሐሳብ በእግዚአብሔር «ልብና ነፍስ እንዳለ እንዲሁ» ሳይጨምርም ሳይቀንስም የሚናገርና የሚፈጽም ሲሆን ነው/1ሳሙ2፡35/፡፡ ከዚህ አኳያ አገልጋይ ማለት በሰው ፊትም ሆነ በእግዚአብሔር ፊት አካሄዱን እንደ ኢየሱስ ክርስቶስ ያደረገ ሰው ማለት ነው፡፡

### <u>ሕያው መሥዋዕት</u>

መሥዋዕቱ ሕያው የሚሆነውም የሚቀርብበት መሠረትና ምክንያት ሕያውነት ያለው ሆኖ ሲገኝ ነው፡፡ ብድራታቸውን ከጌታ ሳይሆን ከሰው ለመቀበል ወይም ስለ ጊዜያዊ ምክንያትና ጥቅም ብለው የሚያገለግሉ መሥዋዕታቸው ህያውነት አይኖረውም፡፡ ስለጌታ ብለው የሚያገለግሉ አገልግሎታቸው የሚጠፋ አይደለም፤ ስለስሙ ፍቅር ብለው የደከሙት ድካም፣ የተቀበሉት መከራ በሕያው እግዚአብሔር ፊት አይዘነጋም፤ «የእግዚአብሔርን ቅዱሳንን ስላገለገላችሁ እስከአሁንም ስለምታገለግሉአቸው ያደረጋችሁትን ሥራ ለስሙም ያሳያችሁትን ፍቅር ይረሳ ዘንድ ዓመፀኛ አይደለምና» /ዕብ6፡10/ ተብሎ እንደተጻፈው፡፡

*(ወደ ገጽ18 ይዞራል)*

**ቤተክርስቲያን..** ከገጽ 11 የዞረ

ሱ ጌታ ኢየሱስ ነው፤ ለዚህ ታላቅ ተልእኮ ደግሞ ሮምም ሆነች እስክንድርያ ወይም ጀርመን ወይም ካናዳ ቁልፉን የወረሱና የሚያወርሱ እንደራሴዎች አይደሉም:: «መክፈቻው በእኛ ዘንድ አለ፤ ወርሰነዋል» በሚሉ ሰዎች እጅ በመጫን ወይም ከወይራም ሆነ ከሌሎች ነገሮች የተገኙ ፍጥረታዊ ቅባቶችን በመቀባት ይህ መክፈቻ አይገኛም፤ ጌታ ኢየሱስ እንዲያው በመጥራቱ ጸጋ አስቀድሞ በቀጥታ ለጴጥሮስ እንደሰጠ ዛሬም በሰዎች ሳይሆን በቀጥታ በመንፈስ ቅዱስ በኩል መክፈቻውን ለአገልግሎት ለተጠሩት ሁሉ ይሰጣል:: ይህ መክፈቻም በዚህ መልኩ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ጸጋውን በተቀበሉት ሁሉ እጅ ዛሬም ይገኛል::

## 3.*መክፈቻው ሥልጣነ ክህነት አይደለም*

ሌሎች ሰዎች ደግሞ ይህን ጴጥሮስ የተቀበለውን መክፈቻ «ሥልጣነ ክህነት» አድርገው ማየታቸው አልቀረም:: የሚያሳዝነው ደግሞ ለዚህ አመለካከታቸው ይህንኑ ምንባብ መሠረት ማድረጋቸው ነው:: በዚህም ያልተማረ ነው ለማለት በምፀት «ምእመን» ወይም «ጨዋ» እያሉ ከሚጠሩት ሕዝብ የሚለያቸውን ሥልጣነ ክህነት ያውም የጴጥሮስን ሥልጣን እንደተላበሱና ከሌላው እንደሚበልጡ ያስባሉ፤ ያስተምራሉ:: እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ከሆነ ደግሞ አንድን አማኝ ከሌላው የበለጠ የሚያደርገው ጌታ «እንደዚህ ህጻን ራሱን የሚያዋርድ»/ማቴ18፡4/ ሲል እንዳስተማረው ራስን ማዋረድ፣ ወይም «ማንም ከእናንተ ታላቅ ሊሆን የሚወድ የእናንተ አገልጋይ ይሁን/ማቴ20፡26-27/ እንዳለው የሌሎች አገልጋይ መሆን፣ ወይም «ሰው ፊተኛ ሊሆን ቢወድ ከሁሉ በኋላ የሁሉ አገልጋይ ይሁን»/ማር.9፡35/ እንዳለ ከሁሉ በኋላ የሁሉ አገልጋይ መሆን፣ ወይም «የአሕዛብ ነገሥታት ይገዙአቸዋል፤ በላያቸውም የሚሠለጥኑት ቸርነት አድራጊዎች ይባላሉ፤ እናንተ ግን እንዲህ አትሁኑ፤ ነገር ግን ከእናንተ ታላቅ የሆነ በመካከላችሁ እንደታናሽ የሚገዛም የሚያገለግል ይሁን» ብሎ የራሱን ምሳሌነት እንዲከተሉ «እኔ ግን በመካከላችሁ እንደሚያገለግል ነኝ» /ሉ.22፡25-27/ ሲል ባስተማረው መሠረት በሚያገለግሉት ላይ አለመሰልጠንና በምትኩ አገልጋይ መሆን ነው:: እውነቱ ይህ ሆኖ ሳለ ከሕዝብ የሚለያቸውና ብልጫ የሚሰጣቸው ሥልጣን እንዳላቸው በማስመሰል እንደነገሥታት በሕዝብ ላይ የሚሠለጥኑ፣ ከሕዝብ የሚለያቸውን ልብስና ልዩ ጌጣጌጦችን ያጠለቁ፣ ልዩ ልዩ ስሞችንም ለራሳቸው ያወጡና ህዝቡን መጽሐፍ ቅዱስ አስተምረው እነርሱ ደረስን ከሚሉበት በማድረስ ፈንታ የአንተን እምነት እኛ እናውቅልሃለን በማለት ራሳቸውን በሚመሩት ሕዝብ ላይ ያሠለጠኑና ራሳቸውን እንደ ብሉይ ኪዳን ሌዋውያን የቆጠሩ ሰዎች በዚህ ምንባብ ላይ ማሳበባቸውን ትተው እንደ ክርስቶስ አገልጋይ ይሁኑ እንላለን:: በክርስቶስ ደም የተዋጁ ቢሆኑ እነርሱም እንደማንኛውም አማኝ «የንጉሥ ካህናት» /1ጴጥ2፡9/ መሆን ይችላሉ:: ይሁን እንጂ ሌላው አማኝ ያላገኘውን ክህነት እነርሱ ተለይተው እንደሚያገኙ ሉ አያሳይም:: እጅ ከእግር እንደሚለይ በጸጋ ስጦታ እንለያያለን እንጂ በብልቶች መካከል በክህነትና በሥልጣን መበላለጥ የለም፤ እኔ ካህን ነኛ ክህነት ተቀብያለሁ አንተ ግን ጨዋ ነህ በማለት ወይም እኔ የተቀባሁ ነኛ አንተ ግን በልሳን አትናገርምና መንፈስ ቅዱስ አያውቅህም ብሎ መለያየትን መፍጠር ራስን በክርስቶስ መንጋ ላይ የማሰልጠን ተልእኮ እንደሆነ 1ኛቆሮ12ን ያነበበ ያገኘዋል:: አማኞች በአዲስ ኪዳን መንፈስ ቅዱስ እንደወደደ በሚሰጣቸው ልዩ ልዩ የጸጋ ስጦታ ዓይነት እንጂ የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ በመሆን አይለያዩም:: እንደ ብሉይ ኪዳን ዘመንም መንፈስ ቅዱስ በአንዱ አማኛ አድሮ በሌላው የማያድርበት፣ ስለሌሎች ጉዳይ ለአንዱ ለተመረጠ ሰው/ለተቀባ/ ብቻ እየገለጠ ከሌሎች የሚሰውርበት ሁኔታ ዛሬ የለም፤ ዛሬ በአዲስ ኪዳን ዘመን በክርስቶስ ያመኑ ሁሉ የተቀቡ ናቸው:: ስለሆነም እጅ ከእግር እግርም ከእጅ አይበልጥምና አማኞች ሁሉም በአካል ውስጥ እኩል ጠቀሜታ ያላቸው ብልቶች ናቸው:: እግዚአብሔር በመንፈስ ቅዱስ በኩል ወደእኛ ያለው ፍቅሩ በመካከላችን ልዩነትን አያደርግም:: እንደዚሁም አንዱ አማኛ ሌላውን አማኛ በዘላለም ሕይወት አይበልጠውም፤ ይህ ላመነ ሁሉ የሚሰጥና የግለሰቦችን ማንነት ከግምት የማያስገባ፣ የክርስቶስን ሞትና ትንሣኤ ብቻ መሠረት ያደረገ ነው፤ ክህነትም እንዲሁ ከማዕዘኑ ድንጋይ ጋር ለተያያዙት ሕያዋን ድንጋዮች ሁሉ የሚሰጥ እንጂ ለአንዱ አማኛ ተሰጥቶ ለሌላው የሚከለከል አይደለም /1ጴጥ2፡5/:: ስለሆነም ከጴጥሮስ እጅ ወደ ቫቲካን የወረደና እስከዛሬ ድረስም ያሻውን የሚያስርና የሚፈታ የክህነት ሥልጣንም ይሁን ወይም ሥልጣነ ጴጥሮስ የለም፤ ከወንጌል እምነት በቀር ወንጌላዊው ማርቆስም ለእስክንድርያ ያወረሰውና በእስክንድርያ በኩል የሚገኛ ወይም ከእስክንድርያ አግኛተነዋል በሚሉ ሰዎች እጅ ብቻ የሚገኛ ሥልጣነ ክህነትም የለም::

## 4.*ጴጥሮስ የመንግሥተ ሰማያት ደጃፍ ጠባቂና ተቆጣጣሪ አይደለም*

ጴጥሮስም በመንግሥተ ሰማያት በር ላይ ተቀምጦ የተወሰኑትን የሚያስገባ የተቀሩትን ደግሞ የሚከለክል አይደለም፤ መዳንን ለዘላለም ታማኛና የእግዚአብሔር ልጅ ሆኖ በእግዚአብሔር ቤት ላይ በተሾመው በክርስቶስ ላይ /ዕብ.3፡6/ በመመሥረት ፈንታ በአንድ ፍጡር በጴጥሮስ ትከሻ ላይ ማስቀመጡ ቅዱሳት መጻሕፍትን ፈጽሞ አለመረዳት ከመሆኑም ባሻገር የጌታ የኢየሱስን ፈራጅነትና ሥልጣንን ወደ ጎን መጣል ነው:: በምድርም ላይ ሆነ በሰማይ ሰዎች ወደ እግዚአብሔር እንዳይገቡ የሚያደርጋቸው ለሉ ምስክርነት የሚሰጡት ምላሽ በጎ ሳይሆን ሲቀር መሆኑን መገንዘብ ይኖርብናል፤ ሰውን ከእግዚአብሔር ፊት የሚሳድደው የገዛ ኃጢአቱ ነው፤ አዳም ከእግዚአብሔር ፊት በገነት ዛፎች የተሸሸገው እግዚአብሔር አሳድዶት አልነበረም፤ የገዛ ራሱ በደል እንዲሸሸግ አደረገው እንጂ/ዘፍ3፡8/:: ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እስከዛሬም ድረስ ሰዎችን ከእግዚ አብሔር ፊት የሚያሳድዳቸው የገዛ በደላቸው ነው:: እውነቱ ይህ ሆኖ ሳለ እነርሱ በምድር ላይ «በሥልጣነ ጴጥሮስ ወጳውሎስ አውግዣለሁ» ብለው ስላሉት ብቻ ያፋቸው ል ያን ሰው ከመንግሥተ ሰማያት የሚያስቀረው የሚመስላቸው ምንኛ ስተዋል! በሌላ በኩል ደግሞ በልብስና በስም ካልሆነ በቀር ከክርስትና ሕይወቱ አኳያ ከእነርሱ አንዳች ልዩነት የሌለው ሰው «ተፈቱ» ብሎ ሲናገራቸው የተፈቱና መንግሥተ ሰማያት የሚገቡ የሚመስላቸው ምንኛ ተታለዋል! ሰውን ወደ እግዚአብሔር መንግሥት እንዳይገባ የሚከለክለው በእግዚአብሔር ልጅ አለማመኑ ብቻ0 ነው፤ «ልጁ ያለው ሕይወት አለው፤ የእግዚአብሔር ልጅ የሌለው ሕይወት የለውም» /1ዮሐ5፡12/:: ጴጥሮስም ሆነ የእርሱ ሥልጣን ሲወርድ ሲዋረድ በእኛ እጅ ይገኛል የሚሉት ማንንም ማስገባት ሆነ መከልከል የሚችሉ አይደሉም:: ስለሆነም መንግሥተ ሰማያትን በተመለከተው ስላለው ጉዳያችን እግዚአብሔር ታማኛ ልጁን በቤቱ ላይ ስለሾመልን እንዲህ ካለው የሰው አመለካከት ተለይተን ወደ ጌታ ኢየሱስ በእምነት እንቅረብ::

## 5. *ምንባቡ ጴጥሮስ ኃጢአት እንደሚያስተሰርይ አያሳይም*

ይህ ምንባብ የኃጢአት ሥርየትን ከግለሰቦች መቀበልን አያሳይም፤ ኃ ጢአታችንንም ይቅር እንዲለን ወደ ጴጥሮስ መጸለይ እንዳለብን አያሳይም፤ ጴጥሮስም ቢሆን በዚህ ምድር ወንጌልን ያገለግል በነበረበት ዘመንም ያላመኑ ሰዎች እንዲያምኑና ንስሐ ገብተው የኃጢአት ሥርየት እንዲያገኙ ይመክር ነበር እንጂ በራሱ ለማንም የኃጢአት ሥርየት አልሰ ጠም/ሐዋ.ሥራ2፡38፣ 8፡22/:: የእምነት ል ከተሰበከላቸው በኋላም ቢሆን ሰዎች ሲ

*(ወደ ገጽ 12 ይዞራል)*

እከሥት በምሳሌ
አፉየ ወእነግር
ዘኅቡእ ዘእምትካት
ማቴ13፡35



# ባረከት ጥበብ

በምሳሌ አፌን እከፍታለሁ ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ የተሰወረውን እናገራ

## ጠበው ዳኛ ሲሆን.....

በአንዲት የፈረንሳይ ከተማ ባለ ጠጋ የነበሩ ባልና ሚስት ይኖሩ ነበር፡፡ ስለትናንትናውም ሆነ ስለነገው ምንም የማያስቡ ነበሩ፡፡ ባልም የንግድ ሥራውን በተገቢ ሁኔታ ሳያስተካክል በድንገት ሞተ፤ ሚስቱም በንግድ ሥራው ውስጥ ብዙ ያልተስተካከለ እና ያልተመቻቸ ነገር እንደነበረ አታውቅም ነበር፡፡ ነገር ግን ሟቹን ይወደው፣ ይረዳውና የሙያ እገዛ ያደርግለት የነበረ አንድ ብልህና ደግ ጠበ ነበር፤ እርሱም ሟቹን ሐሳብ የለሽ እንዳይሆንና ንብረቱንና ሥራውን በየጊዜው ከዕዳ ነጻ እንዲያደርግ ይመክረው ነበር፤ ሆኖም ባለጠጋው ሊሰማው ስላልቻለ ምንም ውጤት አላገኘም ነበር፤ ጠበውም የሰውየውን በድንገት መሞት በሰማ ጊዜ ከልቡ አዝኖ የሟችን ሚስት በሚቻለው ሁሉ በሙያው ሊረዳት አሰበ፤ ሊያጽናናትም ፈልጎ ከጥቂት ቀናት በኋላ ወደ ቤቷ በሄደ ጊዜ ግን እርሷ ያለ ኃዘን ሆና ስለምኞትና ስለደስታ እያሰበች ባል እንዳልሞተባትም ሆና አገኛት፤ ይህ ሁኔታም አሳዘነው፡፡ ቢሆንም በባልዋ መሞት የተሰማውን ኃዘን ከገለጸላት በኋላ «ባለቤትሽ ከመሞቱ በፊት በብድር ስላስያዛቸው ንብረቶቹና ስላሉበት ዕዳዎቹ ሁሉ ያማክረኛ ነበር፤ ይሁን እንጂ ሁሉንም ፈር ሳያስይዝ በድንገት ሞተ፡፡ ይህ ደግሞ በመጀመሪያ የሚጎዳው አንቺን ነው፤ ስለዚህ ጉዳዩ እንዲናልሽ ከፈለግሽ በጥብቅና ሙያዬ ልረዳሽና ፈር ላስይዝልሽ እችላለሁ» በማለት ቅንነት የሞላበትን ል ነገራት፡፡ እርሷም «ስለደግነትህ አመሰግናለሁ ከዕለታት አንድ ቀንም ጉዳዮቹን ፈር እንድታስይዝልኛ ውክልና እሰጥሃለሁ» አለችው፡፡

ጠበውም ጉዳዩን እንዳታዘገየው አጥብቆ ከነገራት በኋላ ሲሰናበታት «ግድ የለም በጥቂት ጊዜ ውስጥ እልክብሃለሁ» ብላ አሰናበተችው፤ ሆኖም ቀናት አለፉ፣ መልእክትም አልላከችበትም፤ ጉዳዩ ስላሳሰበውም ስልክ ደውሎ አነጋገራትና ጉዳዩን ቸል ሳትል በቶሎ እንድትጀምረው ገፋፋት፤ እርሷ ግን «ብዙ ቀጠሮዎች አሉብኛ፣ ለዛሬ አልችልም፤ እንደዚህ ለእኔ ስለተጨነክልኛ አመሰግናለሁ ከአንድ ሣምንት በኋላም እልክብሃለሁ» አለችው፤ እርሱም በልቡ አዝኖ ስልኩን ዘጋው፡፡ እንዲህ እያለ ብዙ ሳምንታት አለፉ፤ የሟቹ ባለቤትም ለጠበው መልእክት አልላከችበትም፡፡ ደግና በጎ አሳቢ የነበረው ጠበም ጉዳዩ አሁንም ስላሳሰበው በድጋሚ ስልክ ደውሎ «እመቤት ሆይ የቤታችሁ ጉዳይ ያለበትን አስቸጋሪ ሁኔታ ብታውቂ ዛሬውኑ ልታነጋግሪኛ በተገባሽ ነበር፤ ስለምን እንዲህ ቸላ ትይዋለሽ?» አላት፤ እርሷ ግን በገዛ ጉዳይዋ ላይ ከፍተኛ የሆነ ቸልተኛነት በማሳየት «ውይ! ዛሬማ ፈጽሞ የማይቻል ነው»

*ወደ ገጽ 15 የዞረ*

## ስለ ክርስቶስ ምን ትላለችሁ?

- ***ቅዱሳን መላእክት***፣ ስለ ክርስቶስ ምን ትላላችሁ?
    - እርሱ ሕዝቡን ከኃጢአታቸው ያድናቸዋል፤/ማቴ.1፡21/
    - የታረደው በግ ኃይልና ባለጠግነት ጥበብም ብርታትም ክብርም ምስጋናም በረከትም ሊቀበል ይገባል/ራ እ5፡12/
- ***ነቢያትስ*** ምን ትላላችሁ?

ሙሴ

«እግዚአብሔር ከወንድሞቻችሁ እንደ እኔ ያለ ነቢይ ያስነሣላችኋል፡ እርሱን ስሙት.. .. ያንን ነቢይ የማትሰማው ነፍስ ሁሉ ከህዝብ ተለይታ ትጠፋለች» /የሐ.ሥ 3፡22፣ 7፡37፣ዘዳ.18፡15-18/

ዳዊት

አምላክ ሆይ ዙፋንህ ለዘላለም ነው
የመንግሥትህም በትር የቅንነት በትር ነው፡፡
/መዝ.44፡6 ዕብ.1፡8/

አቤቱ አንተ ከጥንት ምድርን መሠረትህ
ሰማያትም የእጅህ ሥራ ናቸው
እነርሱ ይጠፋሉ አንተ ግን ትኖራለህ፤
ሁላቸው እንደልብስ ያረጃሉ
እንደመጐናጸፊያም ትለውጣቸዋለህ ይለወጡማል፤
አንተ ግን ያው አንተ ነህ፣
ዓመቶችህም ከቶ አያልቁም
/መዝ101፡25-27፣ዕብ1፡10-12/፡፡

እግዚአብሔር ጌታዬን ጠላቶችህን ለእግርህ መቀመጫ እስካደርግልህ ድረስ በቀኜ ተቀመጥ አለው /መዝ109፡1፣ ማቴ22፡41-46፣ የሐ.ሥ.2፡35፣ ዕብ.1፡13

ኢሳይያስ

«ሕፃን ተወልዶልናልና ወንድ ልጅም ተሰጥቶናልና፤ የሰላም አለ ተብሎ ይጠራል» /ኢሳ.9፡1-6፣ማቴ.4፡13-16/

ሚክያስስ?

«አንቺ ቤተልሔም ኤፍራታ ሆይ አንቺ በይሁዳ አእላፋት መካከል ትሆኚ ዘንድ ታናሽ ነሽ፤ ከአንቺ ግን አወጣጡ ከቀድሞ ጀምሮ ከዘላለም የሆነ፤ በእስራኤልም ላይ ገዥ የሚሆን ይወጣልኛል፡፡ /ሚክ.5፡2፣ማቴ.2፡5-6/

- ***ሐዋርያትስ*** ስለይሁድ ስለጌታ ምን መሰከራችሁ?

«እንግዲህ ይህን እናንተ የሰቀላችሁትን ኢየሱስን እግዚአብሔር ጌታም ክርስቶስም እንዳደረገው የእስራኤል ወገን ሁሉ በእርግጥ ይወቅ»/የሐ.ሥ.2፡36/፡፡

«መዳንም በሌላ በማንም የለም፤ እንድንበት ዘንድ የሚገባን ለሰዎች የተሰጠ ስም ከሰማይ በታች ሌላ የለምና /የሐሥ 4፡12/፡፡

«.....እናንተ በእንጨት ላይ ሰቅላችሁ የገደላችሁትን ኢየሱስን የአባቶቻችን አምላክ አስነሣው፤ ይህን እግዚአብሔር ለእስራሔል ንስሐን የኃጢአትንም ስርየት ይሰጥ ዘንድ ራስም መድኃኒትም አድርጎ በቀኙ ከፍ ከፍ አደረገው፡፡ እኛም ለዚህ ነገር ምስክሮች ነን ደግሞም እግዚአብሔር ለሚታዘዙት የሰጠው

**ጠበው.. ..** ከገጽ 14 የዞረ

አለችው፡ እርሱም እንደገና አዝኖ «ከዚህ ቀን ካለፈ ልረዳሽ የምችል አይደለሁም» አላት። እርሷም ጉዳዩን ቀለል አድርጋ በማየትና በጣም በመዘናጋት «አይ ምንም ችግር የለም በጥቂት ቀናት ውስጥ በሚመቸኝ ጊዜ እልክብሃለሁ» አለችው። ከሁለት ቀናት በኋላም አንድ ሰው መጥቶ «ለባለቤትሽ ይህን ያህል አበድሬው ነበርና በቶሎ ክፈይኝ» አላት፤ እርሷም ወዲያውኑ ቼክ ጽፋ ከባንክ እንዲ ወስድ ላከችው፤ ለካ የተዘናጋችው ባላት የገንዘብ አቅም ተማምና ኖሯል! ይሁን እንጂ በሚቀጥለውም ቀን ሌላኛው አበዳሪም መጥቶ ጠየቀ፤ ለእርሱም እንደ መጀመሪያው በቼክ ከፈለችው፤ ከዚህ ቀጥሎም ሁለት ሌሎች አበዳሪዎች መጡ፤ እነርሱ የጠየቁት ገንዘብ ግን እርሷ በባንክ ካላት ገንዘብ የሚበልጥ ስለ ነበር ልትከፍላቸው አልቻለችምና ከባድ ጭንቀት ውስጥ ወደቀች፤ በዚህን ጊዜ ነበር የባለቤቷ ወዳጅ የነበረው ደግ ጠበቃ ትዝ ያላት፤ ስለሆነም ወዲያውኑ እንዲ መጣ ላከችበት።

ጠበቃውም መልእክቱን ተቀብሎ በማግሥቱ ወደቤቷ በመምጣት ጉዳዩን ጠየቃት፤ እርሷም «አበዳሪዎች በዕዳ ስላስጨነቁኝ የማደርገውን ባጣ ታማክረኝ ዘንድ አስጠራሁህ» በማለት ነገረችው፤ ጠበቃውም እያዘነ «የላክሺብኝ በጣም ዘግይተሽ ነው፤ አሁን እኔ ጠበቃ አይደለሁም፤ በጥብቅና ሙያ ማገልገል አቁሜአለሁ፤ በምትኩም ዳኛ ሆኜ በዳኝነት ሥራ ላይ እገኛለሁ፤ ስለሆነም አሁን ለአንቺ በመከራከር ፈንታ በአንቺ ላይ የምፈርድ ነኝ፤ ዕዳዎችሽንም በሚገባ ስለማውቅ ልፈርድብሽ ብቻ ነው የምችለው» ሲል መለሰላት።

ይህ ታሪክ በሰውና በእግዚአብሔር መካከል ስላለው አሁን ለምእመናን አስታራቂ ሊቀካህናት ሆኖ በጠበቃነት ስለሚያገለግለው ስለ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ መጽሐፍ ቅዱስ ለሚናገረው እውነት ምሳሌ በመሆን ሊያብራራ ይችላል /1ጢሞ.2፡5፣ 1ዮሐ.2፡1-2/

***አንተም አንባቢ ሆይ***

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አሁን በመካከለኛነቱ የሚያገለግለው የጠበቃነት አገልግሎቱ አብቅቶ በፍርድ ዙፋን የሚቀመጥበት ጊዜ እንደሚመጣ ስለሚያውቅ አንተን ዕለት ዕለት በመልእክተኞቹ በኩል ወደ እርሱ እንድትመለስ ከእግዚአብሔርም ጋር እንድትታረቅ እየለመነህ ይገኛል /2ቆሮ.5፡19-20/። ፈራጅ ሆኖ ከመገለጡ በፊትም ከእግዚአብሔር ጋር ያለውን ጉዳይህን ፈር ሊያስይዝልህ ይፈልጋል። አንድ ነገር እወቅ፤ መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር በወሰነው ሰው በኩል በዓለም ላይ በጽድቅ ሊፈርድ ቀን እንደቀጠረ ይናገራል /የሐ.ሥ.17፡31/። ዛሬ አስታራቂህና ጠበቃ በመሆን ሊያገለግልህ የሚፈለገው ጌታ ኢየሱስ ነገ በሕያዋንና በሙታን ላይ የሚፈርድ ፈራጅ ነው/2ጢ //

---

# አዲስ ቅኔ ለበጉ ከተዋጁት

## አንተ ግን አንተ ነህ

አንተ ግን አንተ ነህ
መሳይ ተስተካካይ
እኩያ የሌለህ

ቢወረድ ቢወጣ ቢለፈፍ ቢነገር
ደግሞ ከተቻለም ቢኬድ ወደጠፈር
የሚመስልህ የለም በሰማይ በምድር

ማንነትህ ልዩ አንተነትህ ታላቅ
በሁሉ ላይ ገዢ ሁሉንም የምታውቅ
ዘመናት ያወቁሃል
ዓመታት ያውቁሃል
ታላቅነትህን ይናገሩልሃል
ይመሰክራሉ ክብርህን ሰማያት
ያደናንቁሃል የምድር ፍጥረታት
ዘወትር ይሉሃል ኢየሱስ ጌታ ነህ
ፍጹም ተመሳሳይ እኩያ የሌለህ»
በዘመናት ሁሉ አንተ ያው አንተ ነህ።

እኔም እልሃለሁ አንተ ግን አንተ ነህ
በሰማይ በምድር እኩያ የሌለህ
ድንቅ ድንቁን ሥራ ዛሬም ትሠራለህ
የሚሳንህ የለም ሁሉን ትችላለህ።

የፍጥረት ማጌጫ እውነተኛ ልብሱ
የእስትንፋሱ ጸጋ ክብርና ሞገሱ
የመክረም የመኖር የህይወቱ ዋልታ
በሰማይ በምድር አንተ ብቻ ጌታ።

አንተ ግን አንተ ነህ
መሳይ ተስተካካይ
እኩያ የሌለህ

ከሰማያት በላይ ዙፋንህ የሆነ
ስምህ ድንቅ መካር እጅግ የገነነ
ፍቅርህ በጣም ታላቅ ባንተ ለታመነ
መልስህ አስደናቂ አንተን ለለመነ።

ተራራ ኮረብታን በሚዛን የመዘንህ
አማካሪ የሌለህ ሁሉን ያስተካከልህ
ሰብስበህ የያዝከው የምድርን አፈር
የሁላችን ጌታ አንተ ነህ እግዚአብሔር

የሰማያት ውበት አምላክና ሠሪ
አልፋና ኦሜጋ ለዘላለም ኗሪ
ድምፅህ ጫካ ገላጭ ልህ የተሳለ
የፍርድ ነበልባል በእውነትህ ላልኖረ

በኃይልህም ችሎት አንድ ማይታጣ
በክብር ለክብር በጽድቅ የምትወጣ
አምባ ነህ መጠጊያ ጽኑዕ ማትደፈር
በሙላት የምትኖር በሰማይ በምድር

አንተ ግን አንተ ነህ
መሳይ ተስተካካይ
እኩያ የሌለህ

በእውነት ለእውነት በጽድቅህ የቆሙ
ለሚታመኑብህ ጸጋን የሚያትሙ
በዘመናት ብዛት በድካም ያልዛሉ
ደክሞ የወደቀን በክብር ያፅናኑ
እነዚያ ክንዶችህ ዛሬም ይሰራሉ
ዛሬም...............
ያጸናሉ
ዛሬም ...............
ያንፃሉ
የእውነትን ብሥራት ዛሬም ያውጃሉ
የአንተን አንተንነት ይመሰክራሉ።

ሰማይና ምድር ፍጥረታት በሙሉ
የምድር ኃያላን የተባሉት ሁሉ
ታዋቂ ዝነኛ አሉ የሚባሉ

---

## የሰገበግሎትህ ምክንያት ምንድነው?

የወንጌልን ሥራ ሙሉ ጊዜውን ሰጥቶ ያገለግል የነበረ አንድ አገልጋይ በግል ሥራው ይተዳደር የነበረውን አንድ ክርስቲያን «ጣያትን ለሚያመልኩ የአገርህ ሰዎች ወንጌልን ለመስበክ ትፈቅዳለህን?» ሲል ጠየቀው፤ ሰውየው የሚሠራው ጀልባ ላይ ተቀጥሮ ነበርና በየወሩ 30 ሺልንግ ያገኝ ነበር፤ ይህን ክርስቲያን ለማሰማራት የፈለገው የሙሉ ጊዜ አገልጋይ ግን «ልከፍልህ የምችለው 8 ሺልንግ ብቻ ነው፤ በዚህ 8 ሺልንግ መሄድ ትችላለህን? አለው። ክርስቲያኑ ሰውዬም ረዘም ላለ ጊዜ ተቀምጦ አሰበና «ለ8 ሺልንግ ስል መሄድ አልችልም፤ ነገር ግን ለክርስቶስ ስል መሄድ እችላለሁ» ሲል መለሰለት፤ የሙሉ ጊዜ አገልጋይ ነኝ የሚለውም ሰው በዚህ መልስ ተገርሞ እጁን በአፉ ላይ አኖረ።

ጳውሎስም በተመሳሳይ መልኩ እንዲህ አለ «እንግዲህ ደመወዜ ምንድር ነው? ወንጌልን እየሰበክሁ በወንጌል ካለኝ መብት በሙሉ እንዳልጠቀም ወንጌልን ያለዋጋ ብናገር ነው»/1ቆሮ.9፡18/።

**አንተስ አንባቢ?**

## ክርስቲያን

ከክርስቲያን መታወቂያዎች በጥቂቱ፤

*(ወደ ገጽ 6 የዞረ)*

# የአንባብያን  ዓምድ

«ተሰናአዉ ኵልክሙ እለ በክርስቶስ ሀሎክሙ» /1ጴጥ5፡14/::

«በክርስቶስ ላላችሁ ለሁላችሁ ሠላም ይሁን» /1ጴጥ5፡14/

## በዚህ ዓምድ ሥር ከአንባቢያን የሚደርሱን አስተያየቶችና ጥያቄዎች ይስተናገዳሉ፤

♦

በክርስቶስ ፍቅር የምንወዳችሁ ውድ አንባቢያን፤ ከሁሉ አስቀድሞ የእግዚአብሔር ጸጋና ሰላም ይብዛላችሁ እንላለን፤ ለአንባቢያን በከፈትነው በዚህ ዓምድ ከአንባቢያን ዘንድ ለእኛ ለአዘጋጆቹ የሚቀርቡና ለሌሎች አንባብያን የሚሆኑ አስተያየቶችና ጥያቄዎች እንዲሁም «እውነትን» የሚገልጡ መንፈሳዊ ጽሑፎችን እናስተናግዳለን፤ ስለዚህ አንባብያን በልባችሁ የሚሰማችሁን ሁሉ በግልጽነት እንድትጽፉልን እየጋበዝን በዚህ እትማችን ከደረሱን ደብዳቤዎች መካከል ያንጻሉ ያልናቸውን መርጠን እንደሚከተለ~~ው አትርበንላችኋ~~ል::

- ቀዳሚ ያደረግነው ከአሰላ ከተማ ከመምህርት ወይንሸት በቀለ የተላኩልንን 12 አስተያየቶችንና ጥያቄዎችን ነው፤

ለቦታ ቁጠባና ለተቀላጠፈ ቅንብር ሲባል ተመሳሳይ የሆኑትን አስተያየቶችና ጥያቄዎች በአንድ ላይ እየመደብን ለማሳጠር ሞክረናል፤ መምህርት ወይንሸትም ይህንን እንደምትረጅልን በመተማመን ጥየቄዎችሽንና አስተያየቶችሽን ቀጥሎ እናቀርባለን::

1. የ«እውነት ጋዜጣን» አዘገጃጀት የሚመለከቱት በደብዳቤው ውስጥ በተ.ቁ.1፣ 2፣ እና5 ላይ የሚገኙት ሲሆን እነርሱም የሚከተሉት ናቸው፤

- «እውነት የሚለው ስያሜ የተሰጠበት መሠረታዊ መነሻ የሆነው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጥቅስ አስፈላጊ ነበር፤ ቢታሰብበት፣
- በየሁለት ወሩ እንደሚወጣ ተገልጧል፤ ነገር ግን የመጀመሪያው እትም ቀኑና ወሩ ስላልተጠቀሰ አስተያየት ለመስጠትም ሆነ ለመጥቀስ ያስቸግራል::
- ጋዜጣውን በሁለት ዓምዶች ከፍላችሁ ቋሚና ወቅታዊ ስትሉ ምን ማለታችሁ ነው? የአንባብያን ዓምድስ ያላደረጋችሁት ለምንድነው?»

*ከአዘጋጆች፤* መምህርት ወይንሸት የጻፍሽልን እነዚህን ገንቢ አስተያየቶች.ሽን እጅግ ደስ ብሎን ተቀብለናል፤ እግዚአብሔር ይባርክሽ፤ በደብዳቤው መግቢያ ላይ «ለእውነት ቆማችኋልና የሚሰጣችሁን አስተያየት በትዕግሥትና በልበ ሰፊነት እንዲሁም በንቃት ለማንበብና ለማስተናገድ እግዚአብሔር በጎ ሕሊና ይስጣችሁ» ካልሽው ጋር በጣም ተስማምተናል፤ ልበ ሰፊ መሆን እንደሚገባን ከመጽሐፍ ቅዱስ ተምረናልና/ሐዋ.ሥ17፡11፣ 2ቆሮ7፡2/:: ስለሆነም «እውነት» የሚለው ቃል ለጋዜጣው ስያሜ እንዲሆን የተመረጠበትን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምክንያት በገጽ 2 የአዘጋጆች ስም ከተጻፈበት ከፍ ብሎ ባለው ስፍራ ሁል ጊዜም ተጽፎ እንዲወጣ አድርገናል፤ ባጭሩ ለመግለጽ «እውነት አርነት ያወጣችኋል» የሚለው ጥቅስ ለስያሜው መሠረት ሲሆን ጋዜጣዋም የመጽሐፍ ቅዱስን እውነት ብቻ የምትገልጥ በመሆኗ እውነት ተብላ ልትሰየም ችላለች፤ በየ2 ወሩ እንደሚታተም ተገልጦ የመጀመሪው እትም የወጣበት ወር አለመገለጡም ከዝንጋዔ የመጣ ስህተት ነው፤ 1ኛው እትም በሚያዝያ ወር 1993 ዓ.ም. የወጣ ሲሆን ይህንንም በዚህ እትም በገጽ 20 ላይ ገልጠናል::

**ወቅታዊ ዓምድ**

ስንል ወቅታዊ የሆኑ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መልእክቶችን በተለያዩ አርእስተ ጉዳዩች የምናቀርብበት ሲሆን፣

**ቋሚ ዓምዶች**

ስንል ደግሞ በቋሚ አርእስት ላይ /ለምሣሌ አገልግሎት፣ ቤተክርስቲያን፣ አምልኮ.. ../ የሚጻፉ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶችን የሚያስነብቡ ዓምዶች ማለታችን ነው:: የአንባብያን ዓምድ በቀዳሚው እትም ያልተካተተው የመጀመሪያውን እትም ካስነበብን በኋላ ከአንባብያን ደብዳቤዎች ሲደርሱን በ2ኛው ላይ እንጀምራለን ብለን ስላሰብን ነው፤ ስለዚህም እነሆ ይህ ያለንበት ዓምድ ሊጀመር ችሏል::

2. በተ.ቁ.3፣ 4፣6፣7 እና 8 ያሉት አስተያየቶችሽ ደግሞ የእኛን ያዘጋጆቹን ማንነት ለማወቅ ከሚፈልግ ኅሊና የመነጩ አስተያየቶች ናቸው፤ ጠቅለል ብለው ሲቀርቡም የሚከተለውን ይመስላሉ፤

- «ከየትኛውም የሃይማኖት ድርጅት ከመወገን የራቀች ናት» የሚለውና «በየ 2 ወሩ የሚወጣ የክርስቲያኖች ጋዜጣ» የሚለው ይጋጫል
- ዶክትሪናችሁ ምንድነው? ማለትም የእምነታችሁ መሠረታዊ ነጥቦች ምንድናቸው?

*ከአዘጋጆች፤* መጽሐፍ ቅዱስን የእግዚአብሔር ቃል ነው ብሎ ለሚያምንና በዚያም ላይ የተገለጠውን እውነት ሁሉ ለመቀበል ልቡ የሚሸነፍለት ሰው እርሱ የተባረከ ሰው ነው፤ እኅታችንም ለዚሁ የተዘጋጀ ልብ እንዳለሽ ተስፋ በማድረግ አስተያየቶችሽንና ጥያቄዎችሽን በተመለከተ የእግዚአብሔርን እውነት በኅሊናሽ ፊት እናኖራለን::

ጋዜጣው «*የክርስቲያኖች ጋዜጣ*» ስለተባለ «*ክርስቲያኖች*» የሚለው ቃል የሃይማኖት ድርጅት ስም አይምሰልሽ፤ አሁን የምንሰማቸው የየትኞቹም የሃይማኖት ድርጅት ስሞች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሉም:: ይህንንም ራስሽ በግልሽ ከዘፍጥረት እስከ ራእይ ያለውን ክፍል ጊዜ ሰጥተሽ በማንበብ ማረጋገጥ ትችያለሽ:: «ክርስቲያን» የሚለውን ቃል ግን ታገኛለሽ፤ ይህ ደግሞ የሃይማኖት ድርጅት መጠሪያ ሳይሆን በኢየሱስ የሚያምኑ ደቀመዛሙርት ለመጀመሪያ ጊዜ በአንጾኪያ የተጠሩበት ቃል ነው /የሐ.ሥራ.11፡26/:: ትርጉሙም የክርስቶስ ተከታዮች ማለት ነው:: ስለዚህ ጋዜጣዋ የክርስትናን እውነት ትናገራለች እንጂ በምድር ላይ ካለ የየትኛውም የሃይማኖት ድርጅት ከመወገን የራቀች ናት:: ክርስትና የሃይማኖት ድርጅት ሳይሆን በክርስቶስ ማመን ነውና::

ቤተክርስቲያንም በምድር ላይ ያለች ነገር ግን ሰማያዊ እውቅና ያላት የእግዚአብሔር ጉባዔ ናት እንጂ አሁን በብዙዎች እንደሚታሰበው የሃይማኖት ድርጅት አይደለችም፤ መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ቤተክርስቲያን ሲናገር የእግዚአብሔር ቤት/1ጢሞ.1፡16/፣ የክርስቶስ አካል /ኤፌ 1፡23/፣ የክርስቶስ ሙሽሪት/ኤፌ5፡24-32፣ራእ22፡17/ እያለ ሕያው የሆነች የምእመናን ጉባዔ እንደሆነች ይገልጣል እንጂ የሃይማኖት ድርጅት ናት አይልም:: እንዲህ ሲባል ግን አንድን መንፈሣዊ ሥራ ለመሥራት ክርስቲያኖች መደራጀት አይችሉም ማለት አይደለም፤ ይሁን እንጂ ምን ጊዜም ቢሆን ሥራን ለመሥራት ሲባል የሚፈጠር ድርጅት «ድርጅት» እንጂ ቤተክርስቲያን ሊሆን አይችልም፤ ቢ.ጂ.ኤን.ኤል.ጂ የሚለውም በዚሁ መልክ የቤተክርስቲያን ወይም የአንድ ቤተ እምነት (Denomination) ስም ሳይሆን ወንጌልን በሥነ ጽሑፍና በሌሎችም መንገዶች ለማሠራጨት የሚያስችል

*(ወደ ገጽ 17 የዞረ)*

## የአንባብያን

.. ..ከገጽ 16 የዞረ

የምድራዊ ቢሮ ስም ነው፤ እያንዳንዳችንም በክርስቶስ ደም ለተዋጀችው ለአንዲቱ ቤተክርስቲያን አባል /*የክርስቶስ ብልቶች*/ እንደመሆናችን መጠን ያለን እውቅናም ሰማያዊ ወይም መለኮታዊ እውቅና እንጂ ምድራዊ አይደለም፤ ስለማንነታችንም የምንለው የእግዚአብሔር ቃል ስለእኛ የሚለውን ብቻ ነው፤ በጋዜጣዋም ቢሆን «የተሰቀለውን ክርስቶስን እንሰብካለን» /1ቆሮ1:23/ እንጂ ድርጅትን አንሰጠብክም፤ ሐዋርያው ዳግመኛም «ክርስቶስ ኢየሱስን ጌታ እንደሆነ እንጂ ራሳችንን አንሰብክምና» እንዳለ እንደዚሁ የእግዚአብሔር አብ፣ የመንፈስ ቅዱስና የመጽሐፍ ቅዱስም ዋና አጀንዳ የሆነውን የጌታ ኢየሱስን ጌትነትና አዳኞነት ትተን ስለራሳችን ዛሬም ሆነ ወደፊት የማንሰብክ መሆናችን ይታወቅ።

ዶክትሪንን በተመለከተ መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስተምረውን ዶክትሪን እናምናለን። ይህም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ «*የክርስቶስ ትምህርት*»/2ዮሐ.9/ ወይም የሐዋርያት ትምህርት /የሐ.ሥ.2:42/ ተብሎ የሚታወቀው ነው። ይህም ትምህርት ስለአብ፣ ስለወልድና ስለመንፈስ ቅዱስ የሚናገርና ወልድ ማለትም የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው ሆኖ በሞቱና በትንሣኤው በስሙ የሚያምኑትን ማዳኑን የሚናገር ትምህርት ነው። ከዚህ በተረፈ ደግሞ ምድራዊና ድርጅታዊ ማንነትን ለማወቅ በሚፈልግ ስሜት ከመሞላት ይልቅ የክርስቶስን ማንነት ይበልጥ ለማወቅ በሚጓጓ ፍላጐት መሞላት ይበልጥ ይጠቅማል፤ የሰውና የድርጅት ማንነት ጠሚ ያልሆነ ብቻ ሳይሆን ጎጂም ሊሆን ይችላል፤ እኛ የምንፈልገው የእኛ ማንነት እንዲታወቅ ሳይሆን ተነግሮ የማያልቀው የክርስቶስ ማንነት እንዲታወቅ ነው። ይሁንና ለጥያቄሽ መልስ እንዲሆን መጽሐፍ ቅዱስ ስለክርስቲያን ትክክለኛ ማንነት የሚናገረውንና እኛም ስለማንነታችን ሁል ጊዜም የምንናገረውን ቃል በገጽ 2 ላይ «*መልእክተ እውነት*» የሚለውን ክፍል እድትመለከቺ በጌታችን ፍቅር እንጋብዛሻለን።

3. በተራ ቁጥር 9 እና በመጨረሻ በተጨማሪነት የሰጠሽው አስተያየት ደግሞ የጌታችን የኢየሱስን እናት ማርያምን ይመለከታል።

- «....ለማርያም ሰላም እንተ ተሳተፈት ስብሐተ እሉ» የገባችሁ አይመስለኛም፤ እግዚአብሔር ቢመሰገንና ቢወደስ ከዚህ የተነሣ ማርያም የምስጋናው ተሳታፊ ሆነች ቢባል ህፀፁ ምንድነው?
- «እኛ የተላክነው ስለኢየሱስ ለመመጠስከር እንጂ/የሐ.ሥ.1:8/ የእግዚአብሔር ምርጫ የሆነችውን እመቤት ልንዘልፍና ልናንቋሽሽ አይደለምና አስቡበት የሚል አስተያየት ነው።

*ከአዘጋጆች፡-* እኅታችን ወይንሸት «አምልኮት» በሚለው ዓምድ ውስጥ የተጻፈውን እውነት በትዕግሥትና በጥሞና አንብበሽ ስላቀረብሽው ጥያቄ አዘል አስተያየት ደስ ብሎናል። እግዚአብሔር ይባርክሽ።

የነግሥ ደራሲ «ለማርያም ሰላም እንተ ተሳተፈት ስብሐተ እሉ» ሲል አንቺ እንዳሰብሽው እንዳልሆነ ለመረዳት ልብሽን እንደምታሰፊ ተስፋ እያደረግን በዚህ ርእስ ላይ ጥቂት ማብራሪያ ልናክልልሽ እንወዳለን። «በተስፋ ቃል የመለኮት ባሕርይ ተካፋይ ናችሁ» የሚለውም ጥቅስ የጌታ እናት ከሥላሴ ምስጋና ተሳታፊ እንደሆነች በጥቂቱም እንኳ የማያመለክት ነውና አንድን ጥቅስ ከሚናገረው ውጪ የልባችንን መሻት እንዲመሰክርልን ማድረጉ አግባብ አለመሆኑን እንድትረጂ እናሳስብሻለን። እርግጥ በኢየሱስ የሚያምኑ ሰዎች /ክርስቲያኖች/፣ ሁሉ ሐዋርያው ጴጥሮስ እንዳለው በተስፋ ቃል የመለኮት ባሕርይ ተካፋይ ናቸው/2ጴጥ1:4/። በዚህ ረገድ የጌታን እናት ማርያምን የተለየ የሚያደርጋት ነገር በዚህ ቃል ውስጥ የለም፤ ሆኖም የጌታችን እናት ማርያም ከመጀመሪያዎቹ አማኞች ጋር በጸሎት ትተጋ የነበረች የመጀመሪያይቱ ቤተክርስቲያን አባል በመሆኗ እርሷም በተስፋ ቃል ከመለኮት ባሕርይ ተካፋይ ሆናለች። ይህ ግን ደራሲው እንዳለው ከሥላሴ ጋር የስብሐት /ለአምላክ ብቻ የሚቀርብ ምስጋና/ ተሳታፊ /ተካፋይ/ አያደርጋትም፤ ከጴጥሮስ መልእክት የተጠቀሰው ቃልም የመለኮት ባሕርይ ተካፋይ ይላል እንጂ የመለኮት ክብር ተካፋይ እንደማይል ማስተዋል ይገባል፤ ክብሩን በተመለከተ እግዚአብሔር «ክብሬን ለሌላ ምስጋናዬንም ለተቀረፁ ምስሎች አልሰጥም» ብሎ የተናገረውን የተገለጠ ቃል ልብ ብለሽ አንብቢው/ኢሳ42:8/። እንደዚሁም ጴጥሮስ «የመለኮት ባሕርይ ተካፋይ እንድትሆኑ» ሲል በተስፋ ቃል መሆኑን መገንዘብ ያሻል፤ እንዲያውም ሙሉውን ምንባብ ብንመለከት «ከመለኮት ባሕርይ ተካፋዮች በተስፋ ቃል እንድትሆኑ በእነዚያ ክብርና በጎነት የተከበረና እጅግ ታላቅ የሆነ ተስፋን ሰጠን» ይላል። ስለሆነም ክርስቲያን በአሁን ጊዜ የመለኮት ባሕርይ ተካፋይ ነኝ ሲል በተስፋ መሆኑን አስምሪበት። ከዚህ ተነስቶ ግን ማርያም ከሥላሴ ክብር /ስብሐት/ ተሳታፊ ናት ማለት እጅግ ታላቅ ህፀፅ ነው። ለማርያም ሰላም እንተ ተሳተፈት ስብሐተ እሉ» የሚለውን ድርሰት ትክክለኛ ትርጉም ግእዝን በትክክል ከሚያውቅ ሰው ለመረዳት ሞክሪ፤ ምንም ሳይሸራርፍና ሳይሸፋፍን በሐቀኛ ኅሊና የሚተረጉምልሽ ግእዝ ዐዋቂ ካገኘሽ «አልገባችሁም» ያልሽን አባባል ምን ያህል እንደገባን አንቺው መፍረድ ትችያለሽ። ለጊዜው ግን ደግመን እንተርጉምልሽ። «እሉ» ማለት «እነዚህ» ማለት ነው፤ «እነዚህ» የሚላቸውም ቀደም ብሎ የገለጣቸው አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ናቸው /ሙሉ ሉን እንደገና ተመልከቺ/። ስለዚህ «ለማርያም ሰላም እንተ ተሳተፈት ስብሐተ እሉ» ማለት «የእነዚህን /የሥላሴን/ ስብሐት /ክብር/ ለተሳተፈች ለማርያም ሰላም ይሁን» ማለት ነው፤ ታዲያ ይህ ፍጡር የሆነችውን ማርያምን ወደ ፈጣሪ ተርታ ለማስገባት የመሞከር ያህል ድፍረት አይደለም ትያለሽ? ማርያምስ ይህን እንዴት ትጸየፈው !

- እኅት ወይንሸት አንድ ነገር በእርጋታ ለማሰላሰል ልብሽን አስፊ፡-

በጌታችን በኢየሱስ እናት በማርያም ስም የተጻፉና የሚዜሙ እንዲሁም በየመድረኩ የሚነገሩ የእግዚአብሔርን እውነት የሚፈሩ አባባሎችን በእግዚአብሔር ቃል መግለጥና ምእመናን ካላስተዋሉት መናፍቅነት እንዲላቀቁ ማድረግ ምን ያህል የተወደደ እንደሆነ አንቺም ራስሽ እውነቱን ከቅዱስ መጽሐፍ መርምረሽ በመንፈስ ቅዱስ እገዛ የተገነዘብሽው ዕለት በሚገባ ትረጂዋለሽ። የኢየሱስ እናት ማርያምን በተመለከተ የእግዚአብሔር ቃል መጽሐፍ ቅዱስ በሚሰጣት ተገቢ ሥፍራ ማስቀመጥ ዘለፋ እንዳልሆነ በቅንነት ማሰብ እንድትችዪ ጌታ ይርዳሽ። እርስዋ ጸጋን የተሞላች፣ በእግዚአብሔር ፊት ሞገስን ያገኘች፣ ቡርክት /የተባረከች/ እና ብፅዕት የሆነች፣ የጌታችን እናት መሆኗን መጽሐፍ ቅዱስ በግልጥ ይነግረናል/ሉ1/። የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ከእርስዋ ተወልዶ ዋነኛ የማዳን ሥራውን የሠራው በመስቀል ላይ ነበር፤ እርሱ ከሞተና ከተነሣ በኋላ የጌታ እናት እንደማንኛውም ክርስቲያን በጸሎትና በምእመናን ጉባዔ እየተሳተፈች እንደኖረች ይታወቃል፤ ሰው ናትና ዕድሜዋ ሲደርስ እንደማንኛውም ሰው ሞታለች፤ ይህን ሁሉ እውነት ማንም ሊክድ አይችልም፤ ጌታ የሰውን ሥጋ ለብሶ ለመገለጥ በማርያም መገልገሉ እርግጥ ነው፤ ለዚህም ተፈጻሚነት የተመረጠችበት ዋናው ምክንያትም የእግዚአብሔር ጸጋ ብቻ ነበር፤ ሌሎች የእግዚአብሔር ባሪያዎች በጸጋ ተመርጠው የእግዚአብሔርን ምክር

(ወደ ገጽ18 የዞረ)

## የአንባቢያን .. ከገጽ 17 የዞረ

አገልግለው እንዳለፉ ሁሉ እርሷም የጌታ እናት የመሆን አገልግሎቷን ፈጽማ አልፋለች፤ ስለሆነም ጌታ ኢየሱስ እስከዓለም ፍጻሜ ድረስ ለሚነሱ የሰው ልጆች አዳኝና መካከለኛ እንደሆነው አይነት እርሷ ከወለደችው በኋላ ብሎም ከሞተች በኋላ በአንድ ኃጢአተኛ መዳንም ሆነ በአንድ አማኝ የክርስትና ሕይወት ውስጥ ወሳኝነት የላትም፤ በክርስቲናዊ ሕይወቷ /ለጸሎትና ለሉ ባላት ትጋት እና በትህትናዋ/ ምሳሌ ከምትሆነን በቀር ጌታ የሚያስፈልገንን ያህል ዘላለማዊ አስፈላጊነት የላትም:: ይህንን የማይስማሙት ነገሩን በቀናነት መመለከት የተሣናቸው ሰዎች ናቸው እንጂ እርሷ ግን ነገር ሁሉ በልጇ በኢየሱስ ብቻ ሲጠቀለል የምትደሰት ለመሆኗ ጥርጥር የለውም:: «የሚላችሁን ሁሉ አድርጉ»/ዮሐ.2፡5/ ብላ በሠርግ ቤት የተናገረችው ቓ ለዚህ ዘመን ምእመናንም ኃይል ያለውን ድንቅ መልእክት ያስተላልፋል፤ ሳይረዳ በስሟ የሚከራከር ኅሊናንም በቀላሉ ይረታል!!

በተጨማሪም የምንልሽ ቢኖር በኢየሱስ ደም የነጻ ኅሊና ያለው ሰው እንኳን የጌታችን የኢየሱስን እናት ማርያምን ቀርቶ ሌሎችንም ቅዱሳንን /ምእመናን/ እንዲሁም የማያምኑ ሰዎችንም ጭምር እንዲዘልፍና እንዲያንቋሽሽ የነጻ ኅሊናው አይፈቅድለትም፤ አንቺ አስተያየት ለመስጠት ብለሽ «መዝለፍና ማንቋሸሽ» የሚሉትን ቓት ስትጠቀሚ ምን ያህል ኅሊ ናችንን እንደሰቀጠጠን ሳንነግርሽ አናልፍም:: በመሠረቱ ባነበብሽ ምንባብ ውስጥ የጌታን እናት በተመለከተ አንቺ ያልሽውን አልጻፍንም፤ ከምን ትነስተሽ እንዲህ ያሉ ቓትን እንደተጠቀምሽ ራስሽን ብትጠይቂ መልካም ይሆንልሻል:: በተረፈ በእግዚአብሔር ቓ ስለቅድስት ማርያም ከተጻፈው ያለፈ ላለማሰብ በኅሊናሽ መወሰን እንድትችዪ ጌታ በጸጋው ይርዳሽ::

4. «አዲስ ቅኔ ለበጉ» ከሚለው ንዑስ ዓምድ «ኢየሱስ ለእኔ» ከሚለው ግጥም ውስጥ የሚከተለውን አስተያየት አቅርበሻል፤

ጌታ ከስም በላይ የሆነውን ስም ተቀብሏል/ፊልጵ2፡9-11/፤ ስለዚህ «ማን ልበልህ ስያሜ አጣሁልህ...ወዘተ» ማለቱ በጣም ከፍተኛ ስህተት ነው ይላል::

*ከአዘጋጆቹ፤* «እምነትና በጎ ኅሊና» ካለ የግጥሙን አባባል ለመረዳት አያስቸግርም:: ገጣሚው ለጌታ የተቀኘበትን ርእስ ብትመለከቺው «ኢየሱስ ለእኔ» የሚል ነው:: ስለዚህ የጌታ ስሙ «ኢየሱስ» መሆኑን የዘነጋው ይመስልሻልን? እኅት ወይንሸት አባባልሽ ፀጉር መሰንጠቅ አይሆንምን? እስኪ በትህትናና በፍቅር ለማሰብ ዘንበል በይ «.. .. ስለበዛብኝ ውለታህ፣ ጌታዬ ሆይ ማን ልበልህ? ስያሜ አጣሁ ለአንተነትህ?» ካለ በኋላ «ቓ የለኝም የሚገልጠህ፣ ..ሁሉንም ነህ የኔ ጌታ» ያለውን ልብ ብትይው ገጣሚው ለኢየሱስ ስለውለታው ያቀረበውን ከፍ ያለ አድናቆት ከማሰብ አልፈሽ አትሄጂም ነበር፤ የጌታ እናት ፍጡር ስለሆነች ከሥላሴ ስብሐት ትሳተፍ የሚለው ድርሰት ስህተት ነው መባሉ ቀር አሰኝቶሽና በሥላሴ ምስጋናም እንድትወደስ እየፈለግሽ በሌላ በኩል ደግሞ «በረከትና ክብር፣ ምሥጋናም ኃይልም፣ ከዘላለም እስከዘላለም በዙፋኑ ላይ ለተቀመጠው ለበጉ ይሁን» እያለ «በሰማይና በምድርም፣ ከምድርም በታች በባሕርም ላይ ያለ ፍጥረት» /ራእ5፡13/ ሁሉ የሚያመልከውን ጌታ ባለቅኔው «ስለበዛብኝ ውለታህ፣ ጌታዬ ሆይ ማን ልበልህ? ስያሜ አጣሁ ለአንተነትህ ..ሁሉንም ነህ የኔ ጌታ» እያለ ቢያመሰግን ለምን ቅሬታ ገባሽ? ማርያም ስትመለክ ደስ ብሎሽ የታረደው በግ ሲመሰገን ለምን እንዳዘንሽ፣ ማርያምን ከፈጣሪ ምስጋና ተሳታፊ ማድረጉ ህፀፅ አልባ ሆኖ ኢየሱስን ማወደሱ ለምን ህፀፅ እንደሆነብሽ ራስሽን ብትጠይቂ መልሱ እንደማይጠፋሽ እምነታችን ነው:: ስለዚህ ዳግመኛ ግጥሙን ጌታ ከዋለልሽ ውለታ አኳያ አንብበሽ ደስ

(ወደ ገጽ 20 ይዞራል)

## አገልግሎት .. ..ከገጽ 12 የዞረ

### ቅዱስ መሥዋዕት

ሦስተኛው የመሥዋዕት ጠባይ ቅዱስ መሆኑ ነው:: ቅዱስ ማለትም እንደ ግሪኩ ቓ ከሆነ ለእግዚአብሔር የተለየ ማለት ነው:: ከዚህም አንጻር የአገልጋይ ሰውነት ቅዱስ መሥዋዕት ሊሆን የሚችለው አገልጋዩ ከማናቸውም እግዚ አብሔር ከሚጠላቸው ሐሳቦች፣ ድርጊቶችና ኀብረቶች ራሱን ሲለይ ነው:: ይህንንም ሐሳብ ይበልጥ በዚያው በሮሜ 12 ቁጥር 2 ላይ «የእግዚአ ብሔር ፈድ እርሱም በጎና ደስ የሚያሰኝ ፍጹምም የሆነው ነገር ምን እንደሆነ ፈትናችሁ ታውቁ ዘንድ በልባችሁ መታደስ ተለወጡ እንጂ ይህን ዓለም አትምሰሉ» ተብሎ ተብራ ርቶ እናገኛለን:: ቅድስናን ማጣት ማለትም እግዚአብሔርን የምት ጠላውን ዓለምን መምሰል ማለት ነው:: በእርግጥ ጌታውን የተከተለና እርሱ እንደተመላለሰ በሑና በኑሮው የሚመላለስ ዓለምን ሊመስል አይችልም:: ዓለምን አለመምሰል ማለት ደግሞ ራስን ከዓለማዊ አካሄድና ጠባይ መለየት ነው፤ ለእግዚአብሔር መሥዋዕትነት ራሱን የሰጠ ለዓለም፣ ለሥጋና ለሰይጣን መሥዋዕት ሊሆን አይችልም፤ ሙሉ በሙሉ ለእግዚአ ብሔር መለየት ማለትም ሙሉ በሙሉ ከዚህ ከኃጢአተኛው ዓለም በኑሮና በአስተሳሰብ መለየትን ያሳያል:: ዓለም በአካሄዷና በእያንዳንዱ ተግባርዋ ለእግዚአብሔር ያላትን ጠላትነት በመግለጥ ላይ ትገኛለች/ያዕ4፡4/:: እግዚአብሔርም በዓለም ላይ ፍርድን ሰጥቷል:: ስለሆነም አገልጋይ ለእግዚ አብሔር የተሰጠውን ያህል ከዓለም ይለያል፤ ለጽድቅ የቆመውን ያህል ዓመፀኛነትን ይፀማል፤ እውነትን የሚወደውን ያህል ሐሰትን ይጠላል:: እግዚአብሔርን መውደድ ብቻውን በቂ አይደለም፤ በተጨማሪም ኃጢአትን መጥላት ይገባል:: እግዚአብሔር የሚወደውን መውደድና ያንንም ማድረግ ብቻውን በቂ አይደለም፤ እግዚአብሔር የሚጠላውን መጥላት ከእርሱም መራቅና መለየት ይገባል:: እንደዚህ ያሉ አገልጋዮች በእርግጥ «በጎና ደስ የሚያሰኝ ፍጹምም የሆነው የእግዚአብሔር ፈድ» ምን እንደሆነ ፈትነው የማወቅ አቅም አላቸው:: በዚህ የእግዚአብሔር ፈድ እውቀትም ስለሚመሩ ከስህተት፣ ከፀፀትና ከውድቀት የተረፉ ናቸው:: የጌታ ኢ የሱስ አገልግሎት ሁለትዮሽ ነበር፤ ዓመጻን ይጠላል፣ ጽድቅን ይወዳል፤ እውነትን ይደግፋል፣ ሐሰትን ይፀማል፤ የሚታዘዙትን ያበረታታል፣ የማይታዘዙትን ይገሥጻል:: የእኛም አገልግሎት እንዲሁ መሆን ሲገባው «ተባረክ» የሚል ምርቃት የሚያሰጠውን ብቻ የሚሰብኩና እግዚአብሔርን የሚያሳዝን ሆኖ እያለ ቢናገሩት ግን ነቀፋ የሚያመጣውን ችል የሚሉ፣ ተሰባኪውን ስለበጎ ነገሩ የሚያቆላምጡ ስለነውሩ ግን ግድ የማይላቸው ሰዎች ምስክርነታቸው አንድ እጅ ብቻ ነውና አገልግሎታቸው ቅድስና የጎደለው ነው:: ዓለምን መምሰል ማለትም ይኸው ነው:: መጥምቁ ዮሐንስ «ከእኔ በኋላ የሚመጣ ከእኔ ይበልጣል» እያለ ብቻ ቢሰብክ ኖሮ ሕይወቱን በምድር ላይ ማሰንበት ይችል ነበር፤ ሆኖም ይህ ምስክርነት ብቻውን በቂ ስላልነበረ የጌታውን መንገድ በመከተል በዘመኑ ይደረግ የነበረውን ኃጢአት በመፀሙ/ሉ3፡18-20/ ሰውነቱን «ቅዱስ መሥዋዕት» አድርጎ ለማቅረብ በ፦ ወደዚህ ዓይነቱ አገልግሎት ለመድረስ እንድንችል እግዚአብሔር ይርዳን አሜን::

■

## ከተመሠረተው.. ከገጽ 10 የዞረ

ብዙም ሳይቆዩ ከወጡበት ቦታ ባላነሰ በሌላ ስህተት ከመዋጥ አላመለጡም:: በእርግጥ በመጀመሪያ የነበሩበት ስፍራ የተሳሳተ መሆኑን መገንዘባቸውና ከዚያም ለመለየት ተግባራዊ ምላሽ መስጠታቸው «የጌታን ስም የሚጠራ ሁሉ ከዓመፅ ይራቅ»/2ጢሞ2፡19/ የሚለውን ቅዱስ መርህ መከተላቸው ነውና ሊያስመሰግናቸው ይገባል:: ሆኖም ግን ከዚያ ከወጡ በኋላ «በሰው ጥበብ» ሳይሆን «መንፈሳዊውን ነገር ከመንፈሳዊው ነገር ጋር እያስተያዩ መንፈስ በሚያስተምራቸው ቃል»/1ቆሮ2፡13/ በመመራት «በንጹሕ ልብ ጌታን ከሚጠሩ ጋር ጽድቅን፣ እምነትን ፍቅርን፣ ሠላምን አጥብቀው መከተል»/2ጢሞ2፡22/ ይገባቸው ነበር፤ በንጹሕም ልብ ጌታን የሚጠሩ በዙሪያቸው ከሌሉ ደግሞ «ሁለት ወይም ሦስት ሆነው በጌታ በኢየሱስ ስም» ብቻ መሰብሰብ ይገባቸው ነበር:: ሆኖም አስቀድመው ከክፉ ለመራቅ የሞከሩትም ሆኑ አሁንም እየሞከሩ ያሉት ከሞላ ጎደል በአንድነት በታሪክ ውስጥ የፈጸሙትና እየፈጸሙት የሚገኘው ስህተት ከላይ የተገለጠውን በማድረግ ፈንታ ከስህተት አሠራር ሲወጡ ግንባር ቀደም ሆነው በመሯቸው መሪዎች ዘንድ ራእይ እየጠተባሉ በሚጠሩ የግል አመለካከቶች ዙሪያ ወይም በወቅቱ ጎልቶ በታያቸው አንዳች እውነት ላይ ተመሥርተው ለወጡበት የእምነት ድርጅት ተፎካካሪ የሚሆን አንጻራዊ ድርጅት በምድር ላይ መገንባት ነው:: የሚመሠርቱትንም ማህበር ደግሞ እንደ ቆሮንቶስ ሰዎች የጴጥሮስ ወይም የአጵሎስ ወይም ...ባይሉትም ልባቸውን የሞላ ወይም ልባቸውን ደስ ያሰኘ መንፈሳዊ እውነትን የሚገልጥ ቃል ከመጽሐፍ ቅዱስ ሲያገኙ በዚያ ቃል «እገሌ ቤተክርስቲያን» ብለው ይሰይሙታል፤ ከዚህ ላይም ምንም ያህል በእጅጉ ክቡርና የሚናፈቅ ቢሆንም ስለጌታ ምጽአት የሚናገረው እውነት በአንድ ወቅት ለእኛ ጎልቶ ስለታየን ብቻውን ክርስቶስን ተክቶ የማህበር መሠረት ሊሆንና «የምጽአት ቤተርስቲያን» የሚሰኛ ቤተክርስቲያን እንድንመሠርት አያስችለንም፤ እንደማንኛውም የወንጌል እውነቶች ሁሉ የቅድስናም ሆነ የጥምቀት እውነት ወይም የመንፈስ ቅዱስና የጸጋ ስጦታ እውነት ወይም የብርሃን እውነት ወይም የትንሣኤ እውነት በራሱ የተወደደ ቢሆንም ክርስቶስን ተክቶ የቤተክርስቲያን መሠረት ሊሆን አይበም፤ በሌላ በኩል ደግሞ በመለያየት፣ በጥላቻና በሰው ሠራሽ ሐሳብ ላይ የመሠረቱትን ማህበርም «የክርስቶስ ቤተክርስቲያን» የሚል ስያሜ ቢሰጡትም የክርስቶስ ቤተክርስቲያን ሊሆን እንደማይችል ሊታወቅ ይገባል፤ ምክንያቱም የክርስቶስ ቤተክርስቲያን ከክርስቶስ ሞት የተገኘች እንጂ በሰው ስያሜ የምትመጣ መለያየትም የሚወልዳት አይደለችምና:: ቤተክርስቲያን ክርስቶስ ባቀረበው መሥዋዕትነት መሠረት በበዓለ ሃምሳ ዕለት በርደተ መንፈስ ቅዱስ ተመሥርታለች፤ ዛሬ ሌሎች ስላስቀየሙን ወይም አስቀድሞ በሚገባ ያልተብራራ አንድ እውነት ለእኛ ስለተብራራልን ወይም በአንድ ስፍራ ቀድሞ ያላመኑ ሰዎች አግኝተን ልንመሰክርላቸው ስለቻልንና ስላሰባሰብናቸው ቤተክርስቲያን አትመሠረትም፤ ያላመኑ አዳዲስ ሰዎች በክርስቶስ ሲያምኑም ሆነ ባለማወቅ በተሳሳተና ሰው ሠራሽ በሆነ የክርስትና ሃይማኖት ውስጥ የነበሩት ሰዎች በነበሩበት ክፉት ላይ ነቅተውበት ራሳቸውን ከዚያ ዓመፃ ሲለዩ በትክክል እንዲሆን እግዚአብሔር የሚፈልገው ቀድሞ ወደ ተመሠረተችውና የክርስቶስ አካል ወደሆነችው አንዲት ቤተክርስቲያን ብልት ሆነው እንዲጨመሩና ክርስቶስ ራስ እንዲሆናቸው ነው እንጂ በአንዳች ስም አዲስ ወይም ሌላ ቤተክርስቲያን እንዲመሠርቱ ወይም ቀድሞ ለተመሠረተ የሃይማኖት ድርጅት ቅርንጫፍ እንዲሆኑ አይደለም:: ነቢያትና ሀዋርያት በትምህርታቸው በመሠረቱት መሠረት ላይ አዳዲስና ከዓመፃ የሸሹ ምእመናን ህያዋን ድንጋዮች እየሆኑ እየተጨመሩ ያው የዛሬ ሁለት ሺህ ዓመት ገደማ የተጀመረው ሕንጻ በማዕዘኑ በኢየሱስ ክርስቶስ እየተጋጠመ ያድጋል እንጂ አዲስ ሕንጻ አይሠራም/ኤፌ2፡20-22፣1ጴጥ2፡5/:: ከዚህም አኳያ ሲታይ አሁን በሰው ልጆች በምድር ላይ እየተሠራ ያለው እንደእግዚአብሔር ቃልና እንደጌታ ልብ አለመሆኑ የቅንጣት ያህል አያጠራጥርም፤ ምክንያቱም አዲስ ህንጻ የሚሠሩ ሁሉ አዲስ መሠረት ይጥላሉና:: እንዲህ ዓይነቱ እንቅስቃሴም ምንጩ ሥጋዊነት ከመሆኑም ባሻገር ጉዳቱም ከልክ ያለፈ ነው፤ በመጀመሪያ ደረጃ እነዚህ ሰዎች የሚጥሉት መሠረት ራሱ ክርስቶስ ስላልሆነ በዚያ ላይ የሚሰባሰቡት ሰዎች የተመሠረቱት በሕያው አለት ላይ አይደለምና በመካከላቸው የሚነሣው ጥቂቱ ክርክር ለታላቅ መለያየት ስለሚያበቃው እንደገና ለሌላ መከፋፈል ይዳረጋሉ:: አሁንም ከተከፈሉ በኋላ በንስሐ ወደ እውነተኛው መሠረት በመመለስ ፈንታ በያዟቸው አቋሞች ላይ ስለሚመሠረቱ በድጋሚ እነርሱም ለሌላ መከፋፈል ይጋለጣሉ፤ እንግዲህ አሁን በምድር ላይ በክርስትና ስም የሚጠራው ሃይማኖተኛው ዓለም የዚሁ የሥጋዊነትና የእውነተኛውን መሠረት የመሳት ውጤት ነው:: በሁለተኛ ደረጃ ይህ ክርስቲያኖች ነን በሚሉ ሰዎች መካከል የሚካሄደው መለያየት ከሚሰብኩት የፍቅር አምላክ ባሕርይ ጋር ስለማይጣጣም ስለ ክርስትና የሚሰጠው ምስክርነት ይደክማል፤ ስለሆነም እነዚህ ሰዎች በየጊዜው የሚፈጠረውን ክርክራቸውን በጌታ ፍቅር እየፈቱ ወደ ጌታ በመመለስ ፈንታ አገልጋዮቻቸውን እየተከተሉ ለሥጋዊ ምክንያት በማያባራ መለያየት ውስጥ ተዘፍቀው የተከፈሉት ሲከፈሉ እነዚያም ሲከፈሉ እንዲህም እያሉ በመከፋፈል «ምድርን እየሞሉ» ስናይ የክርስቶስ ልብ ምን ያህል እንደሚያዝንና ስለእርሱ የሚሰጠውም ምስክርነት ምን ያህል እየጎደፈ እንደሆነ ለመገንዘብ አያዳግትም:: በሦስተኛ ደረጃ ደግሞ ይህ ድርጊታቸው በጌታ ፊት ተጠያቂ ያደርጋቸዋል፤ «የጌታን ስም የሚጠራ ሁሉ ከዓመፅ ይራቅ» ከሚለው መለኮታዊ መመሪያ ውጪ በልዩ ልዩ ምድራዊና ሥጋዊ ምክንያቶች ቡድናዊነትን እየፈጠሩ የክርስቶስን መንጋ ከፋፍለው በራሳቸው መሠረት ላይ እንደ አዲስ የሚያንጹ ሁሉ የእግዚአብሔርን ቤተመቅደስ እያፈረሱ እንደሆነ ቢያውቁ ምንኛ ፈጥነው ንስሐ በገቡ! «ማንም የእግዚአብሔርን ቤተመቅደስ ቢያፈርስ እግዚአብሔር እርሱን ያፈርሰዋል፤ የእግዚአብሔር ቤተመቅደስ ቅዱስ ነውና ያውም እናንተ ናችሁ»/1ቆሮ3፡17/ የሚለውንስ አላነበቡም ይሆንን? ሰው ሁል ጊዜ የእግዚአ ብሔርን ሐሳብ ወደጎን በመተው «ቤተክርስቲያን» ብሎ የሚጠራውን በራሱ ሐሳብ ከመገንባት አላረፈም፤ ሲሻው በገዛ እጁ የጠረበውንና የገነባውን የድንጋይና የእንጨት ቤት «እገሌ ቤተክርስቲያን» እያለ ይጠራዋል፤ ሲሻው ደግሞ በራሱ ሐሳብ ላይ የመሠረተውንና «እገሌ» ብሎ የሚሰይመውን ድርጅት «እገሌ ቤተክርስቲያን» ብሎ ይጠራዋል፤ የማይቻለው ሆኖ እንጂ ሌሎቹንም ቢጤዎቹን ውጦ ምድር ሁሉ በእርሱ «እገሌ ቤተክርስቲያን» ብትሞላ ምኞቱ ነው፤ ቢቻለው ሰማይ ላይም «አጥቢያ» ወይም «ቅርንጫፍ» የሚለውን ከፍቶ ሁሉንም በጠቀለለ ምኞቱ ነው:: ሆኖም ግን አንባብያን እዚህ ላይ ሊያውቁት የሚገባው ቁም ነገር እነዚህ በዚህ መልኩ የሚፈጠሩ ሁሉ «ቤተክርስቲያን» ተብለው ቢጠሩም መሠረታቸውን የሳቱ መሆናቸውን ነው:: መሠረቱን የሳተ፣ በክርስቶስ ሁለንተናዊ ማንነት ላይ ሳይሆን በውስን አመለካከቶች ላይ የቆመና ለራሱ ስምን የሰየመ የክርስትና እምነት አራማጅ ነኝ የሚል የእምነት ድርጅትም ቢሆን «ድርጅት» እንጂ ቤተክርስቲያን አይደለም::

ስለሆነም በመጀመሪያም ሆነ ዛሬ ጠላት

> የክርስቶስ ቤተክርስቲያን ከክርስቶስ ሞት የተገኘች እንጂ በሰው ስያሜ የምትመጣ መለያየትም የሚወልዳት አይደለችም::

*(ወደ ገጽ 12 ይዞራል)*

**የአንባቢያን..** ከገጽ 18 የዞረ

እንድትሰኚበትና አንቺም ሌላ አዲስ ቅኔ እንድትቀኚለት ጌታ ይርዳሽ::

5. በአስተያየትሽ መጨረሻ የለገስሽንን የማበረታቻ አስተያየት ደግሞ ቀጥሎ እናቀርባለን::

«እውነትን በእውነት ከያዛችሁ እንደ ጌታ ኢየሱስ፣ እስከ መስቀል ሞት እስከ መቃብር በመዝለቅ በእውነት ወንጌል ወደፊት በመራመድ እውነተኛ ማንነታችሁን ለማሳየት መጣር ይ ጠበቅባችኋል፤ ኢየሱስ ነፍሱን ለእውነት አሳልፎ ከሰጠ በኋላ «ይህ በእውነት የእግዚአብሔር ልጅ ነው» እንደተባለለት የእናንተም እውነት ምናልባት እውነት ከሆነ የሚገለጠው እናንተ ከተሠዋችሁ በኋላ ሊሆን ስለሚችል ተስፋ ሳትቆርጡ መስቀሉን ተሸክማችሁ ወደፊት ተራመዱ ዝለቁ»

*ከአዘጋጆች፤* እንዳልሽው በመጽሐፍ ቅዱስ ለተጻፈው የእግዚአብሔር እውነት እስከሞት የታመነን እንድንሆንና ብዙ ተከታይ ካለው ከሰው አመለካከት ይልቅ የኢየሱስን እውነት በማመንና በመመስከር እንድንጸና አንቺም ጸልዪልን፤ ይህን የምናደርገው ግን አንቺ እንዳልሽው ማንነታችንን ለማሳየት ሳይሆን ለጌታ ኢየሱስ እስከመጨረሻው ለመታመን ነው::

♦

ከዚህ ቀጥሎ ደግሞ ከሌሎች ወገኖች የደረሱንን የማበረታቻ አስተያየት ብቻ ከሆኑት መካከል ጥቂቶቹን እናቀርባለን::

- ውድ የእውነት መንፈሳዊ ጋዜጣ አዘጋጆች፣

የእግዚአብሔር ፍቅር የልጁም የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና ሰላም ይብዛላችሁ:: እውነት ቅጽ.1.ቁ.1 1993 ዓ.ም. የመጀመሪያ ጋዜጣችሁን አንብቤ በጣም ነው የተደሰትኩት፤ እናም እግዚ አብሔር አገልግሎታችሁን ይባርክላችሁ፤ ከዚህ በፊትም በእናንተ የሚታተሙ መጻሕፍት ደርሰውኛል፤ አሁንም የእግዚአብሔርን ሕግ እንሰማና እንደ እግዚአብሔር ፈድ እንጸልይ ዘንድ የእግዚአብሔር እውቀት ያስፈልገናልና በተቻላችሁ መጠን ትብብራችሁ አይለየን::

ታደሰ ወልደሰንበት

አዲስ አበባ

- ለእውነት አሳታሚ ወገኖች

ሰላም ይብዛላችሁ፤ የሥራው ባለቤትም ለሥራው የሚያስፈልገውን ጸጋ ሁሉ አብዝቶ ይስጣችሁ:: ጋዜጣችሁ በእውነት እውነትን የማትሸራርፍ የጉዞን አቅጣጫ የምታሳይ እውነተኛ ምስክር ሆና አይቻታለሁ፣ ስለዚህ ጌታ ይባርካችሁ በርቱ እላለሁ::

ፍስሐ ደሳለኝ

ጂጂጋ

- ለእውነት መንፈሳዊ ጋዜጣ አዘጋጆች

በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም የከበረ ሰላምታዬን አቀርባለሁኝ የምታዘጋጁቸውን መጻሕፍትንና እውነት ጋዜጣን ከሰው ተውሼ ሳነብ በጣም የሚባርኩ እና አስተማሪዎች ሆነው አግኝቼአቸዋለሁ፤ ስለዚህ እኔም ከምታዘጋጁት መንፈሳዊ ማዕድ በቋሚነት መመገብ እፈልጋለሁ፣ ጌታ አገልግሎታችሁን ይባርክ::

መስፍን ገ/ሥላሴ

ጂጂጋ

♥ ወንድማችን ሽመልስ አበበ ከወላይታ ሶዶ የላክልን ግጥም ደርሶናል፤ ስለተሳትፎህ እናመሰግናለን፤ ግጥሙንና አስተያየትህን ከሌሎች አንባብያን ደርሰውን በዚህ እ ት ም

**ያለ ዋጋ የተቀበላችሁትን ያለዋጋ ስጡ/ማቴ10:8/::**

«እውነት» በየሁለት ወሩ የሚታተም የክርስቲያኖች ጋዜጣ ነው:: አሳታሚው ለጋዜጣውም ሆነ ለሌሎች መጻሕፍት የሚሰጠው የዋጋ ዝርዝር የለም፤ ለሚልካቸው ህትመቶች ሁሉ ዋጋ አይጠ ይቅም፤ ለማንበብ የሚፈልግ ሁሉ ዋጋ እንዲከፍል ሳይገደድ ፍላጎቱን በመግለጥ ብቻ ሊያገኝ ይችላል፤ አገልግሎቱ ሙሉ በሙሉ በበጎ ፈድ የገንዘብና የእውቀት አስተዋጽዖ የሚካሄድ የጸጋ አገልግሎት ነው፤ በዚሁ መልክ ጋዜጣውንም ሆነ ሌሎችን መጻሕፍት ለብዙዎች ማዳረስ እንድንችል እግዚአብሔር ልቡን ያነሳሳው አማኝ በፖስታ ቤት በሐዋላ ለአሳታሚው የገንዘብ አስተዋጽዖውን መላክ ይችላል::

እግዚአብሔር በጸጋ ያለዋጋ ከሰ ጠው የሉ ማዕድ ተካፋይ ለመሆን የምትሹ ሁሉ የሚከተሉትን ህትመቶች በመጻጻፍ ማግኘት የምትችሉ መሆኑን እንገልጻለን፤

1.ደብተራ ኦሪት
2.የዕብራውያን መልእክት አንድምታ
3.መካነ ህሩያን
4. ጦማረ ጽድቅ
5. የኦሪት ዘፍጥረት ትርጓሜ
6.መንፈስ ቅዱስ አካል ያለው መለኮት
7.የአዲስ ኪዳን መካከለኛ
8.የኦሪት ዘጸአት ትርጓሜ
9.መጽሐፈ ሰዓታት በመቅደሱ ሚዛን
10. ለጀማሪ አማኞች የሚረዳ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ናቸው::

**መጻሕፍቱንም ሆነ ጋዜጣውን ለማግኘት በአሳታሚው አድራሻ በመጻፍ ይጠይቁ**

## ማሳሰቢያ

1.ከዚህ ቀደም ከእነዚህ መጻሕፍት በከፊል ተጻጽፋችሁ ያገኛችሁ አንባቢያን መጠየቅ የምትችሉት ያልደረሷችሁን መጻሕፍት ብቻ መሆኑን እንገልጻለን፤

2.ጥያቄ ወይም አስተያየት ያለው ሰው በአድራሻችን ቢጽፍልን የምናስተናግድ መሆናችንን እንገልጻለን፤

3. የእውነት ጋዜጣ የመጀመሪያው እትም የወጣበት ወር በጋዜጣው ላይ ባለመገለጡ ይቅርታ እየጠየቅን የታተመበት ወር ሚያዝያ 1993 መሆኑን እንገልጻለን::

4. ጥቅሶች ከመዝሙረ ዳዊት ስ ጠቀሱ [illegible]

**ቴምብር/** STAMP

**COPY RIGHT© BGNLJ**
**`EUNET´ IS PUBLISHED BY : BGNLJ – NON PROFIT ORGANIZATION DEVOUTED TO THE PROPAGATION OF BIBLE TRUTH, P.O.Box 14787, ADDIS ABABA, ETHIOPA**

**ቢጂኤንኤልጀ**
**ፖ. ሣ. ቁጥር** 14787
**አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ**
**BGNLJ**
P.O.Box 14787,
ADDIS ABABA, ETHIOPA.

**ለ**/To